ቅዱስ ሲኖዶስ- በሀገር ሰላም፣ በቤተክርስቲያን፣ በግብረ ሰዶማዊያን ላይ ውሳኔ ሰጠ

**የጠ/ሚ/ሩ መልስ ይጠበቃል**

የበላዩ ማነው?
ሕግ?
መንግስት?
ቡድን?



# ግዮን


በየሳምንቱ ቅዳሜ

ግዮን ቅጽ 2 ቁጥር 60 ሰኔ 2011 ዓ.ም
ዋጋ 14.99

## አገራችን ውስጥ አስጊው ግጭት ምንድን ነው?

ፕሮፌሰር ሕዝቅያስ አሰፋ

(በተለይ ለግዮን)







## “ሞቴን እየጠበቅሁ፣ በተደበላለቀ ስሜት ውስጥ ሆኜ ታሪክን ለትውልድ አስተላልፌያለሁ”

አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ

## “ዛሬ ጥላቻ፣ መፈናቀል፣ መጋጨት የበዛው የተዋቀርንበት ሲስተም “ክልል” በመሆኑ ነው”

ፕ/ር አበራ መሸሻ



3

“ሞቴን እየጠበቅሁ፣ በተደበላለቀ ስሜት ውስጥ ሆኜ ታሪክን ለትውልድ አስተላልፊያለሁ”

**አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ**



14

“ዛሬ ጥላቻ፣ መፈናቀል፣ መጋጨት የበዛው የተዋቀርንበት ሲስተም “ክልል” በመሆኑ ነው”

**ፕ/ር አበራ መሸሻ**



9

አገራችን ውስጥ አስጊው ግጭት ምንድን ነው? ምክንያቶቹና መነሻዎቹስ?

**ፕሮፌሰር ሕዝቅያስ አሰፋ**


194 ተመራማሪዎች ከጠ/ሚ/ር ዐቢይ ሽልማትና ዕውቅና ተሰጣቸው ....2

የበላዩ ማነው? ሕግ? መንግስት? ቡድን?
መላክ ቢ. ....5

የትምህርት ፖሊሲው ትውልድ ማነቃቂያ እንጂ፣ መግደያ መሆን የለበትም! ...8

ቅዱስ ሲኖዶስ- በሀገር ሰላም፣ በቤተክርስቲያን፣ በግብረ ሶዶማዊያን ላይ ውሳኔ ሰጠ ....11

ለዛ ....13

ኢትዮጵያ ዛሬ አርበኛ ትውልድ ትፈልጋለች!
ጥላሁን መሸሻ ....19

ለአንድ አገር የሚጠቅመው የጋራ፣ የግል፣ ወይስ የቡድን የበላይነት?
መታሰቢያ መልአክ ሕይወት ....21

ሃይ ባይ ያጡት ደላሎች! ....25

ፈረቃው
ፍቅርተ ተሾመ ....28


ቀጣይ ዕትም
ቅዳሜ
ሰኔ 15
ይጠብቁን!




ቁጥር 59 ዕትም

# 194 ተመራማሪዎች ከጠ/ሚ/ር ዐቢይ ሽልማትና ዕውቅና ተሰጣቸው

9ኛው ሀገር አቀፍ የሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽ ሽልማት በአፍሪካ ህብረት አዳራሽ ሲካሄድ፤በሰነ ሥርዓቱ 194 ተመራማሪዎችንና ኢኖቬተሮች እውቅናና ሽልማታቸውን ከጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ ተቀብለዋል፡፡

ከእነዚህ ውስጥ 38 ወርቅ፣ 81 ብር፣ 66 ነሃስ፣ 4 የፈጠራ ስራ የምርምር ፣ 5ልዩ ተሸላሚ ናቸው፡፡

ከጅብራና ጥቁር አፈር ሰልፈሪክ አሲድ ማዘጋጀት (የመኪና ባትሪ ለመሙለት የሚያስችል) የአቶ አቦሃይ ውብሸት የምርምር ስራ፤ የሲግናል ዋይፋይ የተማሪ ሃምዛ የፈጠራ ስራ፤ ከፕላስቲክ እና ቆሻሻ ነዳጅ ማምረት የአቶ ሀባሻ ዳርጌ የወርቅ ተሸላሚ ከሆኑት ውስጥ ይገኙበታል፡፡

የረዳት ፕሮፌሰር ዳዊት ዳልጋ የአሜሪካ መጤ ተምች ማጥፊያ፣ የአቶ ዘውዴ ሞገስ የባቡር ሃዲድና ባቡር እግር መፋጨትን ከወዳደቁ ጎማዎች ማስቀረት የሚያስችል ምርምር በብር ደረጃ ከተሸለሙት ተጠቃሾች ናቸው፡፡

ሽልማቱን የሰጡት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ በማይመች ሁኔታ ውስጥ ሆነው፣ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የጀመሩትን የፈጠራ ስራ ጨርሰው ማህበረሰቡን እንዲጠቅሙ በማድረግ የጀግንነት ስራ እንዲሰሩ የፈጠራና የምርምር ባለሙያ



ለሆኑት ሰዎች ጥሪ ያቀረቡ ሲሆን፤

እናውቃለን ብለው ሰዎችን ከሚያጋጩ ሰዎች እነዚህ ወጣቶች በቂ ትምህርት መውሰድ ይገባቸዋልም ብለዋል፡፡

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትሩ ጌታሁን መኩሪያ (ዶ/ር ኢንጂ) በበኩላቸው የፈጠራና የምርምር ስራዎችን ከመሸለም ባለፈ ወደ ምርት እና አገልግሎት ገብተው የማህበረሰቡን ችግር እንዲፈቱ ለማድረግ በመንግስት በኩል ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

## በ2012 መንግስት 59 ቢሊዮን ብር ሊያትም ይችላል

የኢትዮጲያ መንግስት በ2012 የበጀት ጉድለቱን ለመሙላት ከሀገር ውስጥ 59.3 ቢሊዮን ብር በመበደር ሊሸፍን ማሰቡን የገንዘብ ሚንስትር ማስታውቁ ከወዲሁ አነጋጋሪ ዜና ሆኗል፡፡

መንግስታት የበጀት ጉድለታቸውን በሁለት መንገድ ማለትም ከውጪ በሚገኝ ብድር እና እርዳታ እንዲሁም ሌላኛው ከሀገር ውስጥ በቦንድ (በግምጃ ቤት ሰነድ) ሽያጭ ከባለሃብቶች ወይም ከድርጅቶች በመበደር ነው ሊሸፍኑ ይችላሉ፡፡

መንግስት ቦንድ (የግምጃ ቤት ሰነድ) የተወሰነ የብር መጠን ያላቸው እና የመክፈያ ወቅት (የተለመዱት 60፤90 እና120 ቀን) የተቀመጠላቸው ሰነዶች ያዘጋጃል፤ እነሱን ሰነዶች ባለሃብቶች ወይም ድርጅቶች ከመንግስት በመግዛት በምትኩ ገንዘቡን ለመንግስት በማስረከብ ፣ወለድ ይደምራሉ (ለምሳሌ፤ የ1 ቢሊዮን ብር ሰነድ የገዛ ባለሃብት መንግስት 7 ከመቶ ወለድ ቢጨመርበት በተቀመጠው ቀን መንግስት ለባለሃብቱ 1 ቢሊየን 70 ሚሊየን ብር አድርጎ ይከፍላል ማለት ነው)፤

ይህን መሰሉ የሀገር ውስጥ ብድር የሚካሄደው በብር ነው፤ የሚከፈለውም በብር ነው፡፡ መንግስት ከተለያዩ የግብር ምንጮች ከሚያገኘው ገቢ ነው ሊከፍል የሚችለው፡፡ ነገር ግን በ2011 መንግስት ከግብር መሰብሰብ የቻለው 160 ቢሊየን ብር ብቻ ነው፤ ከሀገር ውስጥ ወጪ አንጻር ሲታይ በ70 ቢሊየን ብር ያንሳል፤ ስለዚህ መንግስት በቀላሉ ሲያደርግ የነበረውም ሆነ ሊያደርግ የሚችለው ብርን በማተም እዳውን መክፈል መሆኑ ታውቋል፡፡ ብድሩ ከአጠቃላይ ምርት አንጻር 1.8% ቢሆንም በገቢያው ላይ ተጨማሪ ብር ታትሞ ሲሰራጭ የዋጋ ንረትን ማባባሱ እንደማይቀር እየተነገረ ነው፡፡

በምትኩ የመንግስትን ወጪ በመቀነስ፤ ዝቅተኛ ወለድ ያላቸው የውጪ ብድሮችን በማፈላለግ፤ የውጪ እርዳታን በመጠየቅ፤ ግዙፍ የመንግስት የልማት ተቋማትን በፍጥነት ወደ ግል በማዞር፤ የግብር አሰባሰብን በማዘመን፤ ሙስናን በመከላከል፤ ከውጪ የሚላኩ ገንዘቦችን ወደ ህጋዊ ስርዓት እንዲገቡ በማድረግ፤ ኮንትሮባንድን በመቆጣጠር፤ የሀገሪቷን ሰላም በማረጋጋት (ምርት እና ንግድን ለማሻሻል)፤ ወዘተ እርምጃዎች በመውሰድ የበጀት ጉድለቱን ለመሙላት ቢሞክር የተሻለ ነው የሚሉ ወገኖች ቢኖሩም በመንግስት ደረጃ ግን የመጀመሪያው አማራጭ ቅድሚያ ተሰጥቶታል፡፡

## አርቲስት እቴነሽ ግርማ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየች

የአርቲስት እቴነሽ ግርማ የቀብር ስነ ስርዓት በለቡ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ተፈጽሟል፡፡ በ1959 ዓ.ም በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ቀርሳ ማሊማ ወረዳ የተወለደችው አርቲስት እቴነሽ ግርማ ፣ ከ9 ዓመቷ ጀምራ በአዲስ አበባ ከተማ ነው የኖረችው፡፡

አርቲስት እቴነሽ ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በማረሚያ ቤቶች ተቀጥራ ህይወቷ እስካለፈበት ጊዜ ድረስ እስከ ሻለቃነት ማዕረግ ድረስ ስታገለግለል ቆይታለች፡፡ በአማርኛ እና ኦሮምኛ ቋንቋ የተለያዩ ተወዳጅ ዜማዎችን በማቀንቀን የምትታወቀው እቴነሽ ግርማ፣ ሁለት የሙዚቃ አልበሞችንና ከተለያዩ ታዋቂ አርቲስቶች ጋር በመሆን ለአድማጭ አበርክታለች፡፡

በባህላዊና የሰርግ ዜማዎቹ ከፍተኛ እውቅና ያገኘው የድምጻዊ ደመረ ለገሰ ባለቤት የሆነችው አርቲስት እቴነሽ ግርማ የሁለት ወንድ ልጆችና የአንድ ሴት ልጅ እናት ነበረች፡፡

## ከዓመቱ የትምህርት ጅማሬ አንስቶ የብሔር ግጭት ለመፍጠር የተዘረጋ መረብ መኖሩ ታወቀ


በዓመቱ የትምህርት ማገባደጃ ላይ ሆን ተብሎ በተሰራ ሴራ፣ በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ሁከት በመፍጠር፣ በሰውና በንብረት ላይ ጉዳት ያደረሱ ግለሰቦች በቁጥጥር ስር እየዋሉ መሆናቸው ታውቋል፡፡

ግጭት በተፈጠረባቸው ዩኒቨርሲቲዎች የሚገኙ ተማሪዎች ለፈተና ከመዘጋጀት ይልቅ ስለ ደህንነታቸው እንዲያስቡ የተገደዱ ሲሆን፤

ይህ ደግሞ ተማሪዎቹ ላይ ከፍ ያለ ተፅዕኖ እንደፈጠረባቸው መገንዘብ ተችሏል፡፡

የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስትር ዲኤታ ዶክተር ሳሙኤል ክፍሌ ድርጊቱ ጊዜው የትምህርት መገባደጃ በመሆኑ ተማሪው አመት የለፋበትን ጥረት ዋጋ ለማሳጣት እየተደረገ ያለ እንቅስቃሴ እንደሆነ ይናገራሉ፡ ፡ችግሩ በተለይ በአንድ ቦታ በሚፈጠር ሁከት ብሄርን ሽፋን በማድረግ ሌላም ቦታ እንዲስፋፋ የሚያደርግ መረብ ከአመቱ የትምህርት ጅማሬ አንስቶ እስከ መጨረሻው ድረሽ ተዘርግቶለት እየተሰራ ስለመሆኑም ይፋ አድርገዋል፡፡

ሰሞኑን ግጭት ከታየባቸው ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ በሆነው የደብረ ብርሀን ዩኒቨርሲቲ ሰፊ ውይይት ከተደረገ በኂላ እርቅ መፍጠር የተደረገ ሲሆን፤ ተማሪዎችም ከእርቁ በኂላ በቀጣይ ችግሩ እንዳይደገም መንግስትም ሆነ ተማሪው ሀላፊነታቸውን ሊወጣ እንደሚገባ አሳስበው፣የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴርም በመንግስት በኩል ሊሰሩ የሚገባቸው ስራዎች ሁሉ ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ በመግለጽ ሰላሙን ከማስጠበቅ በተጓዳኝ ከውስጥም፣ ከውጭም ሆነው ሁከቱን የሚቀሰቅሱ አካላትን በማጣራት ገ እርምጃ እየተወሰደ ነው ብሏል፡፡




# “ሞቴን እየጠበቅሁ፣ በተደበላለቀ ስሜት ውስጥ ሆኜ ታሪክን ለትውልድ አስተላልፋያለሁ”

## *አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ (በተለይ ለግዮን)*

የነፃነት ታጋዩ አንዳርጋቸው ጽጌ ዕድሜያቸውን ሙሉ ለኢትዮጵያ ፖለቲካ የሰጡ፣ ዕውቀታቸውንና ልምዳቸውን ትውልድ ለትውልድ ከማካፈል ወደ ኋላ የማይሉ ታላቅ የፖለቲካ ሰው ናቸው፡፡ ኢህአዴግ አዲስ አበባን በተቆጣጠረበት ማግስት ከኢህዴን (ብአዴን) ጋር በመሆን፣ ለዚህች አገር መልካም ነገር ሰንቀው የቻሉትን ለመስራት ቢጥሩም ፤በብሔርተኝነት ፖለቲካና አገር የመናድ አባዜ የተለከፈው አምባገነኑ ስርዓት ሕልማቸውን ዕውን ለማድረግ ምቹ ሊሆንላቸው ባለመቻሉ፣ ሁሉን ነገር ዕርግፍ አድርገው ትተው ኢህአዴግን ለመታገል ቆርጠው ተነሱ፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ተሰሚነት ያላቸውና በኢትዮጵያውያን ዘንድም አመኔታ የተቸራቸው አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ፤ በምርጫ 97 ወቅት የቅንጅት አባል በመሆን ባደረጉት እንቅስቃሴ የተበሳጨው ኢህአዴግ ክፉኛ ደብድቦ ወህኒ ወረወራቸው፡፡ ከእስር ከወጡ በኋላ ከመሰል ባልደረቦቻቸው ጋር በመሰረቱት ግንቦት ሰባት ለዴሞክራሲና ለአንድነት ፓርቲ፤ ከሰላማዊ ትግል ባሻገር የትጥቅ ትግሉን የሚያካሂድ ሁለገብ እንቅስቃሴ ከአሜሪካና ለንደን እስከ ኤርትራ በርሃ ድረስ ሰፊ መረብ መዘርጋታቸው፤ በአሸባሪነት አስፈርጇአቸው የሞት ፍርድ ተላልፎባቸው ነበር፡፡

የመን ሰንዓ ላይ በብዙ ሚልየን የሚቆጠር የሕዝብ ገንዘብ ያላግባብ አፍስሶ፣ በሕገ ወጥ መንገድ ከኤርፖርት አፍኖ ያመጣቸው የጌታቸው አሰፋ ቡድንና የሕወሓት መንግስት፤ ለረዥም ጊዜ ከማንም ሳይገናኙ ለብቻቸው አስሮ ቢያስቀምጣቸውም፣ ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አህመድ ስልጣን በያዙ ማግስት ነፃ ወጥተዋል፡፡ አቶ አንዳርጋቸው እስር ላይ ሆነው የፃፉትና የበርካቶችን ቀልብ የጻፈውን መጽሐፍ አስመልክቶ፣ የግዮን ጋዜጠኞች ፍቃዱ ማ/ወርቅና ሮቤል ምትኩ በአሁን ሰዓት ከሚገኙበት ለንደን ከተማ በስልክ እንዲህ ባለ መልኩ አነጋግረዋቸዋል፡፡

▶

**ግዮን፡- ሰሞኑን ለገበያ ያቀረበው መጽሐፍዎ "ትውልድ አይደናገር፤ እኛም እንናገር" የሚል መጠሪያ የሰጡበት ምክንያት ምንድን ነው?**

አንዳርጋቸው፡- ከ1966 ዓ.ም አብዮት በኋላ የተፃፉ በርካታ የታሪክ ወይም የፖለቲካ መጽሐፎች አሉ፤ እነዚህን መጽሐፎች በምመለከትበት ሰዓት ላይ፣ የተለያዩ የፖለቲካ ጎራ ውስጥ የነበሩ ኃይሎች እንደፃፏቸው መገንዘብ ችያለሁ። ሁሉም መጻሕፍት የተጻፉት በድርጅቶቹ አመራር ነው። በዋነኝነት እነዚህ ጻሕፍት ለማድረግ የሞከሩት እያንዳንዳቸው የድርጅቱ መሪዎች ሲከተሉት ከነበረው የፖለቲካ ዕምነትና ሲሰሩት የነበረውን የፖለቲካ ስራ ትክክለኛነት ከማሳየት ብቻ የተፃፉ ፣ የድርጅት መስመር ተከላካይነት የሞላቸው፣ የራስን ማንነት ለመከላከል የተፃፉ የሚመስሉ ናቸው።

በነገራችን ላይ ይሄ ሁሉም ላይ ነው የታየው። የደርግ ሰዎች፣ እሱን ሲቃወሙ የነበሩት የመኢሶን፣ የኢህአፓና የሌሎች ድርጅቶችም ሰዎች፤ ወያኔም ቢሆን በአሸናፊነት አንግል ነው ታሪክ የሚጻፈው። ስለዚህ እውነተኛ የሆነውና ከእነዚህ መሪዎች ፅሁፍ ውጪ ያለውን የመሀል ታሪክ ያቀረበ ሰው አልነበረም፤ ወይም ጠፍቷል። እኔ ለማድረግ የሞከርኹት አንደኛ ከ1966 ዓ.ም በኋላ የነበረውን የአገራችን ታሪክና ፖለቲካ በተቻለ መጠን ከድርጅት መስመር ተከላካይነት ወጪ በሆነ ነው። ለዛም እኔ አድቫንቴጅ አለኝ ብዬ ስላሰብኩኝ ነው።

ለምሳሌ እንደ ኢህአፓ አመራር የኢህአፓን ታሪክ በማቀርብበት ሰዓት ላይ የምከላከለው መስመር የለኝም። ወይንም ደግሞ በወገንተኝነት የምጠየቅበት ነገር የለም፤ በተሰሩት ጥፋቶች አልያም ሌሎች ነገሮች። የድርጅት አባል በሆንኩበት ኢህአፓ ሰፊ ተሳትፎ ነው የነበረኝ፣ ቁልፍ የነበሩ ብዙ ነገሮችን ማወቅ የምችልበት ስራ እንደነበረኝ በመጽሐፉ ውስጥ በግልፅ ታዩታላችሁ። የማዕከላዊ ኮሚቴ፣ የፖሊት ቢሮ አባል፣የኢህአፓን የገንዘብና የመሳሪያ ቦታዎችን በሙሉ ስለማውቃቸው እነሱን ማንቀሳቀስ ነበር ስራዬ። በተለያዩ ኦፕሬሽን ውስጥ የገባሁበትና የተረፍኩበት ሁኔታም አለ፤ አመራሮችን በቅርበት አጠገባቸው ቁጭ ብዬ ሲወያዩ፣ ሲጨዋወቱ የነበረውን አጋጣሚዎች የማዳመጥ ዕድል ስለነበረኝ፤ በተጨማሪም በዛ ሰዓት በቂ የፖለቲካ ዕውቀት ያለኝ፣ ነገሮችን የመመዘን፣ የመታዘብ የምችልበት የወጣትነት አቅምም ስለነበረኝ፣ ይሄንን የኢህአፓ ታሪክ ቢሆን የድርጅት መሪዎች ከሚፅፉት ነገር በላይ ልፅፍ እንደምችል ስላወቅሁ ነው ያዘጋጀሁት።

የመኢሶንም ሆነ የደርግ ሰዎች ለምሳሌ ኮ/ል መንግስቱ ኃ/ማርያምም ሆኑ ፍቅረስላሴ ወግደረስ የጻፉት መጽሐፍት በተለየ ነገሮችን በዚህ አዲስ መጽሐፍ ውስጥ በትክክለኛው መንገድ ማየት ይቻላል። እነሱ የድርጅት መስመር ነው የተከተሉት። የሰሩት በጎ ነገር ካለ፣ በጎውን ለማየት የሚያስችል አቅም አለኝ፣ ያጠፉት ጥፋትም ካለ ያንን ማሳየት ይቻላል። እነሱ ግን ሁሉንም ነገር በሸመጠጠ መልኩ "እኛ ምንም ያጠፋነው ነገር የለም፣ ሌሎቹ ናቸው ያጠፉት፣ ለእዚህም ነገር ያደረጉን" ነው እያሉ ያሉት። ባላንሱን የጠበቀ የታሪክም፣ የፖለቲካም ሰነድ ለትውልድ እንዲደርሰው ለማድረግ ነው እኔ የሞከርኩት።

ከዛም በተጨማሪ ወደ ኋላ ተመልሼ የአገራችንን ታሪክ ለመቃኘት ሞክሬያለሁ። እዛም ላይ ቢሆን ፖለቲካውን እያጦዘ ያለው የታሪክ ትርክት አለ። ስለዚህ ይሄ የታሪክ ትርክትም ከፖለቲካ አኳያ የሚጎትቱት ኃይሎች እንደሚያስቀምጡት ዓይነት እንዳልሆነ፣ በጣም የተወሳሰበና የተመሰቃቀለ ታሪክ እንደሆነ ለማሳየት ፣ አንዳንዱ ታሪክ ደግሞ ሆን ተብሎ ጭራሹንም ያልተተረከ በመሆኑ፤ ለምሳሌ እንደ አዲስ አበባ ዓይነት ከተማ ሲቆረቆር የነበረበት ሁኔታ፤እነማን ነበሩ መጀመሪያ? የሚለውን ለትውልድ ለማሳወቅ ሞክሪያአለሁ።

**ግዮን፡- በትክክል ከታሪክ አኳያ፣ አዲስ አበባ ላይ መጀመሪያ እነማን ነበሩ የሚኖሩት?**

አንዳርጋቸው፡- መጀመሪያ ላይ ሙሉ ለሙሉ ማለት ይቻላል ከተማው ባዶ ነው የነበረው፤ ከተማ የሚባልም ነገርም አልነበረም። ጫካና ደን የወረሰው ስፍራ ነው የነበረው። እዚህ ቦታ መጀመሪያ የመጡት፣ ወታደራዊ አዛዦችና ወታደሮች ሲሆኑ ከወታደሮቹና ከአዛዦቹ ጋራ ደግሞ ቀድመው የመጡት፣ የጌቶቹ ባሮች እንደሆኑ እንረዳለን። ቀላል ቁጥር ያልነበረው፣ ነፃ ከሚባለው ዜጋ ቁጥር በላይ ባሪያ በዛ ዘመን በአዲስ አበባ ይኖር እንደነበር፣ ከእነዚህ ወታደሮች ጋር ተያይዞ፤ ሚስት የሌለው ወታደር ስለመጣ ይሄን ወታደር የሚያስተናግዱ፣ ጠላ ቤቶችና ሴተኛ አዳሪዎች የመጀመሪያዎቹ የአገልግሎት ኢንዱስትሪንም በዚህ መንገድ በመጣል ነው በከተማዋ ላይ የሰፈሩት። ከተማዋም ስትቆረቆር የወታደሮች እና የሴተኛ አዳሪዎች ከተማ እንደሆነች በሚያስረዳ መልኩ ሰፋ ያለ ነገር በመጽሐፌ ውስጥ ይገኛ ቀርቤያለሁ።

ባርነትን በተመለከተ እንዲሁ ስፋት ያለው መረጃ ቀርቧል። በሀገራችን ውስጥ አይረሴ የሆነው ታሪክ እስካሁን እምብዛም አልተጻፈም፤ ይሄ ለምን እንደሆነ አይገባኝም። በዚህ መልኩ ወደ ኋላ ተመልሼ የተረሱ፣ ያልተወሱ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ታሪክ ለማቅረብና የተሟላ ታሪክ ለትውልድ ለማስተላለፍ ነው የጣርኩት።

> **ከእስር በተፈታሁ ማግስት ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አህመድ ቢሮአቸው ጠይቀውኝ ስንገናኝ ያነሳሁላቸው አንዱ ጥያቄ የመጽሐፉን ጉዳይ ነው፡፡ "እሱ ምንም አይሆንም፣ የት ይደርሳል ብለህ ነው፣ ይገኛል" የሚል ምላሽ ሰጥተውኝ ነበር፡፡**

**ግዮን፡-ብዙ ጊዜ የታሪክ መጻሕፍት ከራስ ፖለቲካ አቅጣጫ በመነሳት የሚጻፉ ከመሆናቸው አኳያ፤ ይሄ የእርስዎ አዲስ መጽሐፍ ትክክለኛውን መልስ የሰጣል ብለው ያምናሉ?**

አንዳርጋቸው፡-ይመልሳል።እኔ በበኩሌ እንደዛ ነው የማምነው። ይሄን ዓይነት መጽሐፍ ካለ ሌሎች ፀሐፊዎች መጠቀም ይችላሉ። ግን እኔ እንዲህ ዓይነት መጽሐፍ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው የተፃፈው ብዬ አስባለሁ። መጽሐፉ በዚህ መንገድ ለምን መፃፍ እንዳለበት የመጀመሪያዎቹ የመጽሐፉ ምዕራፎች ላይ በግልጽ ተቀምጧል። የመጀመሪያዎቹ ምዕራፎች የሚያወሩት ታሪክ ምንድን ነው? ታሪክ ዝም ብሎ የትልልቅ ሰዎች፣ የአሸናፊ ሰዎች ታሪክ ብቻ ሳይሆን፤ ከትልልቆቹ ጄነራሎች፣ ከትልልቆቹ መሐንዲሶች፣ አርክቴክቶች ስር የነበሩ ኩሊዎችን፣ ተዋጊዎችን የሚጨምር እንደሆነ፤ በትልልቆቹ የድርጅት መሪዎች ስር የነበሩ በሺዎች የሚቆጠሩ ተራ አባላት የሰሩት መሆኑን አንባቢ ማየት እንዲችል፣ ብሎም ታሪክ የምንለው ነገር የተሟላ እንዲሆን ከተፈለገ፣ የመሪዎቹ ብቻ ሳይሆን የተመሪዎቹን ታሪክ ጭምር ባካተተ እንዴት መሆን እንደሚገባው ለማሳየት የተሞከረበት አፃፃፍ ነው።

ሁለተኛ ታሪክ ማለት ዝም ብሎ ስታቲስክስ መደርደር አይደለም። ይሄን ያህል ወታደር በዚህ ቦታ ሞተ፤ በዚህ ዓመት ይሄ ነገር ተፈፀመ፣ እከሌ በዚህ ጊዜ ተወልዶ በዚህ ጊዜ ሞተ፤ የሚል ዕርባና የሌለው፣ የዓመተ ምህረትና የሰው ስም ድርደራ እሱ ታሪክ ነው የሚል ዕምነት የለኝም። እንዲህ ዓይነቱ ነገር የመዝገብ ቤት ስራ ነው ብዬ ነው ያስቀመጥሁት።

ታሪክን ትውልድ እንዲረዳው ከተፈለገ፣ በተወሰነ ደረጃ ሕይወት ባለው መልክ የማስቀመጥ ኃላፊነት አለብን፣ ትውልድ እንዲረዳው ከቁጥር በታች ወርዶ በትክክል ማህበረሰቡ ምን ይመስል ነበር? ያ ታሪክ በተሰራበት ወቀት፤ የሚለውን ማስቀመጥ ይጠይቃል። በዘመኑ በነበሩት ሰዎች ስሜቶች ላይ የተወሰነ ነገር ማለት ይገባል፤ የሚል ዕምነት አለኝ። በርግጥ የእዛ ዓይነቱ አፃፃፍ የሚያስነሳው ጥያቄም እንዳለ፣ እንዲህ ዓይነቱ አፃፃፍ ተመሳሳይ ጥያቄ አስነስቶ በአንድ ምዕራፍ ላይ እንዴት እንደተመለሰም መግለጫ ሰጥቼበታለሁ። ስለዚህ ለትውልድ በደንብ ምላሽ የሚሰጥ የታሪክ መጽሐፍ ነው ብዬ አምናለሁ።

**ግዮን፡- ዕስር ላይ ከነበረህ ጊዜ ውስጥ ከነበሩት ዓመታት በአራት ወራት ውስጥ መጽሐፉን የጻፍክበት መነሻ ምክንያትና**

ቀሪውን በገጽ 26 ይመልከቱ

# የበላዩ ማነው?

# ሕግ? መንግስት? ቡድን?



መላክ ቢ.

## ከ27 ዓመታት በፊት

ኢህአዴግ “በኢትዮጵያ የህግ የበላይነት ሰፍኗል” ብሎ አፉን ሞልቶ ይናገር ነበር፡፡ ኢህአዴግ ይህንን የሚናገረው ያወጣቸው ህጎችና መመሪያዎች ህዝቡን ጸጥ ለጥ አድርገው ስለገዙለት ፣ በውጤቱም እስር ቤቶቹ ወንጀለኛ ብሎ በከሰሳቸው ዜጎች ስለሞሉለት፣ ኮሽ የማይል ሰላም መሰል ጸጥታ ስለነገሰለት ነበር፡፡ በሃገሪቱ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች በከፍተኛ የህግ ቁጥጥር ስር ስለወደቁ ፣ የጋዜጠኝነት ስራ ወንጀል እስኪመስል ድረስ የፕሬስ ነጻነት ላይ ከባድ ገደብ ስለተጣለ፣ መደራጀት በከፍተኛ የደህንነት ክትትል ስር ስለወደቀ፣ ሃሳብን በነጻነት መግለጽ ከባድ አደጋ አስከትሎ የሚመጣ ጣጣ ስለሆነ፣ በአጠቃላይ ኢህአዴግን ተቃውሞ በህዝብ ዘንድ ሞገስ ማግኘት የነፍሰገዳይ ያህል ቁም ስቅል ስለሚያሳይ ነበር ኢህአዴግ በኢትዮጵያ የህግ የበላይነት ሰፍኗል ብሎ ሲደሰኩር 27 ዓመታትን ያሳለፈው፡፡

‹‹በኢትዮጵያ ከሕግ የበላይነት ይልቅ የመንግስት ኃያልነት ገዝፏል፤ በሕግና በሕግ ብቻ ከመመራት ይልቅ በመንግስት መልካም ፈቃድ እየተዳኘን ነው፣ መንግስት በፍትህ ስርዓቱ ጤናማ ሂደት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ እንቅስቃሴዎችን በግልጽና በአደባባይ እያካሄደና ሕግን እየጣሰ ነው፡ ፡ ራሱ በህገመንግስቱ የደነገገውን የግለሰቦች መብት ለፖለቲካ ፍላጎት ማሟያ ሲል በግልጽ በመጣስ ጥፋት እየፈጸመ ነው፡፡ በዚህም ዜጎች በፍትህ ስርዓቱ ላይ እምነት አጥተዋል›› የሚሉ ጉምጉምታዎች የበረከቱትም በነዚያው ኢህአዴግ “የህግ የበላይነት ሰፍኗል” ብሎ በሚናገርባቸው 27 ዓመታት ውስጥ ነበር፡፡

ከሰሞኑም በኢትዮጵያ የህግ የበላይነት አለ የለም የሚሉ የክርክር መድረኮች ተከፍተዋል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ ከዐቃቤ ህጎችና ጠበቆች ጋር ካደረጉት ውይይት ጀምሮ የተለያዩ የሲቪክ ተቋማት እስካደራጇቸው መድረኮች ድረስ የህግ የበላይነት ጽንሰሃሳብ እና አተገባበር እንዲሁም በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ያለው ገጽታ ውይይት ሲካሄድበት ቆይቷል፡፡

ለመሆኑ ዛሬስ በኢትዮጵያ የበላዩ ማነው? ህግ? መንግስት? የተደራጀ ቡድን? እነዚህን ጥያቄዎች ከመመለስ በፊት በርግጥስ የህግ የበላይነት በኢትዮጵያ ምን መልክ አለው የሚለውን ጥያቄ መመለስ ተገቢ ይሆናል፡፡

## የህግ የበላይነት ምንድነው?

የአንድ ዲሞክራሲያዊ አገዛዝ ዋነኛ መገለጫ የሕግ የበላይነት /rule of law/ ነው ይላሉ የዘርፉ ምሁራን፡፡ የህግ የበላይነት በቀደመው ኢህአዴግም ይሁን በዛሬው ኢህአዴግ ምን መልክ ላይ ይገኛል የሚለው ጥያቄ ብዙ ውይይትና ክርክር የተደረገበት ነው፡፡

አሪስቶትል የተባለው ስመጥር የግሪክ ፈላስፋ ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት ስለ ሕግ የበላይነት ሲናገር ‹‹የሕግ የበላይነት ከማንኛውም ሰው የበላይነት የተሻለ ነው››! “The rule of law is better than that of any individual”. ብሎ ነበር፡፡ ከአርስቶትል በኋላ የመጡት ምዕራባዊያን የህግ ተመራማሪዎችም ይህንንም ሃሳብ ይበልጥ በማጠናከር ‹‹ንጉስ ራሱም ቢሆን በሰዎች የበላይነት ስር መሆን አይገባውም፤ ከአምላክና ከሕግ በታች እንጂ፡፡ ምክንያቱም ንጉስ ያደረገው ህጉ ነውና›› “The king himself ought not to be subject to man, but subject to God and the law, because the law makes him King”. በማለት የሕግ የበላይነትን ጽንስ ሃሳብ ይበልጥ ያጸኑታል፡፡

ዘመናዊ የዲሞክራሲ ፅንሰ ሀሳብም የህግ የበላይነትን የሚገልጽበት መንገድ አርስቶትል ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት ከሰነዘረው በተለየ ሃሳብ አይደለም፡፡ “ማንኛውም ሰው ወይም ተቋም በሕግ ፊት እኩል ነው” የሚባለው የህግ የበላይነት ከማንኛውም ሰው ወይም ተቋም ወይም ፓርቲ የሚበልጥ ጉዳይ በመሆኑ ብቻ ነው፡፡

ዛሬ በአንደኛው ዓለም ተቀባይነት ያገኘው የሕግ የበላይነት ጽንሰ ሀሳብ ዋና መሰረቱ የግሪክ ፈላስፋዎች ያፈለቁት ሀሳብ ነው፡፡ ያም ሆኖ ግን የሕግ የበላይነት ለሚለው ጸንሰ ▶

ሐሳብ የተለያዩ ወገኖች የተለያየ ትርጉም የሚሰጡት በመሆኑ አንድ ወጥ ወይም ሁሉንም ወገን የሚያስማማ ፍቺ እስካሁን ድረስ አልተገኘለትም፡፡ ያም ሆኖ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የተወሰነውና በዓለም አቀፍ ስርዓት ውስጥ የታቀፉት ተቋሞችም ሆኑ መንግስታት የተስማሙበት የሕግ የበላይነት ውሳኔ በንድፈ ሐሳብ ደረጃም ቢሆን ሁሉንም ወገን ሊያስማማ የሚችል የሕግ በላይነት ትርጓሜ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በዚህም ውሳኔ መሰረት ‹‹ለተባበሩት መንግስታት የሕግ በላይነት ማለት የአስተዳደር መርህ ሲሆን በዚህ መርህ መሰረት ግለሰቦች ፣ ተቋሞችና ቡድኖች የግልም ሆኑ የመንግስት፣ ራሱን መንግስትን ጨምሮ ተጠያቂ የሚሆኑት በይፋ ለተደነገጉ በእኩልነት ለሚተገብሩ፣ በነጻነት ፍርድ ለሚያገኙ ከዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብቶች መመዘኛዎችና ደረጃዎች ጋር የተጣጣመበት ሥርዓት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የሕግ የበላይነት በሕግ ፊት እኩል መሆንን፣ ለሕግ ተጠያቂነትን፣ በሕግ አተገባበር ፍትሐዊነትን ፣ የስልጣን ክፍፍልን በውሳኔ ሰጪነት መሳተፍን ፣ ሕጋዊ እርግጠኝነት ፣ በዘፈቀደ የሚወሰዱ እርምጃዎችን ማስቀረትና የሕግ እርምጃዎችንም ያካትታል››

ኢህአዴግ መራሹ መንግስት የተባበሩት መንግስታትን ቻርተር በመፈረም፣ የተለያዩ ዓለም አቀፋዊ የሰብዓዊና ፖለቲካዊ መብቶች ድንጋጌዎች በመቀበልና በህገ መንግስቱ ውስጥም በማካተት ዓለም የተስማማባቸውን ሰነዶች ተቀብሏል፡፡ እንዲህ በማድረጉ የሚመሰገነውን ያህል ለማስፈጸም ቃል ገብቶ የተቀበላቸውን እነዚህኑ መርሆዎች በተግባር በመተርጎም ረገድ ግን ዳተኛ መንግስት ነው፡፡

ከዚህ ቀደም በነበረ አሰራሩ ኢህአዴግ ለእነዚህ ድክመቶቹ መሸፋፈኛ ከሚጠቅሳቸው ምክንያቶች ውስጥ ‹‹የዲሞክራሲ ተሞክሮ እጥረትና››! ‹‹የአፈጻጸም ድክመት›› የሚሉ ሁለት ከአፉ የማይነጥላቸው ምክንያቶች ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ዛሬ የኢህአዴግ ሶፍትዌር ተቀይሯል፡፡ ኢህአዴግ ግን አሁንም አለ እየተባለ ነው፡፡ የዶክተር ዐቢይ አስተዳደር አዲሱን ኢህአዴግ እየመራ ባለበት በዚህ ዘመን ደግሞ የህግ የበላይነት ጥያቄ ከቀደመው ዘመን ጥያቄ በተለየ መልኩ ወደመድረኩ መጥቷል፡፡ ቡድኖች ከመንግስት በልጠው ተፈሪ ሆነዋል፡፡ የፌዴራል መንግስቱ በክልሎች ተንቆ የህግ አስከባሪነት ቀርቶ የገላጋይነት ሚናው እንኳን እየተንቋሸሸ ነው፡፡ ወንጀሎች ተበራክተዋል፡፡ የደቦ ፍርድ በሃገሪቱ አለ፡፡ ማፈናቀል፣ መግደል እና መዝረፍ ብርቅ አልሆነም፡፡ ጸብ አነሳሽ እና ቆስቋሽ አክቲቪስቶች በነጻነት ይራመዳሉ፡፡ ዜጎች በገዛ ሃገራቸው ከቦታ ቦታ ለመዘዋወር አዳግቷቸዋል፡፡ ህግ መጫወቻ እቃቃ ሊሆን ተቃርቧል፡፡ ሰዎች በፖሊስ እና በፍርድ ቤት ላይ እምነት እያጡ ነው፡፡

በነዚህና በሌሎችም ብዙ ምክንያቶች የህግ የበላይነት አደጋ ላይ ወድቋል፡፡

ለመሆኑ መንግስት በዚህ ሀገር ላይ እያረጋገጠ ያለው የህግ የበላይነትን ነው ወይስ የቡድን እና ግለሰብ አምባገነንነትን? የዶክተር ዐቢይ መንግስት የህግ የበላይነትን በማስፈን ረገድ ያሉበትን ችግሮች ማረም ሲችል ይህን አለማድረጉ ለምን ይሆን? እነዚህን ጥየቄዎች ስናነሳ መንግስት ስህተቶቹን ለማረም ያልቻለባቸውን መሰረታዊ ምክንያቶች መጠቆማችን ግድ ይሆናል፡፡

## በሌለ የህግ የበላይነት ህግ አለ ብሎ ማሰብ

በኢትዮጵያ የህግ የበላይነት አለመኖርን አንስተው መንግስትን የሚሞግቱ ወገኖች “የህግ ማስከበርና የህግ የበላይነትን የማረጋገጥ አፈጻጸም ድክመቶቹ የሚመነጩት የመርሁን ትርጉም በአግባቡ ካለመገንዘብ ብቻ ሳይሆን ይህንን መርህ ተሸክመው ማስፈጸም የሚችሉ ዲሞክራሲያዊ ተቋሞች ካለመመስረታቸው ወይም ካለመጠናከራቸውም ጭምር ነው” ይላሉ፡፡ በኢትዮጵያ የህግ የበላይነት በሌሎች ተዛማጅ መርሆች አልተደገፈም የሚሉ ተቺዎች በበኩላቸው በህግ አውጪነት፣ በህግ ተርጓሚውና በህግ አስፈጻሚው መካከል እውነተኛ ልዩነት (separation of powers) ባለመኖሩ የሁሉም ነገር ግንባር ቀደም አስፈጻሚ ገዥው ፓርቲ ኢህአዴግ ሆኖ መኖሩን ለዛሬው የህግ የበላይነት አለመከበር ምክንያት አድርገው ያቀርባሉ፡፡

**...አሪስቶትል የተባለው ስመጥር የግሪክ ፈላስፋ ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት ስለ ሕግ የበላይነት ሲናገር ‹‹የሕግ የበላይነት ከማንኛውም ሰው የበላይነት የተሻለ ነው››! “The rule of law is better than that of any individual”. ብሎ ነበር፡፡ ከአርስቶትል በኋላ የመጡት ምዕራባዊያን የህግ ተመራማሪዎችም ይህንንም ሃሳብ ይበልጥ በማጠናከር ‹‹ንጉስ ራሱም ቢሆን በሰዎች የበላይነት ስር መሆን አይገባውም፤ ከአምላክና ከሕግ በታች እንጂ...**

እንደነዚህ ተቺዎች ምልከታ ኢህአዴግ ዛሬም ድረስ የገዢ ፓርቲነት ባህሪውን ትቶ የመንግስትነት ባህሪን በመልበሱ ራሱን ህግ አውጪም፣ ህግ አስፈጻሚም፣ ህግ ተርጓሚም በማድረግ በመንግስት እና በፓርቲ መካከል ያለውን ልዩነት ጥሶ የህግ የበላይነት ላይ ጥላ አጥልቷል ይላሉ፡፡ በፓርቲና በመንግስት መካከል ያለው የጥቅምና የሚና መገናኘት (convergence of interest) የፍትህ ስርዓቱ ነጻነት ላይ የጎላ ጥያቄ ማስነሳቱን የሚናገሩት ተቺዎች ይህም የፍትህ ስርዓቱን በነጻነት መንቀሳቀስ እንዳይችል ማድረጉን ነው የሚናገሩት፡፡ በዚህም የተነሳ ማንም ቡድንና ግለሰብ በፖለቲካ ፍላጎት ሲጠዛጠዝ በመካከል ህዝብን መጨፍለቅ እና ለመከራ መዳረግን ስራዬ ብሎ ይዞታል ባይ ናቸው፡፡ በዚህም ህግ ይከበርልኛል ብሎ መብቱን የሚጠብቀው ህዝብ በሃገሩ ህግ እንደሌለ በመስጋት ሰዎች ከህግ በላይ መሆናቸውን እንዲያስቡ አድርጓቸዋል፡፡

## የጠንካራ መንግስት መሰረት መለላት

ኢህአዴግ በጠመንጃ ያፈረጠመውን ጡንቻውን ይዞ ወደመንግስትነት ሲመጣ ጠንካራ መሰረት አለኝ ብሎ ያስብ ነበር፡፡ ነገር ግን የአንድ መንግስት ጠንካራ መሰረት ጠመንጃ ሳይሆን ህግ እና ስርዓት ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ በህግ እና ስርዓት የሚያምንና ለዚህ የሚገዛ ህዝብ መፍጠር ወሳኝ ነጥብ ነው፡፡ በዲሞክራሲ አግባብ መንግስት ማለት የህዝብ ውክልና ያለው ተቋም ማለት ሲሆን የህግ የበላይነትን በሚገባ ማስፈጸም ካልቻለ ግን ይህ መንግስት የህዝብ መንግስት ሳይሆን የተወሰኑ መደቦች ወይም ጥቂት ቡድኖች ፍላጎት ማስፈጸሚያ ነው የሚል ትንተናም ይቀርባል፡፡ አሁን ባለንበት የብሄር ፖለቲካ ጽንፍ መንግስትን እየዘወረ ያለው ገዢ መደብ ከቀደመው የአንድ ብሄር ስብስብ ወደሌላ አንድ ብሄር ስብስብ እንዲሸጋገር አድርጎታል ተብሎም ይተቻል፡፡ በዚህ ሳቢያም የኢህአዴግ መንግስት የህግ የበላይነትን ማስፈጸም ያልቻለው ማህበራዊ መሰረቱ በብሄር ቡድኖች ላይ የተጣለ በመሆኑ ነው፡፡ የኢህአዴግ የእስካሁን ስልጣን አንድም በጠመንጃ ሌላም በተጭበረበረ ምርጫ በተገኘ ውክልና እንጂ በእውነተኛና ሰፊ ህዝባዊ ውክልና የመጣ ባለመሆኑ ለመሰረታዊ የህግ የበላይነት ጥሰት ትልቁን ድርሻ ይዟል፡፡

ህዝባዊ ውክልና ባለበት ስርዓት ውስጥ የስልጣን ክፍፍል (separation of powers) እንዲሁም የመቆጣጠሪያና ሚዛን ማስጠበቂያ ተቋሞች (checks and balances) በሚገባ ይበጃሉ፡፡ ኢህአዴግ የህግ የበላይነት ጥያቄ ውስጥ ሲገባ ይህንን መሰረታዊ ጥመት የሚያስተካክልበት አሰራር እንኳን የለውም፡፡ ከመደበኛው ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጨማሪ ሕገ መንግስታዊ ፍርድ ቤት (constitutional court) አልተቋቋመም፡፡ በዚ ሳቢያ የህግ የበላይነት ጥሰትን ተመልክቶ ውሳኔ የሚሰጥ አካል የለም፡፡

▶ በሀገራችን የሚታየው አንዱ የህግ የበላይነት ጠፍቶ መንግስት፣ ቡድን ወይም ግለሰብ ከህግ በላይ የሚሆኑበት ችግር እንደዚህ አይነት ገለልተኛ የህገመንግስት ፍርድ ቤቶች ያለመኖር ችግር መሆኑን ብዙዎች ይተቻሉ።

## የህግ ስርዓቱ ደካማነት

ሰሞኑን ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር ውይይት ያደረጉት ዐቃቢ ህጎችና ጠበቆች በሃገሪቱ የህግ የበላይነት ያለመስፈኑ ምክንያት የህግ ስርዓቱ ጥሰት ነው ይላሉ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ዳኛ ሆነው እየተሾሙ የሚገኙት ሰዎች በእድሜ ከበሰሉት እና ከተረጋጉት ሰዎች ይልቅ ወጣቶች መሆናቸው የፍትህ ስርዓቱ አቅም ባላቸው ሰዎች እንዳይመራ ምክንያት ሆኗል ብለው አስተያየት የሰጡ አሉ። "በሌላው ሀገር ዳኛ ሆነው የሚሾሙ ሰዎች ከ12 ክፍል ሳይሆን በመጀመሪያ ደረጃ በማህበራዊ ሳይንስ (social science) የመጀመሪያ ዲግሪ ሊኖራቸው ግድ ነው። ዳኝነት ከባድ ስራ ነው። ቴክኒክና ሙያውን ማወቅ ብቻ ሳይሆን የህይወት ልምዶችንም ይጠይቃል። ዳኛ የሚሆን ሰው መስከን አለበት፣ ብዙ የህይወት ተሞክሮ ሊኖረው ይገባል። ያለበለዚያ በህግ ላይ አደጋ አለው" ብለዋል ላለፉት 40 አመታት ከዳኝነት እና ጥብቅና ሙያ ጋር ያሉ አንድ አስተያየት ሰጪ።

## የመንግስት ጣልቃገብነት

መንግስት የህግ የበላይነትን አላሳፈነም ተብሎ ከሚተችባቸው ነጥቦች አንዱ በህግ ሂደት ውስጥ ጣልቃ በመግባት የፍርድ ሂደቱን ሊያዛቡ የሚችሉ አስተያየቶችን አስቀድሞ በመገናኛ ብዙሃን ማሰራጨቱ ነው። በአንድ ወቅት ጅሃዳዊ ሃረካት እና አኬልዳማ የተባሉ ዶክመንተሪዎች በቴሌቪዥን ሲተላለፉ ብዙ ውግዘት ደርሶባቸው ነበር። የቀድሞው የኢፌዲሪ ፕሬዚዳንት ነጋሶ ጊዳዳ (ነፍስ ሄር) ይህንን አስመልክተው ለአንድ ጋዜጣ በሰጡት አስተያየት እንዲህ ብለው ነበር። ‹‹… በፍርድ ቤት የተያዙ ጉዳዮችን አስቀድሞ የሰዎችን ስም በማጥፋት ወይም ደግሞ ሰዎች የሚናገሩትን እየቀነጨቡና ፎርጅድ እየሰሩ በፊልም እያቀረቡ ነው የሚገኙት። ይህ ጉዳይ ለእኛ አዲስ አይደለም። ከዚህ ቀደም ‹በአኬልዳማ› አሁን ደግሞ በሙስሊም ማህበረሰብ ላይ ‹ጅሃዳዊ ሐረካት› በሚል ዶክመንተሪ ፊልም አቅርበዋል። ፍርድ ቤት ጅሀዳዊ ሀረካት በመገናኛ ብዙሃን እንዳይተላለፍ ቢያግድም ከህግ ውጪ የሆነው ኢቲቪ ህገ-መንግስቱ ላይ የተቀመጠውን ድንጋጌ ከቁብ ሳይቆጥር ለህዝብ አስተላልፏል። እንዲህ ሲያደርግ በኢ-ፍትሃዊ እየሰራና ማንም አይነካኝም በማለት መሆኑን እየተመለከትን ነው። ይህ የሚያሳየን ህግ አስፈጻሚው አካል እንደፈለገ እየሰራ መሆኑን ነው። እንደዚህ በሚሆንበት ጊዜ ሰዎች በፍትህ አካላት ላይ እምነት እንዲያጡ ያደርጋል›› ነበር ያሉት።

የአሁኑ የዶክተር ዐቢይ አስተዳደርም ይህንኑ ጥፋት እየደገመው ነው የሚሉ ሰዎች አልጠፉም። በሜቴክ እና በማዕከላዊ እስር ቤት ላይ የተሰሩ ዶክመንተሪዎች ከቀደሙት

**…አሁን ባለንበት የብሄር ፖለቲካ ጽንፍ መንግስትን እየዘወረ ያለው ገዢ መደብ ከቀደመው የአንድ ብሄር ስብስብ ወደሌላ አንድ ብሄር ስብስብ እንዲሸጋገር አድርጎታል ተብሎም ይተቻል። በዚህ ሳቢያም የኢህአዴግ መንግስት የህግ የበላይነትን ማስፈጸም ያልቻለው ማህበራዊ መሰረቱ በብሄር ቡድኖች ላይ የተጣለ በመሆኑ ነው…**

አኬልዳማ እና ጅሃዳዊ ሃረካት የሚለያቸው ርዕሰጉዳይ እንጂ ሁለቱም የፍትህ ስርዓቱ ላይ የተሰነዘሩ ጥቃቶች ናቸው ብለውም ይከራከራሉ።

## የህግ የበላይነት መቼ?

በአገራችን የህግ የበላይነት ተረጋግጧል ማለት የሚቻለው የህግ የበላይነት ላይ የተመሰረተ ህገ-መንግስት ሲኖር ነው። በመቀጠልም በአገሪቱ ውስጥ ሙሉ በሙሉ አንዱ ተቋም ሌላኛውን የሚቆጣጠርበት ማለትም በህግ አውጪው፣ ተርጓሚውና አስፈጻሚው መንግስታዊ አካላት መካከል አንዱ አንዱን እየተቆጣጠረ ተገቢ የስልጣን ክፍፍል ስርዓት መዘርጋት አለበት። አገሪቱ በህግ እንጂ በሰዎች ፍቃድ መመራት ስታቆም የህግ የበላይነት ተረጋገጠ ማለት ይቻላል። የፍትህ አካላቱ ነጻና ግልጽ ፤ ከመንግስት ጣልቃ ገብነት ውጪ መሆን ይጠበቅባቸዋል። ለምሳሌ አሜሪካ ነጻና ግልጽ የሆነ የፍትህ ስርዓት ስለዘረጋች የዘር መከፋፈልን አስቀርታለች። ባርነት ጠፍቶ አንድነታቸው እንዲያብብ ያደረገው የፍትህ ስርዓቱ ነጻ በመሆኑ ነው። እያንዳንዱ ዜጋ በፍትህ ስርዓቱ ላይ ካለው ፍጹም እምነት የተነሳ እንደመንግስት አካል ሳይሆን እንደ አንድ እምነት ተቋም የሚመለከቱት ሆኗል። በሀገራችን ያለው የፍትህ ሰርዓት በዚህ መልኩ ከተተረጎመ ለማንም ሳናጎበድድ በፍርድ ቤቶች ብቻ እምነት እንዲኖረን ያደርገናል። ይህ ሲሆን የህግ የበላይነት ተከበረ ማለት እንደሚቻል ብዙዎች ይስማሙበታል።

## ማነው የበላይ

ዛሬ በኢትዮጵያ መንግስት የህግ ማስከበር ሃላፊነቱን መወጣት ባለመቻሉ በሁሉም የሃገራችን ክፍል ግጭት በርትቷል። ይህ ግጭት መሰረት ያደረገው ዘርን መሆኑ ደግሞ ሰዎች የሚያስተዳድራቸው መንግስት እንደሌለ እንዲያስቡ እና ህግም እንደማያድናቸው እንዲሰጉ አድርጓቸዋል። ሃገሪቱ ውስጥ ባለው የጸጥታ ችግር መንግስት ህግን ለማስከበር የበላይ ሚናውን መውሰድ እንዳልቻለ ያሳብቃል። ይህም በተራው ፍርሃትን አንግሷል።

በሌላ በኩል እንደጌታቸው አሰፋ ወንጀል ፈጽመው በፌዴራል ደረጃ የሚፈለጉ ባለስልጣናትን ለፍርድ ማቅረብ ያልተቻለባት ሃገር ሆናለች ኢትዮጵያ። አንድ ክልል ከፌዴራል ነጻ በሆነ መስመር ህዝብን እየመራ እና ከመሃል ሃገር እያቆራረጠ ሲጓዝ ህግም በዚያኑ መጠን የመከበር ሃይሏ እየመነመነ ይሄዳል። በውጤቱም ፓርቲ እንጂ ህግ ሃገር እንዳይገዙ በር ይከፍታል። የበላዩ ማነው ለሚለው ጥያቄም መልስ ምጥ የሚሆነው ይሄኔ ነው። ህግ መንግስት ወይስ ቡድን !

## ምን ይደረግ

በኢትዮጵያ ለህግ የበላይነት አለመኖር ምክንያቶቹ በዚህ አንድ አመት የተከሰቱ ሳይሆኑ ላለፉት 28 አመታት ሲንከባለሉ የቆዩ ጥርቅሞች ናቸው። ችግሩ ይህ የተጣመመ መስመር መስተካከል አለመቻሉ ነው። የዴሞክራሲ ስርዓት ቁንጮ ይኸው የህግ የበላይነት ሆኖ ሳለ ነገር ግን ጉዳዩ ችላ መባሉ እየቆየ ህግን መናቅ እና ህግን መራቅ ውጤት ያመጣል።

የህግ የበላይነት በኢትዮጵያ እንዲሰፍን መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች በብዙ ምሁራን ተጠቅሰዋል። ለምሳሌም የሚከተሉት አራት መሰረታዊ ጉዳዮች እንደመፍትሔ ይታያሉ

አንደኛ በፍትህ አካላት ውስጥ የሚሰሩ ሰዎች ሁሉ በተለይ ፍርድ ቤት ውስጥ የሚሰሩና ለሕዝብ ፍትሕ የሚሰጡ አካላት ከወገንተኝነት የጸዱ መሆን አለባቸው። በሁለተኛ ደረጃ የፍትህ አከካት ሥራቸውን በሚሰሩበት ጊዜ ህግ አስፈጻሚው በነጻነታቸው ጣልቃ ሳይገባ በትክክል መወሰን እንዲችሉ መደረግ አለበት። ሶስተኛው ሕገ-መንግስቱ የያዛቸውን የመብት ድንጋጌዎች እና ሌሎች ከህግ የበላይነት ጋር የተያያዙ ሃሳቦችን ብዙሃኑ ማወቅ የሚችልበት አሰራር መዘርጋት ይገባዋል።

ህዝብ ካወቀ የራሱንም የሌሎችን መብት መጣስ መቃወም እንዲሁም ፍትህ በሚጣስበት ጊዜ ትክክል አይደለም ብሎ መከላከል ይችላል። አራተኛው መፍትሔ ደግሞ የተለያዩ ሲቪክ ማህበራት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ህዝቡ በህገ-መንግስቱ በተቀመጠው መሰረት ህግ እንዲተረጎም ማስገደድ አለባቸው። እነዚህ መካሄድ ከቻሉ ሲጣመም የኖረው የህግ የበላይነት ግንድ ወደአንድ አቅጣጫ ተመልሶ ከማንም በላይ ህግ ከፍ ያለባት ፣ ቡድንና ጀሌ የማይፈነጭባት፣ የዜጎቿ የስጋት ምንጭ ያልሆነች እና ስርዓት የሰፈነባትን ኢትዮጵያ መፍጠር ይቻላል የሚል እምነት አለ።

# የትምህርት ፖሊሲው ትውልድ ማነቃቂያ እንጂ፤ መግደያ መሆን የለበትም!

የዘንድሮው የ10ኛ እና የ12ኛ ክፍል አገር አቀፍ ፈተና በያዝነው ሳምንት በተሳካ ሁኔታ ተካሂዷል፡፡ የፈተናውን መጀመር ተከትሎ በተለይም ከሰኞ ማለዳ ጀምሮ የኢንተርኔት አገልግሎት እስከ ምሽት ድረስ መቋረጡ ፤ ከሲስተም ጋር በተያያዘ በባንክ አገልግሎት እንዲሁም ሌሎች ትልልቅ ተቋማት ላይ ግልፅ የሆነ ችግር መፍጠሩን ታዝበናል፡፡ በትምህርት ሚኒስቴር የአገር ዓቀፍ ፈተናዎች ድርጅት በሰሞነኛ መግለጫው፣ የፈተናው ህትመት ሂደት 24 ሰዓት ሙሉ በካሜራ ቁጥጥር ስር እንደነበር ቢናገርም፣ የኢንተርኔት አገልግሎት በዚህን ያህል ደረጃ እንዲቋረጥ መደረጉ ግርምትን ፈጥሯል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አሰራር ወደ ፊት ዕርምት ሊደረግበት እንደሚገባ በዚህ አጋጣሚ ለመጠቆም እንወዳለን፡፡

ዓመቱ ወደ መጠናቀቁ ከመቃረቡ አኳያ፣ በክረምቱ መርሃ ግብር ተማሪዎች ምን ለመስራት አስበዋል? ያላቸውን አነስተኛ የዕረፍት ጊዜ በመጠቀም ከራሳቸው አልፈው፣ ለሀገርና ለወገን በሚጠቀሙ የልማት፣ የበጎ አድራጎትና ትውልዱን በመልካም ስነ ምግባር በሚያንጽ  ተግባር ላይ በመሰማራት ፣ አመርቂ ውጤት ሊያስመዘግቡ የሚችሉበትን መንገድ ከወዲሁ መምረጥ ይኖርባቸዋል፡፡

በመንግስት ደረጃ ቀጣዩን የትምህርት ዘመን በተመለከተ በርካታ ስራዎች ይጠበቃሉ፡፡ በተለይም "ትውልድ ገዳይ" መሆኑ የተነገረለት የትምህርት ፖሊሲውን መቀየር ዋነኛ  የቤት ሥራው ይሆናል፡፡

በወ/ሮ ገነት ዘውዴ የትምህርት ሚኒስትርነት ዘመን ዕውን የሆነው "ትውልድ የማኮላሸት" ተግባር በየቤታችን፣ በየአካባቢያችን የአስራ አምስትና አስራ ስድስት ዓመት ታዳጊዎች "ጨርሰዋል" በሚል ሰበብ፤ ከ10ኛ ክፍል ከዕውቀት ገበታ የራቁበት መንገድ፣ በርግጥም ስርዓቱን የሚጋፈጡ፣ ለሀገርና ለሕዝብ፣ ለዴሞክራሲና ለሰላማዊ ትግል ራሳቸውን መስዋዕት የሚያደርጉ ወጣቶች በዚህች ሀገር ላይ በሚፈለገው መጠን እንዳይፈጠሩ ተደርጓል፡፡

ከቤት እስከ ት/ቤት፣ከገጠር እስከ ከተማ ኢትዮጵያዊነትን አሽቀንጥሮ በመጣል፣ ታዳጊዎች ከባህልና ታሪካቸው ጋር ሊኖራቸው የሚገባውን ቁርኝት በብሔርተኝነት መንፈስና በባዕዳን አላስፈላጊ ዘመናዊነት የተካው ኢህአዴግ፤ ትውልድ ይቅር የማይለው ስህተት እየተተገበረ ባለው የትምህርት ፖሊሲ አማካይነት ሰርቷል፡፡ በተጠቀሱት ዓመታት ውስጥም፣ ብዙኃኑ ወላጆች ያለ ዕድሜያቸውና ያለ በቂ ዕውቀት የሚሰናበቱ የ "ልጅ ጡረተኞች" እንዲረከቡ፣ ሕይወትንም በተስፋ መቁረጥ ውስጥ እንዲገፉ ተደርገዋል፡፡

ሀገር እንደ ሀገር በሁለት እግሯ የምትቆመው፣ በቂ የተማረ የሰው ኃይል ሲኖራት ብቻ ነው፡፡ ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ ስልጣን በያዙበት ማግስት፤ በገቡት ቃል መሰረት የትምህርት ስርዓት ፖሊሲውን በማሻሻል፣ ቀድሞ ወደነበረበት ይዘት እንደሚመልሱት ቃል ገብተው የነበረ ቢሆንም፤ በያዝነው ዓመት ተግባራዊ ሳይሆን ቀርቷል፡፡ በቀጣይ አዲስ ዓመት ግን ይህ ዕድል ሊያመልጠን አይገባም፡፡ ዳግመኛ ሌላ በቅጡ ያልታነፀ ትውልድ እንዲፈጠር አንሻምና፡፡ መንግስት በአዲሱ 2012 ዓ.ም ላይ ይህንን መርዘኛ የት/ት ፖሊሲ ነቅሎ ይጥልልናል ብለን ተስፋ እናደርጋለን፡፡

ከዚህ ባሻገር መንግስት በትምህርቱ ዘርፍ እየወሰደ ያላቸው አዳዲስ ዕርምጃዎች ይበል የሚያሰኙ ናቸው፡፡ የአዲስ አበባ መስተዳድር ት/ቤቶችን ከማደስ ባሻገር፣ በመንግስት ት/ቤቶች ላሉ ተማሪዎች የደንብ ልብስ ለማልበስና የት/ት ቁሳቁሶችን በነፃ ለማቅረብ ወሰኑን ሌሎች ክልሎችም ቢጋሩት ጠቀሜታው የጎላ ይሆናል፡፡


**ግዮን መጽሔት**
**ኢትዮ ሐበሻ ኅትመትና ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር**
**በየሳምንቱ ለኅትመት የምትበቃ መጽሔት**

**ማኔጂንግ ዳይሬክተር**
ፍቃዱ ማ/ወርቅ

**ዋና አዘጋጅ**
ሮቤል ምትኩ
አድራሻ፡- የካ ክ/ከተማ
ወረዳ 2 የቤት ቁጥር 475

**ከፍተኛ አዘጋጅ**
ብሩክ መኮንን
ፍቅርተ ተሾመ

**ተባባሪ ዘጋቢያችን**
ቶማስ አያሌው(ከአሜሪካ)

**አምደኞች**
ወንድሙ ነጋሽ(ኢ/ር ከለንደን)
ተረፈ ወርቁ
ሁሴን ከድር

**ክርኤቲቭ ዲዛይን**
ፍፁም ንጉሴ


**ጸሐፊ**
ሠላም ግርማ

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**
አራዳ ክ/ከ ወረዳ 09
የቤት ቁጥር 552/1
አምባቸው ህንፃ 2ተኛ
ፎቅ ቢሮ ቁ. 207
ፖስታ ቁ. 676 ኮድ 1029
ስልክ ፡ +251 911 22 76 61
+251 912 165606
+251 118 12 2333
ኢ-ሜይል፡
enqu2013@ gmail.com
Ghion2011meg@gmail.com
**Facebook**
Gihon-meg Fekadu
www. facebook.com/enqu2013


በዚህ መጽሔት ላይ የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ ማተሚያ ቤቱን አይመለከትም


**አታሚ**
ቴዎድሮስ ገብሩ ማተሚያ ቤት ፤ አራዳ ክፍለ ከተማ
ወረዳ 10 የቤ.ቁ. 066/ሀ
0911223335/ 0911420506

# አገራችን ውስጥ አስጊው ግጭት ምንድን ነው? ምክንያቶቹና መነሻዎቹስ?



## ፕሮፌሰር ሕዝቅያስ አሰፋ

**ፕሮፌሰር ሕዝቅያስ አሰፋ በአገራችን ከጊዜ ወደ ጊዜ አሳሳቢነቱ እየጨመረ የመጣውን ማንነትን መሠረት ያደረ ግጭትን በመፍታቱ ረገድ የሀገር ሽማግሌዎች እና የሃይማኖት መሪዎች ሊኖራቸው የሚችለው ሚና ምን መሆን እንዳለበት የሚጠቁም የግንዛቤ ማስጨባጫ ሐተታቸውን እንደሚከተለው አቅርበዋል፡፡**

### መጠቆሚያ

**አንደኛ፣** አሁን አገራችን ውስጥ በጣም አስጊ የሆነው ግጭት ምንድን ነው? ምክንያቶቹና መነሾዎቹስ ምንድን ናቸው?

**ሁለተኛ፤** ለእነዚህስ ግጭቶች መፍትሄ ሊጠቁሙ የሚችሉ አንዳንድ ሀሳቦች ምን ይመስላሉ?

**ሶስተኛ፤** አገራችን የረጅም ታሪክና የጥንታዊ ሃይማኖቶች ባለቤት እንዲሁም የጠቢባን ሽማግሌዎች አገር ስለሆነች፣ ይህንን አስጊ ግጭት ለመፍታት የእነዚህ ተዋንያን ሚና ምን መሆን ይገባዋል? የሚሉትን ሶስት ጥያቄዎች እመረምራለሁ፡፡

### ወደ ዋናው ጭብጥ ልዝለቅ

ለጽሑፌ መግቢያ ትሆን ዘንድ በአገራችን ያለንበትን ሁኔታ በጉልህ በምታንጸባርቅና የጠቢባንንም ሚና በምትጠቁም አንዲት ትንሽ ታሪክ ለመጀመር እወዳለሁ፡፡

በአንዲት ከተማ ውስጥ የሚኖሩ አዋቂ የሚባሉ አንድ አዛውንት ነበሩ፡፡ መቼም በየቦታው ተጠራጣሪና ተፈታታኝ ስለማይጠፋ አንድ ሰው እኚህ አዛውንት ምንኛ አዋቂ እንደሆኑ ሊፈታተናቸው ተነሳ፡፡

አንድ ቀን አዛውንቱ አደባባይ ላይ እንደተቀመጡ ይህ ሰው ብድግ ብሎ አንድ ጥያቄ ጠየቃቸው፡፡

“አባታችን፣ እንደሚያዩት በእጄ ውስጥ አንዲት ወፍ አለች፡፡ እንግዲህ ዝነኛ ጠቢብ እንደመሆንዎ ይቺ ወፍ በሕይወት መኖርዋን ወይም በድን/የሞተች መሆንዋን ሊነግሩን ይችላሉ?” ብሎ በመሳለቅ መልክ በድንገት ተጋፈጣቸው፡፡

እንግዲህ የተፈታታኙ ሰው ተንኮል፣በእጆቹ ሸፍኖ አንዲት ጫጩት ወፍ ይዟል፡፡ አዛውንቱ ወፍዋ የሞተች ነች ቢሉት እጁን ከፍቶ ሊለቃትና እንድትበር አድርጎ አዛውንቱ መሳሳታቸውን ሕዝቡ ፊት ሊያጋልጣቸው ይችላል፡፡ በሕይወት ያለች ነች ቢሉት ወፍዋ ጫጩት ስለሆነች እጆቹን ጫን አድርጎ ጨፍልቆ ሊገድላትና በድን መሆኗን ለተመልካቾች ሁሉ ሊያሳይና አዛውንቱ መሳሳታቸውን አስመስክሮ ሊረታቸው ይችላል፡፡

አዛውንቱ ጥቂት በጥያቄው ላይ ካሰላሰሉ በኋላ ፡ “አይ ልጄ፡ ለጥያቄህ የምሰጥህ መልስ፡ ወፍዋ በእጅህ ነች የሚል ብቻ ነው” ብለው የተፈታተናቸውን ሰው ረቱት ይባላል፡፡

ምን ማለታቸው ነው? አባባላቸው፣ “ወፍዋ ወይ ትኑር ወይ ትሙት የምትወስነው አንተ ብቻ ነህ፡፡ ስለዚህ ያቀረብክልኝ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የሚያገኘው በአንተ ብቻ እንጅ በሌላ ሰው አይደለም፡፡” ማለታቸው ነው፡፡

በተመሳሳይም አሁን በአገራችን ውስጥ ሰላም ልክ እንደ ወፍዋ በእጃችን ነው ያለችው፡ ፡ ሰላም እንድትኖር ወይ እንድትቀጭ፤ እንድትከስም ወይ እንድትለመልም ለማድረግ ችሎታው በእጃችን ነው፡፡ ያ ሰውዬ እጁን ከፈት አድርጎ ወፍዋ እንድትበር ሊያደርጋት እንደሚችለው ሁሉ፤ እኛም ልባችንንና አእምሯችንን ከፈት አድርገን ሰላም አገራችን ውስጥ እንድትበር/ እንድትሰፍን ለማድረግ እንችላለን፡፡

### ምን ማለቴ ነው?

በአገራችን ውስጥ የሚካሄዱት ግጭቶች ከሰማይ አልወረዱም፤ ወይ ከውጭ አልመ ጡም፡፡ የጠነሰስናቸው፣ የምናካሄዳቸው፣ የም ናፋፍማቸው እኛ ነን፡፡ ስለዚህ እኛ እስከፈ ጠርናቸው ድረስ እንዳልተፈጠሩ ለማድረግ ደግሞ ችሎታው አለን፡፡ ነገ በዚች አገር ሁላችንም ሰላም ይሁን ብለን ብንወስን ይህንን ለማድረግ ቁልፉ በእጃችን ነው፡ ፡ ይህ የሰላም መጥፋት የተፈጠረው አብረን ለመሥራት ባለመቻላችን፤ እያንዳንዳችን “እኔ ብቻ” በማለታችን፣ የራሳችንን ፍላጎት ብቻ በማስቀደማችን፤ እንደበሰለ ሰው ቁጭ ብለን ልባችንንና አእምራችንን ከፍተን የጋራ ችግራችንን ግልጥልጥ አድርገን ተወያይተን ለመነጋገርና መፍትሄ ለማግኘት ባለመፈለጋችን የፈጠርነው ችግር ነው፡፡ የእኛው መዘዝ ነው፡፡

እንግዲህ የዘላቂ ሰላም ግንባታ የመጀመሪያው ትምህርት፡ 1) ለሰላም መጥፋት ምክንያት የሆንነው እኛው ኢትዮጵያውያን፣ በተለይ ምሁራንና የፖለቲካ መሪዎች፣መሆናችንን ማወቅና መቀበል 2) ▶

▶የችግሮቹ ፈጣሪዎች እንደመሆናችን መጠን ችግሮቹንም ለማስወገድ ችሎታ እንዳለን መገንዘብ ነው። በሌላ አነጋገር፣ ፍላጎቱ ካለ ሰላምን በኢትዮጵያ ውስጥ ለማስፈን ይቻላል። እንግዲህ ችግሩም መፍትሔውም በራሳችን እንጂ በሌላ ሰው እጅ አለመሆኑን መገንዘብ ባንድ በኩል ታላቅ ኃላፊነትን ይፈጥርብናል፤ በሌላ በኩል ደግሞ፣ ታላቅ ኃይልን ያስታጥቀናል።

በብዙ አገሮች በተሳተፍኩባቸው የሰላም ሥራዎች እንደተገነዘብኩት፤ ግጭት በገነነበት ወይም ባፈጠጠበትና የግጭቱ ወገኖች በተወጠሩበት ሁኔታ ውስጥ ሰላምን ማምጣት ይቻላል ብሎ ማመንና በግጭቱ ውስጥ የሚፋለሙትን ወገኖች ማሳመን ዘላቂ ሰላምን ለመመሥረት ከሚያስፈልገው ሥራ ሀምሳ በመቶው ነው። ሰላም ይቻላል ብለን ካመንና ሌሎችንም ማሳመን ከቻልን ለሰላም ሥራ ትልቅ መሠረት ጣልን ማለት ነው። ሆኖም ይህ ሰላም ይቻላል የሚለው እምነት ብቻ በቂ አይደለም። የሚጠይቃቸውን ግዴታዎችና ሚናዎች በኋላ እተነትናለሁ።

አሁን ወደ አንደኛው ጥያቄአችን ልመለስና፤ በአገራችን ከምናያቸው ግጭቶች አንዱና እየተባባሰ የመጣው በብሔር ጎሳና ዘር ላይ የተመሠረተ ጥላቻና ግጭት መሆኑ አይካድም። እዚህ ላይ በጥልቅ ልናጤነውና ልናብሰለስለው የሚገባ አንድ ትልቅ ነጥብ አለ። ይኸውም፡ - ከሁሉ ግጭቶች በማንንት ላይ የተመሠረቱ ግጭቶች (በእንግሊዝኛ፣ አይደንቲቲ ቤዝድ ኮንፍሊክትስ የምንላቸው) ማለት፤ በዘር፣ በብሔር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በቋንቋ ላይ ለተመሠረቱ ግጭቶች መፍትሄ ለማግኘት በጣም አስቸጋሪና አደገኛ ነው።

ከሥራ ልምድ እንደተመለከትኩት፣ የኢኮኖሚ ግጭት ይፈታል፡ ፡ አሁንም ባይፈታ፣ ወደፊት ጊዜ ይፈታዋል። በአገራችን እንዳየነው በአፄ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ ፊውዳሊዝም ነበር። በኋላ ሶሻያሊዝም ተካው፣ አሁን ደግሞ ማኔጅድ ፍሪ ማርኬት ውስጥ ነው ያለነው። የኢኮኖሚው ሥርዓቶች ተለዋወጡ፤ ነገር ግን አገሪቱም ሆነች ሕብረተሰቡ አለ።

የፖለቲካም እንደዚሁ፤ በፊት የንጉሥ አገዛዝ፣ ከዚያ ኮሙኒዝም፣ አሁን ደግም ዲቨሎፕሜንታል ስቴት በሚባል ሥርዓት ውስጥ እንገኛለን። የፖለቲካው ሥርዓቶቹ ተለዋወጡ፤ ነገር ግን አገሪቱም ሆነች ሕብረተሰቡ አለ።

በሕዝብና ሕዝብ፣ በዘር፣ በቀለም፣ በሃይማኖት በሚያጣሉ ግጭቶች አንድ ጊዜ ሕዝቡ እርስ በርሱ ደም ከተቃባ ይህንን ለመቀልበስ፣ እንደገና ጉርብትናንና ትስስርን ለመፍጠር በጣም አስቸጋሪ ነው። እንደ እሳት እየተቀጣጠለ እንደ ወረርሽኝ ከሰው ወደ ሰው እየተላለፈ ነው የሚሄደው። የሚቀጥለው ትውልድም በዚህ ጥላቻ ውስጥ ይጠመዳል፤ ኅብረተሰቡ፤ አገሩ ይበተናል። ስለዚህ ግጭቱ እዚያ ከመድረሱ በፊት አስቀድሞ አግባብ ያለው ሂደትና መፍትሄ መፈለጉ በጣም ወሳኝ ነው።

በሩዋንዳ፣ በቡሩንዲ፣ በኬንያ፣ እንዲሁም በቀድሞዋ ዩጎዝላቪያ በጎሳ፣ በዘር ግጭቶች ከባድ ጉዳት በደረሰባቸው ወይም በወደሙ አገሮች ሠርቻለሁ። ለምሳሌ በዩጎዝላቪያ ውስጥ ኅብረተሰቡ ሲበተንና አገሪቷ ስትቆራረስ የነበረው ጥያቄ፡- ማን ነው የሰርብ ብሄር? ማን ነው የክሮአት ብሄር? ማን ነው የአልባንያ ብሔር? ወዘተ የሚል እና በዚያ መሠረት መከፋፈል ነበር። አገሪቷዋ ከተበተነች በኋላ ችግሩ እዚያ ላይ አልቆመም።

አሁን ተገንጥለው በተፈጠሩት አገሮች ውስጥ የተፈጠረው ጥያቄ “ማን ነው ንጹህ ዘር?” የሚል ሆኗል፣ ማለት፡ ማን ነው ንጹህ ክሮዌሺያዊ? አሁን የሰርብ ደም ያላቸው ክሮዌሺያዊያን ንጹህ አይደላችሁም ተብለው ክሮዌሺያ ውስጥ ቦታ የላችሁም እየተባሉ ነው። ወደ ሰርቢያ እንዳይሄዱ የክሮውሺያ ደም አለባቸው፡ ፡ ክሮውሺያ ውስጥ እንዳይቀመጡ ባዕድ ናችሁ ተባሉ። አሁን እነዚህ ከተለያዩ ጎሳዎች ጋብቻ የተወለዱ የት ነው የሚገቡት? ይህ የክሮሺያኖች ብቻ ችግር አይደለም። በተመሳሳይ አልባንያኖች፣ ስሎቪንያኖች ወዘተ ተመሳሳይ ችግር እያጋጠማቸው ነው።

እንግዲህ፣ ንጹህ ዘር የት ነው የሚገኘው? ሁላችንስ ብንሆን ከሌላ ቦታ ከሌላ ሕዝብ አይደለም ወይ የፈለስነው፣ የመነጨነው? ማን ሕዝብ ነው ከአዳምና ሔዋን ጊዜ ጀምሮ አንድ ቦታ የተቀመጠ? ንጹህ ዘር እንዴት ነው የሚለካው? እንዴት ነው የሚመዘነው? በዚች ምድር ውስጥ እንኳን ለብዙ ዘመን አብረው የኖሩ ሰዎች ቀርቶ ለጥቂት ጊዜ የተዋወቁ እንኳን ያልተጋቡ፣ ያልተቀላቀሉ ሕዝቦች አሉ ወይ? ስንት ትውልድ ተመልሰን ሄደን ነው ይህንን የዘር ጥራት የምናረጋግጠው? ማንነው ምስክሩ? ማንነው ዳኛው? ንጹኅ ዘር አይደላችሁም በማለት አይደለም ወይ የጀርመኑ ሂተለር እና የሩዋንዳው ሀቢያሪማናና ኢንተረሀምዌ ስንት ሚሊዮን ሰው ያወደሙት?

ነገሮች ወደዚህ ከመረማመዳቸው በፊት ይህንን በማንነት ላይ የተመሠረተ ወደ ልጅ ልጆቻችን የሚተላለፍ የጥላቻ መርዝ ማቆም አለብን። ነገሮች ስር ከሰደዱ በኋላ ዋይ ቢሉ እንደፈሰሰ ውሃ መመለሻ የለውም። እንደ ፖለቲካና የኢኮኖሚ ችግሮችና ግጭቶች በቀላሉ ሊታረሙ ወይም ሊያዙ አይችሉም።

## ስለዚህ እነዚህን ግጭቶች ለማቆም ወይም ለመቀነስና ለማብረድ ምን መደረግ አለበት?

በመጀመሪያ ደረጃ ከግጭት አያያዝና አፈታት ጥናት ከመነጨ አንድ ጽንሰ ሐሳብ ለመጀምር እፈልጋለሁ። ይህ ጽንሰ ሐሳብ፣ ግጭቶች ዘላቂ መፍትሄ የሚያገኙት የግጭቶቹ ሥር መነሻዎች የሆኑት ችግሮች ምን እንደሆኑ ተመርምረው ለእነዚያ ሥረ ምክንያቶች መፍትሄ ሲገኝ ብቻ ነው ይላል። ይህ ማለት፣ ግጭት ብዙ ጊዜ አታላይ ነው። ከላይ ከላይ ሲመለከቱትና ወደ ውስጥ ገብተው ሲመረምሩት የተለያየ ገጾችን ሊያመላክት ይችላል። ከላይ ለሚታየው ችግር ብቻ መፍትሄ ብንሰጥ ጊዜያዊ እንጂ ዘላቂ ሰላም አናገኝም። እንዲያውም ይህ መፍትሄ ብለን የምናመጣው ፈውስ ከመሆን ፋንታ ችግሮቹን ሊያባብሳቸው ይችላል ይላል።

በብሄሮች መካከል ለሚከሰቱ ግጭቶችና መተላለቆች ዋናው ሥረ ምክንያት በብሄሮች መካከል ካለው የዘር፣ የቋንቋ፣ የባሕልና የልምድ ልዩነት የተነሳ የሚመጣው አለመጣጣምና አለመቻቻል፣ ሲከርም ጥላቻ ነው ብለው የሚያስቡ ብዙ ሰዎች አሉ። እንግዲህ ምክንያቱ ይህ ከሆነ፤ ዘላቂ መፍትሄው የሚጣሉትን ብሄሮች መለያየት፣ ማለት፤ እያንዳንዱ ብሔር የራሱን ክልል፣ የራሱን ቦታ፤ የራሱን ቀጠና ቢይዝ በብሔሮቹ መካከል ያለው ግጭት ሊቆምና ሰላም ሊመሠረት ይችላል ወደሚል አስተሳሰብ ሊመራን ይችላል። ግን ይህ መፍትሄ ይሆናል የሚባለው መልስ እራሱ ሌሎችን ግጭቶችን ሊፈጥር፣ እንዲያውም ያለውንም ግጭት ሊያባብሰው ይችላል፡ ፡ እያንዳንዱ የራሱ ቀጠና ይኑረው ስንል እንዴት ነው ድንበሩን የምንከልለው? የጋራ ሐብቶች እንደ ውሃ፣ የግጦሽ መሬት፣ የደን ሐብትና ማዕድን ለማን ይሰጣሉ ወይም እንዴት ይከፋፈላሉ? ሲከፈሉስ ለሁለቱ በቂ ይሆናሉ ወይ? ከሁለቱ ብሄሮች ጋብቻ የተወለዱት ልጆች የት ይሆናሉ? ከዚህ በላይ ስለ ዩጎዝላቪያ ባብራራሁት መሠረት የዘረኞች ልብወለድ ካልሆነ በስተቀር ያልተነካካ ንጹኅ ዘር የሚባል እንደሌለ፣ ሊኖርም እንደማይችል አመልክተን ነበር። እንግዲህ ድንበር ይከለል ሲባል ብዙ ከባድ ጥያቄዎችን ያስነሳል። እነዚህን የብዙ ዘር ትውልዶች እራሳቸው ሳይፈልጉ እዚህ ትሆናላችሁ ወይም አትሆኑም የሚለውን ጥያቄ የሚወስነው ማን ነው? እዚህ መሆን እንፈልጋለን ብለው ቢወስኑስ

ቀሪውን በገጽ 24 ይመልከቱ

**...የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሙሉ የዜግነት መብቱ መከበር፣ መጠበቅ አለበት፡፡ ይኽም ካልሆነ ብዙ ጊዜ ሳይወሰድ፣ ካለ ብዙ መሰናከል፣ መጉላላትና ወጭ፤ ባስተማማኝ ሁኔታ ሙሉ የዜግነት መብቱን የሚያስከብርበት ሂደት እና መዋቅር መኖር አለበት...**

# ቅዱስ ሲኖዶስ - በሀገር ሰላም፣ በቤተክርስቲያን፣ በግብረ ሶዶማዊያን ላይ ውሳኔ ሰጠ



## የጠ/ሚ/ሩ መልስ ይጠበቃል

ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ፣ ብፁዕ አቡነ ያሬድ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ኾነው በምልአተ ጉባኤ ተመረጡ!

በሕጉ መሠረት፣ ቅዱስ ፓትርያርኩ፣ የብፁዕ ዋና ጸሐፊውን መሠየም በደብዳቤ ይገልጹላቸዋል፤ የተመረጡትን ብፁዕ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ በፊርማቸው ይሾሟቸዋል፤ ብፁዕ ዋና ጸሐፊ አቡነ ዮሴፍ፣ የሕፃናት እና ቤተሰብ ጉዳይ ድርጅትንም በቦርድ ሰብሳቢነት ይመራሉ፤ ተሰናባቾቹ፥ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ እና ዋና ጸሐፊ ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ፣ በምልአተ ጉባኤው አባላት ሽልማትና ከፍተኛ ምስጋና ተሸኙ! ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ፣ ሀገረ ስብከታቸውን እንደያዙ፣ የምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም ሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢነትና የገዳሙ የበላይ ጠባቂነት ተመደቡ፤

ምልአተ ጉባኤው በተ.ቁ(22) በያዘው በዚኹ አጀንዳ፣ ዓርብ፣ ግንቦት 30 ቀን ባካሔደው ምርጫ፣ የአርሲ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና የጠቅላይ ቤተ ክህነት የሰበካ ጉባኤ ማዳራጃ መምሪያ የበላይ ሓላፊ ብፁዕ አቡነ ያሬድን፣ በከፍተኛ ድምፅ በመምረጥ፣ ለቀጣይ ሦስት ዓመታት፣ የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤትን በጠቅላይ ሥራ አስኪያጅነት እንዲመሩ መርጧቸዋል፡፡

በሕገ ቤተ ክርስቲያን የጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ አመራረጥና ሹመት አንቀጽ 43 መሠረት፣ ምልአተ ጉባኤው የሠየመው በብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ ሰብሳቢነት በሚመራው ሰባት አባላት ያሉት አስመራጭ ኮሚቴ፣ ሦስት ዕጩዎችን ከአባላቱ መካከል የጠቆመ ሲኾን፣ በምሥጢራዊ የድምፅ አሰጣጥ በተከናወነው ምርጫ፣ ብፁዕ አቡነ ያሬድ፣ ድምፅ ከሰጡት 53 አባላት 38 ከፍተኛ ድምፅ በማግኘት ተመርጠዋል፡፡

ከብፁዕነታቸው ጋራ ለውድድር የቀረቡት፣ የባሕር ዳር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ አብርሃም 12 ድምፅ፣ የከፋ ሸካ ቤንች ማጂ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ሕዝቅኤል 3 የምልአተ ጉባኤውን አባላት ድምፅ በማግኘት 2ኛ እና 3ኛ ኾነዋል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ፣ በሕገ ቤተ ክርስቲያኑ አንቀጽ 24 መሠረት፣ ለቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊነት በተደረገው ውድድር፣ የምሥራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ፣ 21 ከፍተኛ ድምፅ በማግኘት፣ ለቀጣይ ሦስት ዓመታት የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ ኾነው እንዲያገለግሉ ምልአተ ጉባኤው መርጧቸዋል፡፡

ከብፁዕነታቸው ጋራ የምሥራቅ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ እና ሆሩ ጉድሩ አህጉረ ስብከት ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ናትናኤል እንዲሁም የምዕራብ ሐረርጌ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ እንጦንስ የተወዳደሩ ሲኾን፣ 17 እና 14 ድምፅ እንደ ቅደም ተከተላቸው በማግኘት 2ኛ እና 3ኛ ኾነዋል፡፡

በድንጋጌው አንቀጽ 24 ንኡስ አንቀጽ 2 መሠረት፣ በቅዱስ ሲኖዶስ ምልአተ ጉባኤ የተመረጡት ብፁዕ ዋና ጸሐፊ መሠየም፣ በቅዱስ ፓትርያርኩ በተጻፈ ደብዳቤ ይገለጽላቸዋል፤ በአንቀጽ 43 ንኡስ አንቀጽ 1 መሠረት፣ በምልአተ ጉባኤው የተመረጡት ብፁዕ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ደግሞ በቅዱስ ፓትርያርኩ በተፈረመ ደብዳቤ ይሾማሉ፡፡

ከግንቦት 2008 ዓ.ም. ጀምሮ ላለፉት ሦስት ዓመታት በጠቅላይ ሥራ አስኪያጅነት ያገለገሉት የደቡብ ትግራይ - ማይጨው እና ደቡባዊ ምሥራቅ ትግራይ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ቅርስ ጥበቃ ቤተ መጻሕፍት ወመዘክር መምሪያ የበላይ ሓላፊ ብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ እና በዋና ጸሐፊነት ያገለገሉት የደቡብ ምዕራብ ሸዋ-ወሊሶ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ፣ ትልቅ የሥራ ፍሬ ማስመዝገባቸውን ምልአተ ጉባኤው ገልጾ፣ በከፍተኛ ደረጃ አመስግኗቸዋል፤ መላው የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት አዋጥተው የገዙትን የብር የአንገት አይከንና የእጅ መስቀል ሽልማትም፣ በርእሰ መንበሩ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ አቡነ ማትያስ አማካይነት በሽልማት ተበርክቶላቸው በድምቀት ተሸኝተዋል፡፡

ምልአተ ጉባኤው፣ የሕፃናትና ቤተሰብ ጉዳይ ድርጅትን ቀጣይ ዕድገት አስመልክቶ በሥራ አስኪያጁ የቀረበውን ጥናት በተወያየበት አጀንዳ ተ.ቁ(17)፣ ተመራጩ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ፣ የድርጅቱ የቦርድ ሰብሳቢ እንዲኾን የወሰነ በመኾኑ፣ የተመረጡት ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ፣ ሓላፊነቱን ደርበው የሚይዙ ይኾናሉ፡፡

በራሳቸው ጥያቄ የቦርድ ሰብሳቢነቱን ያስረከቡት ብፁዕ ዋና ሳዊሮስ ደግሞ፣ ሀገረ ስብከታቸውን እንደያዙ ባለፈው ግንቦት 27 በሞተ ዕረፍት በተለዩን ብፁዕ አቡነ ገሪማ ምትክ፣ የምስካየ ኅዙናን ገዳም የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ እና የገዳሙ የበላይ ጠባቂ እንዲኾኑ ተመድበዋል፡፡

### ስለ ግብረሰዶም

ለሰው ፍጹም ተፈጥሯዊ ያልኾነውን የግብረ ሰዶም ኀጢአት፣ ነውርና ወንጀል ማውገዝ፣ ቤተሰብን የማዳንና ትውልድን የማስቀጠል ጉዳይ እንደኾነ ለቅዱስ ሲኖዶስ ምልአተ ጉባኤ ያስረዱት የፋሚሊ ዎች ኢንተርናሽናል ፕሬዝዳንት ሻሮን ስሌተር፣ ቤተ ክርስቲያን ችግሩን የመከላከል አቋሟን በማጠናከር ሰለባዎችን ነጥቆ የማዳን ሥራም እንድትሠራ ተማፀኑ፡፡ ▶

በቱሪዝም ሽፋን በተደራጀ መንገድ ወደ ኢትዮጵያ በመግባት ድርጊቱን ለማስፋፋት ያቀዱ ግብረ ሰዶማውያንን ቅዱስ ሲኖዶስ ካወገዘበት ስብሰባ በኂላ፣ ከብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ አቡነ ማትያስ ጋራ ምሽቱ ላይ ተገናኝተው የተወያዩት ፕሬዝዳንቷ፣ በማግሥቱ ጠዋት ከሦስት የሥራ ባልደረቦቻቸው ጋራ በምልአተ ጉባኤው ፊት ቀርበው፣ ለተወሰደው ጠንካራ አቋም የድርጅታቸውን ድጋፍና አድናቆት ገልጸዋል፡፡

መቀመጫውን አሜሪካ ያደረገው የበጎ ፈቃድ ድርጅታቸው፥ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት፣ በራሱ በአሜሪካ መንግሥትና በየአህጉሩ በሚንቀሳቀሱ አካላት ላይ፣ ቤተሰብ ተኮር በኾኑ ጉዳዮች፦ ወላጆች ልጆችን በመልካም የሚያሳድጉበትን፣ ልጆችም በትምህርት ተቋማት ከሞራል እና ሠናይ ምግባር ተፃራሪዎች ተጋላጭነት የሚጠበቁበትን፣ በዋናነትም በሚመለከታቸው አካላት፣ በጎ ፖሊሲዎች የሚታነፁበትን አዎንታዊ ተጽዕኖ በመፍጠር እየሠራ እንደኾነ ጠቅሰዋል፡፡

በአንጻሩ፣ በሰብአዊ ረድኤትና ልማት ስም ወደ አፍሪቃ ከሚመጡ ድርጅቶች ጥቂት የማይባሉት፣ ለመንግሥታቱ በይፋ ከሚያቀርቡት ማኒፌስቶ በተቃራኒ፣ ግብረ ሰዶምን የመሳሰሉ ነውረኛ ተግባራትን፣ በወጣቶች ዖታዊ መብቶችና ነፃነቶች ጥበቃ ሽፋን እያስፋፉ እንደሚገኙ አስረድተዋል፡፡

የሩካቤ ሥጋ ነፃነት እና ጤናማ ሥነ ተዋልዶ የሚሉት ዋነኛ እንደኾኑ አንሥተዋል፡፡ በሰዶማዊ ድርጊት፥ ወጣት ወንዶችን፥ ለኤች.አይ.ቪ. አትጋለጡም፤ ከበሽታውም ነፃ ትኾናላችኁ፤ በማለት፣ ወጣት ሴቶችን ደግሞ፣ እርግዝና እና ውርጃ አያስጋችኹም፤ እያሉ እየገፋፉ ለልቅነት እንደሚያበረታቷቸው አብራርተዋል፤ “በፊንጢጣ የሚደረግ ግንኙነት ከተፈጥሯዊው 17 እጥፍ ለኤች.አይ.ቪ. ተጋላጭ እንደሚያደርግ በጥናት ተረጋግጧል፤” ብለዋል ፕሬዝዳንቷ፡፡ በማደጎ ስም የወሰዷቸውን ሕፃናት፣ ተፈጥሯዊ የፆታ ማንነትና ሚና እያቃወሱ መልሰው ወደ ትውልድ አገራቸው በማምጣት ብዙዎችን በአስተሳሰቡና በድርጊቱ እየጎዱ እንዳሉ፤ ኢትዮጵያም ከዚሁ ስጋት ነፃ እንዳልኾነች አስታውቀዋል፡፡

በበጎ አድራጎት ሽፋን ድርጊቱን ያስፋፋሉ ካሏቸው ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ውስጥ፣ መቀመጫውን ናይሮቢ ያደረገውን IPPFAR የተባለ እንግሊዛዊ ድርጅት በአብነት ጠቅሰዋል፡፡ በሰብአዊ መብቶችና ረድኤት ስም የሚያገኛቸውን በተለይ ከ25 ዓመት በታች የኾኑ ወጣቶች፣ በሩካቤ ሥጋና በሥነ ተዋልዶ ጤና መብቶች(sexual and reproductive health and rights - access to SRHR services) ምንም ዓይነት ገደብና ክልከላ ሊደረግ እንዳይገባ አድርጎ እየሰበከ እንደሚያበላሻቸው፥ Rights, Sexuality and Living with HIV/AIDS የተሰኘ ኅትመቱን በአስረጅነት ለምልአተ ጉባኤ እያሳዩ አስረድተዋል፡፡

ወደ ኢትዮጵያ ቅዱሳት መካናት ለመምጣት እየፎከሩ ያሉት የተደራጁ ግብረ ሰዶማውያን፣ የቅዱስ ሲኖዶስን ውግዘትና ሌሎች አካላትን ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ተከትሎ፣ ልዩ ልዩ የማዘናጊያ መልእክቶችን እያስተላለፉ እንዳሉ ቢገለጽም፣ አጀንዳቸውን በየጊዜው እየቀያየሩ ያለማስታወቂያም ሊመጡ ስለሚችሉ፣ ፕሬዝዳንቷ እንዳሉት ንቃትና ጥንቃቄ ከማድረግ መቦዘን የለብንም፡፡ የርክበ ካህናት ምልአተ ጉባኤ በውግዘቱ፦ ተቃውሞውን ገልጾ ለመንግሥት ደብዳቤ እንዲጻፍ፣ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት በየአህጉረ ስብከታቸው ጠንክረው እንዲያስተምሩ፣ ቤተሰብ ራሱንና ልጆቹን እንዲከታተልና እንዲጠብቅ፣ በቅዱሳት መካናት ትብብር እንዳይደረግላቸውና በንቃት እንዲጠበቁ መወሰኑ ይታወሳል፡፡

የድርጁ ግብረ ሰዶማውያኑን የእንመጣለን ማስታወቂያ በግንባር ቀደምነት ከተቃወሙት አንዱ የኾኑት፣ የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ጠቅላይ ጸሐፊ ሊቀ ትጉሃን ታጋይ ታደለ፣ የፋሚሊ. ዎች ኢንተርናሽናል ፕሬዝዳንትና የሥራ ባልደረቦቻቸው፣ ከብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ጋራ እንዲገናኙና በቅዱስ ሲኖዶስ ምልአተ ጉባኤ ላይ ቀርበው ማስረዳት እንዲችሉ ኹኔታዎችን በማመቻቸት የበኩላቸውን ሚና ተጫውተዋል፡፡

## ቅዱስ ሲኖዶስ፡ ለሰላም እና ዕርቅ ዐቢይ ኮሚቴው ከ6 ሚሊዮን ብር በላይ በጀት አጸደቀ፤

ግጭቶችና ጥቃቶች ያስከተሏቸውን ቅራኔዎች በማስወገድ ዕርቀ ሰላምን ለማስፈን፣ አንድነትን ለማጠናከርና ተጎጂዎችን ለመካስ በሚደረገው አገራዊ ጥረት የቤተ ክርስቲያንን ሚና እንዲወጣ በቅዱስ ሲኖዶስ ምልአተ ጉባኤ ለተቋቋመው የሰላምና ዕርቅ ዐቢይ ኮሚቴ፣ ከ6 ሚሊዮን ብር በላይ በጀት ጸደቀ፡፡

በጅማ እና ሰሜን ጎንደር አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ እስጢፋኖስ ሰብሳቢነት የሚመራው ዐቢይ ኮሚቴ፣ የተግባር ዕቅዱንና አፈጻጸሙን በሚያስፈልገው ወጪ ደግፎ ለምልአተ ጉባኤው ያቀረበ ሲኾን፣ የ6.7 ሚሊዮን ብር በጀት ጸድቆለታል፡፡

ጠቅላይ ጽ/ቤቱ ባለፈው ታኅሣሥ እና የካቲት በኹለት ዙሮች ከአካሔደው አገር አቀፍ የሰላምና ስብከተ ወንጌል ስምሪት ተመድቦ ከነበረው ብር 8 ሚሊዮን አጠቃላይ በጀት ቀሪውን ዐቢይ ኮሚቴው ለሥራው እንዲጠቀምበት ቅዱስ ሲኖዶሱ ወስኗል፡፡

የሰላምና ዕርቅ ዐቢይ ኮሚቴው፣ የአህጉረ ስብከት ንኡሳን ኮሚቴዎች ይኖሩታል፤ ግጭቶችና ጥቃቶች እንዳይከሠቱ ትምህርትና ሥልጠና ይሰጣል፤ ሲያጋጥሙ በቦታው በመገኘት ዐይነቱንና መጠኑን ለይቶ በየደረጃው ያቀርባል፤ እንዳይደገም ዘላቂ ዋስትናና አስተማማኝ ሰላም ለማስፈን፣ በይቅርታ ለማለፍና ዕርቅ ለማውረድ ከሚመለከታቸው ጋራ ይሠራል፤ የቤተ ክርስቲያንን የፍቅርና አንድነት አስተምህሮ ያስተላልፋል፡፡

## ለጠ/ሚኒስትሩ ደብዳቤ ተፃፈ

ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ በሰላምና ዕርቅ የቤተ ክርስቲያን አገራዊ ሚና ላይ ለምልአተ ጉባኤው ያስተላለፉትን መልእክት ተቀብሎና በአጀንዳውም መሠረት፣ ቅዱስ ሲኖዶሱ ዐቢይ ኮሚቴውን አቋቁሟል፤ በተጨማሪም፣ በዚሁ የርክበ ካህናት መደበኛ ስብሰባው፣ መንግሥት ከ1983 ዓ.ም. ጀምሮ ቤተ ክርስቲያን ለደረሰባት ጥቃት ዕውቅና እና የደኅንነት ዋስትና እንዲሰጥ ከሚመለከታቸው አካላት ጋራ በጉዳዩ ላይ ፊት ለፊት ለመነጋገር፣ በፓትርያርኩ አማካይነት ጠቅላይ ሚኒስትሩን በደብዳቤ ቢጠይቅም፣ ምልአተ ጉባኤው እስከሚጠናቀቅበት ድረስ ምላሽ ባለመገኘቱ፣ ውይይቱ በዐቢይ ኮሚቴው አማካይነት በሌላ ደብዳቤ ተጠይቆ እንደሚደረግ ተመልክቷል፡፡

ለውይይቱ ተዘጋጅቶ በነበረው የዐቢይ ኮሚቴው ሰነድ፣ ልዩ ትኩረት ያሻቸዋል የተባሉና በከፍተኛ ጫና ሥር ያሉ ዐሥር አህጉረ ስብከት ተለይተዋል፡፡ ጅማ፣ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ምዕራብ እና ምሥራቅ ሐረርጌ፡ - ምእመናን በከፍተኛ ጫና ሥር የወደቁባቸውና መንግሥት በፍትሕና ጸጥታ መዋቅሩ ሕጋዊ ዋስትና እንዲሰጥ በአስቸኳይ የሚጠየቅባቸው አህጉረ ስብከት ናቸው፡፡ የደቡብ ወሎ፣ አርሲ፣ ድሬዳዋ፣ ጅግጅጋ፣ ባሌ እና ሰሜን ምዕራብ ሸዋ - ሰላሌ አህጉረ ስብከትም፣ ከጥበቃ ዋስትናው በተጨማሪ፣ ጥቃት ለደረሰባቸው አካላት ካሳ እንዲከፈል፣እንዲሁም ልዩ የማጣራት ርምጃ ተወስዶ ጥቃት አድራሾችን በሕግ ለመጠየቅ ይፋዊ ጥያቄ የሚቀርብባቸው እንደኾኑ ተጠቁሟል፡፡

## ከግንቦት 13 - ሰኔ 3 2011 ሲካሄድ የቆየው የሲኖዶሱ መግለጫ

ለ18 ቀናት ሲያካሒድ የሰነበተውን የርክበ ካህናት ምልአተ ጉባኤ መደበኛ ስብሰባ፣ ሰኞ፣ ሰኔ 3 ቀን 2011 ዓ.ም. ሲያጠናቅቅ፣ ባወጣው ባለ15 ነጥቦች መግለጫ፣ ቤተ ክርስቲያን ከምትሰጠው መንፈሳዊ አገልግሎት በተጨማሪ በማኅበራዊ ዘርፍ ለአገር ዕድገትና ለሕዝቡ የኑሮ መሻሻል፣ በተለይም ለሰላምና አንድነት በመቆም ድርሻዋን እንድትወጣ መወሰኑን ቅዱስ ሲኖዶሱ አስታውቋል፡፡

አገራችን ከጥንቱ ከመሠረቱ ጀምሮ፣ “የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው” የሚለውን መርሕ ተከትላ፣ ሰላሟን፣ ፍቅሯንና አንድነቷን ጠብቃ የውጭ ባዕዳን ወራሪዎችን በመመከት ክብርዋንና ልዕልናዋን ለረጅም ዘመናት ጠብቃና አስጠብቃ እንደኖረች አስታውሶ፣ በአኹኑ ዘመን የሚታዩትን ያልተለመዱ ባሕርያት፣ ሕዝቦችዋ በሰከነ መንፈስ ቆም ብለው በመምከርና በመወያየት ወደ ጥንተ ሰላምዋ እንድትመለስ የማድረግ ሓላፊነት እንዳለባቸው አስገንዝቧል፡፡

ቤተ ክርስቲያን ለምትፈጽመው ማኅበራዊና ልማታዊ ተግባር በጎ ፈቃድ በማያሳዩ ባለሥልጣናት፣ በተለያዩ ዞኖችና ወረዳዎች የቤተ ክርስቲያንንና የተከታዮቿ ምእመናንን መብትና ደኅንነት ለአደጋ እያጋለጡና እየጎዱ እንደሚገኙ፣ ቅዱስ ሲኖዶሱ በመግለጫው አመልክቷል፡፡ ከየአህጉረ ስብከቱ በቀረበለት ሪፖርት መሠረት፡-

ቀሪውን በገጽ 23 ይመልከቱ

## አንደበት



"በግጭቶች የአመራሮች እጅ አለበት ወይ?" የሚል ግምገማ አድርገናል፡፡ በግምገማውም በግጭቶች ተሳትፈው የተገኙ አመራሮች ካሉ አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ እንዲወስድባቸው ውሳኔ ላይ ደርሰናል፡፡ በዚህ መሰረትም ከ100 በላይ በሆኑት የቀበሌ፣ የወረዳና የዞን አመራሮች አስተዳደራዊ እርምጃ ተወስዶባቸዋል፡፡ ሌላው የህግ የበላይነትን ከማስከበር አኳያ በዞን ደረጃ ከፖሊስ ሁለት መርማሪ ቡድኖች አዋቅረናል፡፡ እነሱም ተንቀሳቅሰው እየሰሩ ነው፡፡ በአጠቃላይ በዚህ እንቅስቃሴ ወደ 267 ተጠርጣሪዎች ተይዘዋል፡፡ 89 ተፈርዶባቸዋል፡ ፡ ቀጠሮ ላይ ያሉ አሉ፡፡ 25ቱ ጉዳያቸው በፌደራል አቃቤ ህግ እየታየ ነው፣ በጥቅሉ አሁን በዞኑ አንፃራዊ ሰላም አለ ብሎ መናገር ይቻላል፡፡"

**አቶ አበራ ቡኖ / የምዕራብ ጉጂ ዞን ዋና አስተዳዳሪ/**
**አዲስ ዘመን ጋዜጣ ሰኔ 5 ቀን 2011 ዓ.ም**



"በ1997 ዓ.ም ምርጫ እንኳ፣ የኛ ተወዳዳሪዎች ከ90 በመቶ በላይ ወጣቶች ነበሩ፡፡ድርጅታችን ከ20 ዓመት በላይ ተሸክሞ፣ እዚህ ያደረሰው ወጣቱ ነው፡፡ ቁሮው እኮ ነው ስለኛ የታገለውና ከእስር ያስፈታን፡ ፡ ከዚህ በላይ ቦታ ከፈለገ እኛ የምንከለክለው አይሆንም፡፡ በአገርም ደረጃ ለውጥ ያመጣው ወጣቱ ሀይል ነው፡፡ ከዚህ ወጣት ጋር መጣላት የሚፈልግ የፖለቲካ ድርጅት እብድ ነው፡፡ ይልቁንስ "እነ እገሌን እንፈልጋለን፣ እነ እገሌን አንፈልግም" የሚሉበት ደረጃ በመድረሳቸው ተፅዕኖ ሊመጣ የሚችለው ከእነሱ እንጂ ከእኛ አይሆንም፡፡"

**ፕ/ር መረራ ጉዲና /የኦሮሞ ህዝቦች ኮንግረስ መሪ/**
**አዲስ ዘመን ጋዜጣ ሰኔ 1 ቀን 2011 ዓ.ም**

## አባባል

☛"ማንኛውም ቋንቋ እንዳይጠፋ መጠበቅ አለብን፣ ምክንያቱም ቋንቋዎች የብሔሮች የዘር ሐረግ መዛግብት ናቸውና፡፡"
*ሳሙኤል ጆንሰን*

☛ "ከሴቶች ዕምባ ቀድሞ የሚደርቅ ምንም ነገር የለም፡፡"
*ጆን ዌብስተር*

☛ "ማንም ሰው የሌለውን ነገር አያጣም፡፡"
*አይዛክ ዋልተን*

☛ "ካንተ አስበልጦ ራሱን በመውደዱ ልትታዘበው አይገባም፡፡"
*ፍራንሲስ ባንኮን*

☛ "ስለ ራሱ መጻሕፍት ብቻ የሚናገር ደራሲና ስለ ልጇ ብቻ የምታወራ እናት አንድ ናቸው፡፡"
*ቤንጃሚን ዲዝራኤል*

## ለጠቅላላ አውቀት

➞የደም ስራችን ተገጣጥመው ከተዘረጉ ሁለት ጊዜ ምድርን ይዞራል፡፡ ጡንቻዎቻችን የሚያፈልቁት ሙቀት በአንድ ሰዓት ውስጥ ሁለት ሊትር ውሃ ማፍላት ይችላል፡፡

➞ አይናችንን በአንድ ቅፅበት ስናርገበግብ ለ0.3 ያህል ሴኮንዶች እንጨፍናለን፡፡

➞ልብ በሰዓት 7.500 ሊትር ደም ይረጫል፡፡

➞ወደ ውስጥ ከምንስበው አየር ውስጥ ጭንቅላትታችን 20 ፐርሰንቱን (ተኝተን እንኳ ቢሆን) ይጠቀምበታል፡፡

➞ ስናዛጋ ሰውነታችን ብዙ ኦክስጂን እንዳስፈለገው ይጠቁማል፡፡
በሀይል ስንተነፍስ በተለይ ስናቃስት፣ የትንፋሻችን ፍጥነት በሰዓት 160 ኪሎ ሜትር ነው፡፡
ሕፃናት ከተወለዱበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 3 - 6 ሳምንት ድረስ ሲያለቅሱ እንባ አያመነጩም፡፡



"ዝቅ ሲል ግዴለሽነት፣ ከፍ ሲል ደግሞ ሆነ ተብሎ የሚሰራ አፍራሽና ከሙያው ስነ ምግባር ያፈነገጠ አዘጋገብ አለ፡፡ ለግለሰቦች፣ ለማሕበረሰብና ለብሔረሰቦች ስሜት ሚዲያው በጣም መጠንቀቅ አለበት፡፡ ከጠቀስኩልህ የእንግሊዝ ተሞክሮ በመውሰድ የአሰራርና የመመሪያ ስርዓት ቢኖር ጥሩ ነው፡፡ የሚታወቁና ስሜት የሚጎዱ፣ የሚያስቆጡ ወይም በአሉታዊ መልኩ የሚቀሰቅሱ ቃላት ባለሙያው ተሰባስቦ ለይቶ ካወጣቸው በኋላ ማገድ አለበት፡፡"

**ጋዜጠኛ ስርጉት ያደታ /የኢትዮጵያ ዲያስፖራ ፈንድ የቦርድ አባል/**
**ጉለሌ ፖስት መጽሔት ሰኔ 2011 ዓ.ም**



"የመለስ ፎቶ ሲቀደድ ክህደት ነው ለኔ፡፡ የኔ መከራከሪያ ለመለስ እውቅና ላለመስጠት ፎቶውን የቀደዱ አሉ፣ ወይስ የሉም? መልሱ አሉ የሚል ነው፡፡ እነዚያ ሰዎች ታዲያ ክደውታል፣ መክዳታቸው ትክክል ነው? ለሀገር ምንም አልሰሩም ከተባለ ሊያከራክር ይችላል፣. መቀደዱ ክህደት ነው.... ማነው የቀደደው ?ማነው የከዳው?"

**አቶ ሽፈራው ተክለሃይማኖት /የመቐለ እግር ኳስ ክለብ ዋና ስራ አስኪያጅ/ህትሪክ ጋዜጣ ሰኔ 5 ቀን 2011 ዓ.ም**



"በጎ ስራቸውን በማበረታት ሀገራዊ ለውጥ ማምጣት ይቻላል ብዬ አስባለሁ፡፡ ራሳቸውን ችለውና ፍፁም ገለልተኛ ሆነው እንዲቋቋሙ ማድረግና ማበረታታት ከተቻለ ሀገርን መለወጥ ይቻላል፡፡ ሀገርን የሚቀይረው ሰው ነው እንጂ ተፈጥሮአዊ የሆነው ሃብት፣ ማለትም ነዳጅ ወይም ማዕድን ብቻ አይደለም፡፡ ጃፓን ምንም ማዕድን የሌላት ሀገር ነች፡ ፡ ትልቁ የለውጥ ምንጯ የሰው ሀይል ነው"

**ዶ/ር መሰለ መንግስተአብ**
**/የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሶሻል ወርክ መምህር/**
**አዲስ ልሳን ጋዜጣ ሰኔ 4 ቀን 2011 ዓ.ም**

## ግጥም

### መድኃኒቱን

ከጀግናው እትብት ማህደር፣ ከማንነቱ ጎተራ፣
ከዛች ከናቱ ማጀት፣ ከደም ካጥንቱ አሻራ፣
ካሳ ሳይሰማ ሳያይ፣ ማነው የገባ ከቋራ?
ከደርቡሽ ሲዋጋ በጊንጥ፣
ማህዲስት በእባብ ሲያሯሩጥ፣
የጦቢያን ፍቅር ከልቡ፣ በደም ነጠብጣቡ ሲያነቁጥ፣
ቆዳውን በጋሬጣ፣ ባዶ እግሩን ሲገሸለጥ፣
ሲፋለም ከኖረበት
ፍቅሩን ካነገተበት
ወንድነት ከተካነበት፣ ማነው የገባ ከቋራ?
ልጅ ካሳ ከተከለበት፣ የናት ሀገሩን ባንዲራ፡፡
ለካ ያ ኮሶ ተጣብቶኝ፣ አድፍጦ ኑሮ እስከዛሬ፣
መድኃኒቱ አለመኖሩን፣ ቢያይ እኮ ነው መደፈሬ፡፡
የቋራው ካሳን ጥሩልኝ፣ ከዛች ኮሶ ሻጭ እናቱ፣
እያስቀመጠ ሳይወስደኝ፣ ይፈለግ ፍቱን መድኃኒቱ፡፡

***የቀንድ አውጣ ኑሮ***
***በይስማዕከ ወርቁ***



# “ዛሬ ጥላቻ፣ መፈናቀል፣ መጋጨት የበዛው የተዋቀርንበት ሲስተም “ክልል” በመሆኑ ነው”

## ፕ/ር አበራ መሸሻ

ፕ/ር አበራ መሸሻ ወለጋ ደምቢዶሎ ከተማ፣ቄለም አውራጃ “አረሜ ጫካ” ተብሎ ከሚጠራው የገጠር መንደር ውስጥ ነው የተወለዱት። አባታቸው መሸሻ ዋቄ የሚባሉ የሰላሌ ሰው ሲሆኑ፣ እናታቸው ተዋበች ይብረኩ የጅሩ ተወላጅ ናቸው።

የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ደምቢዶሎ ከተማ ካጠናቀቁ በኋላ ሐረር መምህራን ማሰልጠኛ በመግባት በመምህርነት ተመርቀዋል። ለአንድ ዓመት ያህል ጊምቢ በመምህርነት እንደሰሩ የቀድሞው ቀዳማዊ ኃ/ስላሴ ዩኒቨርስቲ በመግባት በሂሳብ ዘርፍ በዲፕሎማ ከተመረቁ በኋላ፤ በድጋሚ ወደ መምህርነት ሙያ በመመለስ ደብረ ብርሃን ኃ/ማርያም ማሞ ት/ቤት ለተወሰነ ጊዜ አስተምረዋል።

ዲግሪያቸውን ለመያዝ ወደ አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ በተመለሱበት ወቅት የዩንቨርስቲው የተማሪዎች ፕሬዝዳንት የነበረው ጥላሁን ግዛውን ጨምሮ ሰባት ተማሪዎች በጃንሆይ ፖሊሶች ሲገደሉ በዓይናቸው በመመልከታቸው፣ ከሂሳብ ይልቅ የመንግስትን ባህሪይ ለማወቅ “ፐብሊክ አድሚኒስትሬሽን” ለማጥናት ወሰኑ። የዩንቨርስቲው የፖለቲካል ሳይንስ ዲን ጥያቄያቸውን ቢቀበሉም ሌላኛው የዲፓርትመንቱ ኃላፊ ግን በጀመሩት የሂሳብ ዘርፍ እንዲቀጥሉ በመወሰን የፈለጉትን እንዳይማሩ ስለከለከሏቸው፣ ዳግመኛ በመድኃኔዓለም አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ወደ መምህርነት ሙያ ተመለሱ።

ላለፉት አርባ ሰባት ዓመታት በአሜሪካን ሀገር የኖሩት፣ ከወለጋዋ “አረሜ ጫካ” አነስተኛ መንደር ተነስተው፣ የፕሮፌሰርነት ማዕረግ የተጎናፀፉት፣ ከአርባ ዓመት በላይ በአሜሪካን ታላላቅ ዩንቨርስቲዎች ውስጥ በመምህርነት ያገለገሉት፤ እኚህ ታላቅ ኢትዮጵያዊ ምን ዓይነት የሕይወት ውጣ ውረዶችን አሳለፉ? ለሚለው ፕሮፌሰር አበራ መሸሻ ለእረፍት ወደ ኢትዮጵያ በመጡበት ወቅት የግዮን ጋዜጠኞች ሮቤል ምትኩና ፍቃዱ ማ/ወርቅ በዚህ መልክ አነጋግረዋቸዋል። መልካም ቆይታ።

***ግዮን፡- አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ከሂሳብ ትምህርት ይልቅ ፐብሊክ አድሚኒስትሬሽን ለማጥናት ያደረጉት ጥረት ሳይሳካ በመቅረቱ ወደ መምህርነት ተመልሰው፣ መድኃኔዓለም አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት እያስተማሩ ነበር ወደ አሜሪካ የሄዱት፡፡ ዕድሉ እንዴት ተፈጠረ?***

ፕ/ር አበራ፡- እ.ኤ.አ በ1970 ዓ.ም ዶ/ር ኤፍሬም ይስሃቅ የሚባል ሰው እዚህ መጥቶ ነበር፤ የዶ/ር ኤፍሬም ታናሽ ወንድም ዮናታን ይስሃቅ የአኔ ጓደኛ ስለነበር፣ በእሱ በኩል ዶ/ር ኤፍሬምን አገኘሁት፡፡ እዛ የትምህርት ዕድል አገኝ እንደሆነ ጠይቄው ስለነበር፤ እሱ ወደ አሜሪካ ከተመለሰ በኋላ የጉብኝት ደብዳቤ ላከልኝ፡፡ ያኔ እንደ አሁኑ ከባድ ስላልነበረ ደብዳዬን ይዤ ትኬት ገዛሁ፤ በጉብኝት መልክ ወደ አሜሪካ ተጓዝኩ፣ የዛሬ አርባ ስምንት ዓመት ገደማ ማለት ነው፡፡

ትራንስክሪፕቴን ይዤ ሄጄ ስለነበር እዛ ስደርስ በዶ/ር ኤፍሬም ይስሃቅ እገዛ ቦስተን ስቴት ኮሌጅ ገባሁ፡፡ እዚህ የነበረኝ የሶስት ዓመት የዩንቨርስቲ ክሬዲት ወደ እዛ ተዛውሮልኝ፣አንድ ዓመት ተኩል ነው የምረቃ ትምህርቴን የሰራሁት፡፡ የምፈልገውን ፐብሊክ አድሚኒስቴሬሽን በማግኘቴ ፣ በሀውድ ዩንቨርስቲ ማስተርሴን አጥንቼ እንዳገኘሁ የጃንሆይ መንግስት ተነሳ፡፡ ወደ ሀገሬ ልመጣ ባስብም አንዳንድ ሁኔታዎች ይስተ ካከሉ በሚል፣ ስጠባበቅ ►

ነገሮች ጭራሽ ከመጥፎነት ወደባሰበት ደረጃ ተሸጋገሩ፤ ቀይ ሽብር ሁሉ መጣ።

ያኔ ሀሳቤን ሙሉ በሙሉ ቀይሬ ለዶክትሬት ፕሮግራም ኒውዮርክ ዩኒቨርስቲ ሄድኩ። እሱን ከጨረስኩ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት ሳስብ፣ አሁንም እዚህ ያለው ሁኔታ ጥሩ ስላልነበር ሀውድ ዩንቨርስቲ አስተማሪነት ተቀጠርኩ። ሁለት ዓመት ካስተማርኩ በኋላ ዩናይትድ ኔሽንስ ለስድስት ወር ለስራ ወደ ኢትዮጵያ ሲልከኝ፣ ከአስራ አምስት ዓመት በኋላ በደርግ የስልጣን ዘመን አዲስ አበባ የመምጣት ዕድሉን አገኘሁ። ወደ አሜሪካ ላለመመለስና እዚሁ ሀገሬ ለመቅረት ፈልጌ ነበር፣ ግን ሁኔታዎችን ሳይ ገና ያልተረጋጋ በመሆኑ ተመልሼ ሄድኩኝ።

***ግዮን፦ በደርግ ዘመን በዩናይትድ ኔሽን ተወክለው የመጡበት የስልጠና አሰጣጥ ቆይታ ምን ይመስል ነበር?***

ፕ/ር አበራ፦ መልካም ጊዜ ነው ያሳለፍኩት። እንደውም ሰልጣኞቹ "እንደ እርስዎ ዓይነት ሌሎች ፕሮፌሰሮችን ሰብስበው ከፕሬዝዳቱ ጭምር፣የኢሰፓን ሰዎች በጠቅላላ ስለዴቨሎፕመንት አድሚኒስትሬሽን አሰልጥኑልን" የሚል ጥያቄ ሁሉ አቅርበውልኝ ነበር። ሰልጣኞቹ ብዙ ነገር እንደተማሩና በቆይታዬም ደስተኛ እንደሆኑ ነግረውኛል፡፡ ከመንግስት ኃላፊዎቹ ይልቅ ከሌሎች የታችኛው ሰልጣኞች ጋር የቀረበ ግንኙነት ነበረኝ። ከእኔ ጋር ከዩናይትድ ኔሽን የመጡ የውጭ ሰዎችም ከደርግ ባለስልጣናት ጋር ሲመገቡና ውስኪ እንደ ውሃ ሲጠጡ እኔ ከሰልጣኞቹ ጋር ነበር የምበላው። ባለስልጣናቱ እነሱ ወዳሉበት ብፌ ሲያስጠሩኝ "እዚህ ተመችቶኛል" ነበር የምላቸው። በምረቃ ስነ ስርዓቱም መድረክ ላይ ከተደረደሩት ሰባት ወንበሮች የእኔ ብቻ ባዶ ነበር፤ ሹማምንቱ ሲያፈላለፍጉኝ ያገኙኝ ከተመራቂዎቹ ጀርባ፣ ከኋላ ወንበር ተቀምጬ ነው። ይሄ የእኔ ባህሪይ ነው፣ በዚህ መልክ ነፃ መሆኔ ደግሞ ከብዙኃኑ ሰልጣኞች ጋር የበለጠ እንድቀራረብ አድርጎኛል። እነሱም በጣም ስለወደዱኝ ገንዘብ አዋጥተው የባህል ልብስ አልብሰውኛል፤ የሸለሙኝን የጣት ቀለበትም ይኸው ዕድሜዬን በሙሉ ይገፌው እየዞርኩ ነው።በርካታ ነገሮችን ነው በስጦታ ያበረከቱልኝ።

አሜሪካ እንደተመለስኩ አስተማሪነቴን ነው የቀጠልኩት። ሳውዘርን ዩኒቨርስቲ ስምንት ዓመት አስተምሪያለሁ። በመቀጠል አሁን ያለሁበት ዩንቨርስቲ እ.ኤ.አ 1994 ሎህክ ስቴት መጣሁ። እንግዲህ እዛ ደግሞ 26 ዓመት ነው ያስተማርኩት። ተማሪዎቼ ሳይቀሩ "የአሜሪካን መንግስት ጉድለት እንኳን ምን እንደሆነ የምታውቅ ሰው ነህ፣ ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ነገር እንሰማለንና ለምን ወደ ሀገርህ ሄደህ ባሉት ችግሮች ላይ የመፍትሄ ሀሳብ አታቀርብም" ብለው ደጋግመው ሲጠይቁኝ ወደ እዚህ መጣሁ ።

***ግዮን፦ አሜሪካኖቹ ከምን ተነስተው እንዲህ ዓይነት ሀሳብ ሊያቀርቡልዎት የቻሉት?***

ፕ/ር አበራ፦ እዛ "ሳዳም ሁሴን የተሰቀለበት ገመድ፣ በዶክቼኒ አንገት ላይ መቀመጥ አለበት" ብዬ የምናገር ሰው ነኝ፤ እስከዚህ ድረስ ነፃነት አለ። አሜሪካኖቹ ኢራቅ ላይ ጦርነት ሳይጀምሩ፣ የተወሰኑ ጀነራሎች የማስተምርበት ዩንቨርስቲ መጥተው ጦርነቱ ትክክለኛ መሆኑን ለተማሪዎቼና ለመምህራን ሲያስረዱ ተነስቼ በግልፅ ጦርነቱን የተቃወምኩ እኔ ብቻ ነኝ። "የአፍጋኒስታን ጦርነት ልክ ነው፤ አልቃኢዳ እነዛን ሕንፃዎች ኒውዮርክ ውስጥ ያወደመው ያላግባብ ነው። የኢራቅ ጦርነት ግን ምንም ምክንያት የለውም" ብዬ ተናግሬያለሁ።

ከእኔ በተጨማሪ ዴዝሞን ቱቱ ከሳውዝ አፍሪካ በመምጣት ዩናይትድ ኔሽንስ በመሄድ ጦርነቱ አግባብ እንዳልሆነ በመናገር ሲያወግዙ ብዙ ሰው ተከትሏቸው ነበር። በጊዜው ፕሬዝዳንት ቡሽና ዶክቼኒ " ስለሀገራችን እኛ እናውቃለን፣ ማንም ሊነግረን አይችልም" ሲሉ መናገራቸውን ብዙዎች ያስታውሱታል። ያኔ በዛ መልክ የጀመሩት ጦርነት አራት ሚሊዮን ሕዝብ እንዲያልቅ፣ እስካሁንም በቅጡ የቆመ መንግስት እንዳይኖራቸው አድርጓል፤ ኢራቃውያንን።

አሜሪካኖቹ ከእዚህ ሌላ ሊቢያ፣ ሶርያ ውስጥ ያደረጉትን እያየን ነው። እነሱ ዓላማ አላቸው፤ ግጭት ሲፈጠር ጥይት፣ መሳሪያ፣ቦንብና አውሮፕላን ይሸጣሉ። ይሄ ለእነሱ ትልቅ ሪሶርስ ነው። እኛ ግን ያንን አይደለም የምናየው፤ የሕዝባችንን ሰላምና አንድነት ነው የምንፈልገው። ዛሬ እኔ



ተደፋፍሬ መጥቼ "የማዕከል መንግስት ስልጣን በተዋረድ ወይንም በመገርሰስ ለአውራጃ፣ ለወረዳ እንዲሆን ይገባል" የሚል ሀሳብ ይዤ የመጣሁት፤ ዛሬ ስልጣን ላይ ያለው የጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ መንግስት እንዲህ ያለውን ሀሳብ ሊፈቅድና ሊደግፍ ይችላል በሚል ዕምነት ነው።

***ግዮን፦ ከሀገር ከወጡ ከአስራ አምስት ዓመት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ በዩናይትድ ኔሽን ተወክለው ሲመጡ፤ ሻዕቢያ ኤርትራን ለመገንጠል፣ ወያኔም ስልጣን ለመያዝ ከደርግ ጋር ጦርነት ላይ ነበሩ፡፡ እርስዎ እንደው አጋጣሚውን እንዴት አገኙት?***

ፕ/ር አበራ፦ ጊዜው ቀይሽብር የተፋፋመበትና ነገሮች ሙሉ ለሙሉ ያልጠሩበት ነበር። እ.ኤ.አ በ1986 ዓ.ም ዩኤን ወደ እዚህ ሲልከኝ፣ ማለትም ከ15 ዓመት በኋላ ወደሀገሬ በመጣሁበት ወቅት፤ ከተማዋ በብዙ ገፅታዋ እየተበላሸች፣ ትቻት የወጣኂት አዲስ አበባ አትመስልም ነበር፡፡ በብዙ መልኩ ሶሻል ሳይኮሎጂው በጦር የተወረረ ዓይነነት ሕብረተሰብ ነበር የማየው፡፡ የኢትዮጵያውያን ድፍረትና ወኔ ጠፍቶ፣ ሁሉም አንገት የመድፋት፣ የፍራቻ ስሜት ነበር የሚንፀባረቅበት። ያ ነገር በጣም ረብሾኝ፤ በኢትዮጵያ ተስፋ የመቁረጥ እሳቤ ውስጥ ሊከተኝ ሞክሮ ነበር። ነገር ግን ኢትዮጵያውያን ተስፋ አይቆርጡምና የፈራሁት አልሆነም።

ግን በወቅቱ ሕዝቡን በኢትዮጵያዊነቱ ኩራት የሚሰማው አድርጌ አልወሰድኩም፡፡ ሕዝቡ የደርግን ጥይትና ግድያ ፍራቻ፣ ያንን ድፍረትን የተላበሰ ኢትዮጵያዊነቱ ትቶ፣ አሜን ብሎ የመቀበል ዓይነት ነገር ነው የተመለከትኩበት። ሕወሓት ሲገባና ስልጣን ሲይዝ፣ ከደርግ ይብሳል ብሎ ሕዝብ አላሰበም ነበር። አሁን ግን የታየው ከዛ የከፋ ነው። በርግጥ "ወያኔ ከደርግ ይሻላል፣ ጥሩ ነው" የሚሉ ሌሎች ወገኖችም አሉ፤ እሱን ለእውነታው ነው የምንተወው።

ከበርካታ ዓመታት ቆይታ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ስመጣ ሌላው የተታዘብኩት ነገር ፣ ሰርቶ የማግኘት ስሜት፣ የመጣር ፍላጎት፣ ቀዝቅዞ ነው ያገኘሁት። ምክንያቱም ደርግ መጣና ሰው ለፍቶ፣ ደክሞ፣ በላቡ ያገኘውን እየወረሰ፤ ሕዝብን የስራ ተስፋና ዕምነቱን አሳጣው። ደስ የማይል ጊዜ ነበር። በጊዜው ዩናይትድኔሽን ስልጠና እንድሰጥ ነበር ወደ እዚህ የላከኝ። አሜሪካን የዶክትሬት ፕሮራሜን ሳጠና በፐብሊክ አድሚኒስትሬሽን ቲዮሪ ኤንድ ፕራክቲስ የሚል ዘርፍ አለ፤ አሁን እያስተማርኩ ያለሁት፣ እሱን ለመስጠት ነበር፡፡ ሁለተኛው ኢንተርናሽናል ኦርጋናይዜሽንስ ይሰኛል፤ ዩኤን፣ ወርልድ ባንክን የመሳሰሉትን አስተዳደር ገጽታ የሚመለከት ሲሆን፣ ሶስተኛው ደግሞ ዴቨሎፕመንት አድሚኒስትሬሽን ይባላል፤ ታዳጊ ሀገሮች ሕዝቡ እንዲያድግ ምን ማድረግ እንዳለባቸው የሚያመለክት ነው፡፡ ያንን ለስድስት ወር የመንግት ባለስልጣናት፣ ም/ሚኒስትሮች፣ ማናጀሮች፣ የየክ/ሀገር ም/አስተዳዳሪዎች ተሰሰብሰብው፤ ደብረዘይት የሚገኘው ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት ሳሰለጥን የቆየሁት።

***ግዮን፡- ፕ/ር አበራ ከደምቢዶሎ ጋር በተያያዘ ታሪክ ሆኖ የሚነገርልዎትን ትልቅ ነገር ከጥቂት ዓመታት በፊት እንደሰሩ ሰምተናል፡፡ እስኪ ይሄንን አጫውቱን?***

ፕ/ር አበራ፡- ሟች መውቀስ አይሁንብኝና “ደምቢዶሎ የኦነግ መፈልፈያ ነው” የሚል ግምት ነበራቸው አቶ መለስ ዜናዊ፡፡ ከዚህ በመነሳት ከጊምቢ ወደ ደምቢዶሎ የሚሄደው መንገድ በጠጠር እንዲቀር፣ አስፋልት እንዳይገባው ተደርጓል፡፡ በጃንሆይ የስልጣን ዘመን ሶስት ጊዜ ነበር አውሮፕላን ደምቢዶሎ የሚመጣው፡፡ ደርግ ስልጣን ሲይዝ በሳምንት አንድ ጊዜ ብቻ እንዲሆን አደረገው፡፡ በመለስ የስልጣን ዘመን ጊዜ ደግሞ እሱም ቀረና አውሮፕላን ማረፊያ ሜዳው ወደ ጫካነት ተለወጠ፡፡

በየዓመቱ ለዕረፍት ስመጣ፤ወደ ደምቢዶሎ በመኪና ለመሄድ ሁለት ቀን፣ ስመለስ ሁለት ቀን ስለሚወስድብኝ የትውልድ መንደሬን ሳላይ አዲስ አበባ እየከረምኩ ወደ አሜሪካ እመለሳለሁ፡፡ የዛሬ አምስት ዓመት ስመጣ ግን “የሆነው ይሁን የእናቴን መቃብር ማየት አለብኝ” ብዬ ሁለት ቀን በአውቶቢስ ተጉዤ ደምቢዶሎ ስደርስ፤ በደርግ ጊዜ የተሰራው የጠጠር መንገድ ጭቃና ጎርፍ ሆኖ ሰው መሄድ አይችልም፡፡ በተለይ ረዣዥም ቀሚስ የሚለብሱ የሀይስኩል ተማሪዎች ጭቃው እስከ ጉልበታቸው ይደርሳል፤ እሱን አይቼ እንባዬ ረገፈ፡፡

የደምቢዶሎ ሕዝብ ለምንድን ነው እንደዚህ የሚሰቃየው? የሚበደለውስ? ብዬ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ጠየቅሁ፡፡ ሁሉም በአጠቃላይ “ደምቢዶሎ መንግስት የላትም፤ ከላይ ተሹሞ ይመጣል፣ የሚችለውን ጉቦ ይበላል፡፡ እሱ ሲወፍር ደግሞ ሌላ ይመጣል” የሚል ምላሽ ነው የሚሰጡኝ፡፡ አንድ ቀን ማታ ሰዎች እራት ጋብዘውኝ፣ ከፊትና ከኋላ መብራት እየበራልኝ ወዳረፍኩበት ቤት ስመለስ፤ ጭቃው አድጦኝ የሚፈስ ጎርፍ ውስጥ ከነ ልብሴ ገባሁ፡፡ ያኔ ከመተኛቴ በፊት ተንበርክኬ “እግዚዘአብሔር ሆይ ለዚህ ለተበደለ ሕዝብ ቁምለት፡፡ እኔ መፍትሔ የለኝም፤ አንተ መንገዱን ፍጠር” በሚል እያለቀስኩ ከልቤ ፀለይኩ፡፡ እኔ ወደ እዛ ከመሄዴ ሁለት ሳምንት በፊት አባይ ፀሐዬ ደምቢዶሎ ሄደው ስለነበር፤ አዲስ አበባ እንደደረስኩ እሳቸውን ለማግኘት ፍለጋ ጀመርኩ፡፡ ይሄንን ነገር ሳጠያይቅ የሰማ የአሰላ ተወላጅ የሆነ ፓይለት፤ አሁን የእርሻ ሚኒስትር ለሆኑት ለአቶ ዑመር “አንድ ፕ/ር ከአሜሪካ መጥተው ስለደምቢዶሎ መንገድ መልካም ነገር እያሰቡ ነው” ብሎ ሲነግራቸው፤ አቶ ዑመርም “ይሄ ሰው ሳይሄድ አስተዋውቀኝ” ስላለ ኢንተርኮንትኔንታል ሆቴል ተገናኘን፡፡ መልሼ የደምቢዶሎን ችግር ለአቶ ዑመር ስናገር ስሜቴን መቆጣጠር አቅቶኝ እንባዬ ፈሰሰ፡፡ ያኔ ዑመር ከመቀመጫው ተነስቶ “ፕሮፌሰር ይተው! ይሄ የእኛ ችግር ነው፤ ሰዎች መርጠን የምንልከው ይሰራሉ ብለን እንጂ ህዝብ ላይ እንዲህ ዓይነት ችግር እንደሚደርስ አናውቅም፡፡” አለኝ፤ ይሄ አጋጣሚ ነው እንግዲህ ነገሮችን የቀያየረው፡፡

በማግስቱ ዶ/ር መሰለ የCCD ባለቤት ከሰለሞን ጋር ስለምንተዋወቅ እሱ ጋር ሄጄ የሆነውን ነገር ሳስረዳው “የነቀምትን ሕዝብ ለውጫለሁ፤ መንገድ ተሰርቷል፣ ውሃና መብራት ገብቷል፡፡ በተቃራኒ ደምቢዶሎ አሁን እንዳልከው ከሆነ ቃል እገባልሀለሁ፣ ሁሉን ነገር አደርጋለሁ” ሲለኝ ከአቶ ዑመር ጋር አገናኝቼ፣ ሁለቱን ለህሳቡ ዕውን መሆን እጅ ለእጅ ካያያዝኩ በኋላ ወደ አሜሪካ ተመለስኩ፡፡ አንድ ዓመት ቆይቼ ስመለስ ምንም የተሰራ ነገር የለም፡፡ “ዶ/ር መሰለ ምነው ቃልህን አጠፍክ?” ስለው፤ የተለያዩ ውጭ ሀገራት እንደነበረ ከይቅርታ ጋር ገልፆልኝ “አሁን ወደ ቀጣይ ስራችን እንግባ” አለኝ፡፡

በዛ መሰረት በአውሮፕላን ወደ ጋምቤላ እንድሄድና ከዛ ደግሞ የመንግስት መኪና ቀርቦ፣ በወታደሮች ታጅቤ ደምቢዶሎ እንድገባ አመቻቸልኝ፡፡ በወቅቱ የነበረው አስተዳዳሪ አቶ ታምራት ክበበው ይባላል፣ በጣም ቅን ሰው ነው፡፡ በእሱ አስተባባሪነት በቅድሚያ ካቢኔውን ሰብስቤ አነጋገርኩ፣ በቀጣይ ሕዝቡን በአዳራሽ ስብሰባን አወያየን፡፡ ሕዝብና መንግስት እንዴት አብረው መስራት እንዳለባቸው በጥልቀት ተወያየን፡፡ ሕዝብም በውስጡ ያመቀውን ነገር ተራ በተራ በግልፅ መተንፈስ ቻለ፡፡ በኋላ ልማቱን እውን የሚያደርግ ፣ ሕዝብንና መንግስትን ድልድይ ሆኖ የሚያገናኝ ኮሚቴ፤ ከሁለቱም ወገን አዋቅሬ፣ እኔም እግረ መንገዴን በሀገር ሽማግሌዎችና በሕዝብ ተመርቄ ተመለስሁ፡፡

አዲስ አበባ በገባሁ በማግስቱ ከዶ/ር መሰለ ቢሮ ተደውሎ፤ “የኦሮሚያ ም/ ፕሬዝዳንቶች (አራት ናቸው) ይፈልጉሃል” ተባልኩ፡፡ እውነቱን ለመናገር ያኔ የማደርገው እንቅስቃሴ ለሕይወቴ አስጊ ነበር፡፡ በዚህ በኩል ኦነግ “ኢህአዴግ የላከው ነው” ብሎ ሊያጠፋኝ ይችል ነበር፡፡ በመንግስት በኩል ደግሞ “ማን ስለሆነና ነው ሕዝብን ሰብስቦ እንዲህ የሚናገረው?” በሚል ብድግ አድርጎ ወህኒ ሊከተኝ ይችላል፡፡ እንደዛሬው የተሻለ ነገር ባይኖርም ሪስክ ወስጄ ነው የገባሁበት፡፡

በዚህን መሰሉ ስሜት ውስጥ ሆኜ ቢሮአቸው ስደርስ አንዱ ብድግ አለና“ በአሮ ሚያ መንግስትና ሕዝብ ስም፣ አብረውኝ ባሉት ጓደኞቼ ስም ለመናገር የምፈልገው ትናንትና ደምቢዶሎ የተናገሩትን ነገሮች ሁሉ ሰምተናል፡፡ በጣም ነው የምናመሰግነው፡፡ የእኛ ምሁራን በትክክል መሆን ያለበትን፣ እንዲህ ዓይነቱን ነገር ቢነግሩን መስራት እንችላለን፡፡ እርስዎ ያንን አሳይተውናል፤ በደምቢዶሎ ጉዳይ በአጭር ጊዜ አንድ ነገር ይሰማሉ፤ ቃል እንገባልዎታለን” ብለውኝ እንደ ልማዴ ወደ አሜሪካ ተመለስሁ፡፡ ዶ/ር መሰለ በሁለተኛው ወር 296 ሚሊዮን ብር ለመንገድ ግንባታው ፕሮጀክት እንደተመደበ ነገረኝ፡፡

በዛ መሰረት መሰለ ኮንትራቱን ወሰደ፤ ነቀምት ያደረገውን ደምቢዶሎ ላይ ተገበረ፡፡ እስካሁን ድረስ አስፋልት በአስፋልት እየሆነ ነው ከተማው፡፡



***...እ.ኤ.አ በ1993 የዛሬ ሃያ አምስት ዓመት አካባቢ፣ “አራት ወይም አምስት ዓመት ብቻ ነው የምትኖረው” ብለውኝ ነበር ሐኪሞቹ፡፡ ስምንት ዓመት ያስተማርኩበትን ዩንቨርስቲ ዊዚያናን ትቼ፣ አሁን ያለሁበት ቨርጅኒያ ቢች ስመጣ አየሩም ተስማማኝ፤ በዛው መጠን ሕክምናም እያደረግሁ የካንሰሩ እድገት ሳይጨምር በመቅረቱ እስካሁን አለሁ...***

***ግዮን፡- ለደምቢዶሎ ይህን ያህል ደክመው፣ መንገዱ እንዲሰራ ቢያደርጉም፤ የምርቃት ስነስርዓቱን ግን ድንገት ነው የተነገርዎት ሲባል ሰምተናል፤ ትክክል ነው?***

ፕ/ር አበራ፡- መንገዱ መሰራት ሲጀምር፤ ሕዝቡ ስልኬን እፈላልጎ እየደወለ “ደምቢዶሎ አይዷ በራ፤ በአበራ” እያሉ ምስጋናቸውን ቸረውኛል፡፡ መንገዱ ከተሰራ እና ከተጠናቀቀ በኋላ አምና ጠ/ሚ/ሩና አቶ ለማ መገርሳ ደምቢዶሎ ዩንቨርስቲና ኤርፖርቱን ሲመርቁ እንደሆነ በስልክ ተደውሎ ድንገት ተነገረኝ፡፡ ረቡዕ ነው የሰማሁት፡፡ “አንተ ተመላልሰህ ያሰራኸው መንገድ ነውና መምጣት አለብህ” አሉኝ፤ የምርቃቱ ቀን ስለደረሰ፣ ሀሙስ ትኬት ቆርጬ አርብ እዚህ አገባሁ፡፡ ቅዳሜ ደምቢዶሎ ኤርፖርት ስደርስ የነበረው አቀባበል፣ በከተማው ላይ ስንሄድ አስፋልቱ የነበረው ገፅታ በእጅጉ ይገርማል፡፡ እኔም ለስራው እግዚአብሄርን ከልብ አመሰገንኩ፡፡

ያኔ አንድ ቄስ “ዶ/ር አበራ የደምቢዶሎ ሕዝብ እንዳለ ይመርቅሃል” ሲሉኝ እሺ አልኳቸው፡፡ “ግን ደግሞ አንዳንዱ እየረገመህ ነው” አሉኝ፡፡ እኔም “ምን አጥፍቼ?” ብዬ ስጠይቅ፡፡ “መንገድ ሲመጣ ቤቱ የፈረሰበት አለ፡፡ ድሮ ሞተረኞች መንገድ እየመረጡ፣ በዝግታ ነበር የሚሄዱት፤ አሁን በአስፓልቱ እንደ ልብ እየሮጡ እየተገለበጡ ነውና እነሱም ይረግሙሀል” የሚል ምላሽ ሰጡኝ፡፡ መቼም ሁሉን ማስደሰት አይቻልም፡፡ ዋናው ነገር መንገዱ መሰራቱ ነው፡፡

***ግዮን፡- በአሜሪካን ሀገር የተመሰረተውና በአንድ ወቅት በእርስዎ ሊ/መንበርነት የሚመራው “ሀገራዊ ጉባኤ” የተሰኘው ድርጅት አሁንም አለ?***

ፕ/ር አበራ፡- ሀገራዊ ጉባኤ በባህርማዶ በርካታ ተግባራትን አከናውኗል፡፡ በዶ/ር አክሊሉ ከሚመራው ከተሰኘው አንጋፋ “ሸንጎ” የተሰኘ ድርጅት ጋርም በጥምረት ለመስራት ሞክሯል፡፡ ግን ብዙ ችግሮች በመሀል ነበሩ፣ በሀገራዊ ጉባኤ የተለያዩ ድርጅቶችን አቅፎ ለመያዝ የነበረው ሀብሳ በተወሰነ ደረጃ ተሳክቶ ነበር፡፡ አስራ ስምንት በአሜሪካ፣አውሮፓ፣ካናዳና ሌሎች ቦታዎች ያሉ ድርጅቶችን ለማቀራረብና አንድ ላይ ለመስራት ተሞክሯል፡፡ እዚህ ላይ ሀሳቡ እውን እንዲሆን ኤልያስ ክፍሌ በጣም ረድቶኛል፡፡ ግን ብዙም ሳንጓዝ የተለያዩ አለመግባባቶች ተፈጠሩ፤ በርግጥ ብዙዎች እኔ ባልፈልግም የእዚህ ስብስብ የማዕከል ኮሚቴው ሊ/መንበር እንድሆን ሀሳብ ስለነበራቸው ተቀብዬ በምሰራበት ጊዜ፤ አስቀድሞ ሀገራዊ ጉባኤ ውስጥ የነበሩ ሰዎች “የእኛ ድርጅት መስራት ያለበትን ስራ አሳልፎ፣ በራሱ ስልጣን ሌላ ኮሚቴ አቋቋመ፤ ራሱንም ሊ/መንበር አደረገ” የሚል ወቀሳ አቀረቡብኝ፡፡ በዚህ ተናድጄ ሀሳቤን በኢሜል በተንኩና ራሴን ከድርጅቱ አወጣሁ፡፡ ያ ድርጅት ሶስት ቦታ ተከፈለ፤ አሁን ስሙም የለም፤ ማን እንደሚመራውም አይታወቅም፡፡

***ግዮን፡- በውጭው ዓለም ያሉ ሰዎች የፖለቲካ ፓርቲዎችን በመቀላቀል በግልፅ ተቃዋሚነታቸውን ሲያውጁ በብዛት ይታያል፡፡ እርስዎ እስካሁን ድረስ በዚህ ደረጃ የየትኛውም አባል ያልሆኑበት ምክንያት ምንድን ነው?***

ፕ/ር አበራ፡- አንደኛ እኔ የጋንዲ ተማሪ ነኝ፤ በሁለተኛ ደረጃ የማርቲን ሉተር ኪንግ ተማሪ ነኝ፡፡ በነገ ባላንስ ነው የማምነው፡፡ ቀን ሀሳብ ካለ፣ ሕዝብ ሆ ብሎ ወጥቶ የፈለገውን ነገር መለወጥ ይችላል ብዬ አስባለሁ፡፡ ቀደም ሲል እንደገለፅኩት ከሀገራዊ ጉባኤ አመራርነቴ በገዛ ፍቃዴ ከለቀቅሁ በኋላ ድምፄን ሳላሰማ፣ ሁሉን ነገር እርግፍ አድርጌ ነው የተቀመጥኩት፡፡

እኔ የሉኪሚያ ካንሰር ተጠቂ ነኝ፡፡ እ.ኤ.አ በ1993 የዛሬ ሃያ አምስት አካባቢ፣ “አራት ወይም አምስት ዓመት ብቻ ነው የምትኖረው” ብለውኝ ነበር ሐኪሞቹ፡፡ ስምንት ዓመት ያስተማርኩበትን ዩንቨርስቲ ዊዚያናን ትቼ፣ አሁን ያለሁበት ቨርጅኒያ ቢች ስመጣ አየሩም ተስማማኝ፤ በዛው መጠን ሕክምናም እያደረግሁ የካንሰሩ እድገት ሳይጨምር በመቀረቱ እስካሁን አለሁ፡፡

የሚገርመው ነገር እግዚአብሄርን “የኢትዮጵያን አንድ ነገር ሳላይ፣ ጌታ ሆይ ወደ አንተ ልመጣ ነወይ?” እያልኩ ሁሌ እጸልይ ነበር፡፡ ብዙ ሰዎች በፖለቲካ ውስጥ እንድቀሳቀስ ይፈልጉ ነበር፤ ግን እኔ ከዛን ጊዜ ወዲህ ሁሉን ትቼ ተስፋ ያደረግሁት በፈጣሪ ብቻ ነበር፡፡

***ግዮን፡- በ1997 ዓ.ም ምርጫ ወቅት በአጋጣሚ ለዕረፍት እዚህ ነበሩ፤ እስኪ ያኔ የታዘቡትን ወደ ኋላ መለስ ብለው ቢያጫውቱን?***

ፕ/ር አበራ፡- ቅዳሜ ኢህአዴግ ጠርቶ ሰዎች ሰልፍ ሲወጡ፣ በማግስቱ የቅንጅት ደጋፊ ከተማዋን እንደዚያ ሲያስጨንቃት ተመልክቻለሁ፡፡ የምርጫው ቀን ደብረዘይት ነበርኩ፤ እዛ አራትና አምስት ምርጫ ጣቢያዎች ነው ያሉት፡፡ ማታ ላይ ያረፍኩበት ሆቴል አንድ ስድስት ታዛቢዎች መጥተው “ፕ/ር ቅንጅት አሸንፏል፡፡ ይሄንን አሜሪካ ሲሄዱ ይንገሩልን” አሉኝ፡፡ ሙሉ ውስኪ አውርደው፣ ጋብዘውኝ እነሱ ወጡ፡፡ እዛው ቁጭ ብዬ ቲቪ ስመለከት መለስ በቴሌቭዥን ብቅ ብሎ፣ “ኢህአዴግ አሸንፏልና ሁለተኛ ጣት መቀሰር የለም፡፡ ጣቱን የሚቀስር ይቆረጣል” ሲል ተናገረ ፡፡ ትንሽ ቆይቶ ደግሞ “የፖሊስ ዋና አዛዥ ጠ/ሚኒስትሩ ሆነዋል” አለ፡፡ ቀየና ደግሞ “በየክ/ሀገሩ የሚቆጠሩ ድምፆች አሉና እነርሱን መጠበቅ ይኖርብናል” ሲል ተናገረ፡፡

ያኔ የመለስ ዜናዊ መንግስት የሚሰጠው መግለጫ እርስ በርሱ የሚጣረስ ነበር፡፡ “ኢህአዴግ አሸንፏል”፣ ብሎ ተናገረ፡፡ ግን ደግሞ “የሚቆጠሩ አሉ” የሚል መግለጫ ደግሞ ሰጠ፡፡ ይሄ የሆነው ሰኞ ነው፡፡ ማክሰኞ ወደ አ/አ ተመልሼ ጠዋት ኢ.ሴ.ኤ ጉዳይ ስለነበረኝ ልሄድ ስል ትራንስፖርት የለም፡፡ “ዛሬ ዝግ ነው፤ ሰራተኛው አድማ አድርጓል” ተባለ፡፡ ከዛ ተኩስ ተጀመረ፤ አንዲት ልጅ ኮተቤ ተገደለች፡፡ ነገሩ ወደ ዩንቨርስቲ ተሸጋገረ፡፡ በኋላ የሆነው ነገር ሁሉ የሚያሳዝን፣ የተወሰዱት ዕርምጃዎች በሙሉ ኃይልን የተመረኮዙ እንደነበሩ አንዘነጋም፡፡

***ግዮን፡- አሁን ከሃያ አመት በኋላ ደግሞ ወደ ፖለቲካ እየተመለሱ ነው፡፡ እንደ መፍትሄ ይዘው የመጡት ሀሳብ አለና እስኪ ስለ እርሱ አንዳንድ ነገሮች ያካፍሉን?***

ፕ/ር አበራ፡- መቼም በተባበሩት መንግስታት ሃሳብ፣ ፅሁፍና ወሳኝ ነጥቦች የማያምን ሰው አለ ማለት ከባድ ነው፡፡ የስልጣን ጉዳይ በተለይ ለታዳጊ አገሮች የስልጣን መገርሰስ፣ ከማዕከል መንግስት ብቻ እየተሾመ መላክ እንደሌለበት የተባበሩት መንግስታት ሀሳብ ይናገራል፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ደግሞ ለብዙ ጊዜ ዲሞክራሲ፣ ዲሞክራሲ እንላለን ግን በትክክል ቃሉ አልተተገበረም፡፡ ምንድን ነው? ይሄ ዴሞክራሲ? ትክክለኛ ዴሞክራሲ ለሕዝብ እንዲሆን ማድረግ የሚቻለው ዩኤን የሚናገረውን ሀሳብ ስራ ላይ እንዲውል ማድረግ ሲቻል ብቻ ነው፡፡

ክልል የሚለው ነገር ዛሬ ብዙ ችግር እያሳየን ነው፤ ራሳቸውን እንደ መንግስት የሚያስቡ ሰዎች እየተመለከትን ነው፡፡ ማን? ለምን? እንዴትመጣው፣ ይሄ ለብዙዎቻችን ግልፅ ነው፡፡ ሕዝብ የራሱ ሕግ አውጪና አስፈፃሚ አሰራር መኖር አለበት፡፡ አሁን የማዕከል መንግስት እንደ ባህል አድርጎ የሚወስደው ነገር፣ የክልል መሪዎችን ጠ/ሚሩ ነው የሚሾመው፡፡ ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ ይሄ አሰራር ባህል ሆኖ ቀርቷል፡፡ በፊት መለስ በዚህ መልክ ኦሮሚያ ላይ አንዴ ኩማን፣ ሌላ ጊዜ ጁነዲንን፣ ቀጥሎ አባዱላን እያረገ የፈለገውን ሲሾም፣ ሲሽር ነው የኖረው፡፡ ይሄ አሰራር መቅረት አለበት፤ በተለይ በአሁኑ ሰዓት፡፡ መሪዎቹን ሕዝብ ራሱ መምረጥ ይኖርበታል፡፡ ስለዚህ ይሄ ክ/ሀገር፣ ክልል የሚባለው ነገር ይቅርና መዋቅሩ እስቲ በወረዳ ይጀመር፤ የማዕከል መንግስት ማለት በራሱ ፍላጎት የሚሄድ አንድ ሰውን ነው አምጥቶ በፈለገው ክልል ላይ ቁጭ የሚያደርገው፡፡ ከዚህ አካሄድ ወጥተን እስቲ ከስር ጀምሮ መሪዎቻችን ራሳችን እየመረጥን፣ ዴሞክራሲን በትክክል እየተገበርን እንሂድ፡፡ ስልጣን የሕዝብ መሆን ይኖርበታል፡፡ የተወሰኑ ምሁራኖች በዚህ ሃሳብ ላይ በሙሉ መግባባት ቢተባበሩ፣ ጠ/ሚኒስትሩ ቢያንስ የተወሰነውን ነጥብ ስራ ላይ እንደሚያውሉ ሙሉ ዕምነት አለኝ፡፡ ዛሬ ጥላቻ፣ መፈናቀል፣ መጋጨት የበዛው የተዋቀርንበት ሲስተም “ክልል” በመሆኑ ነው፡፡

በቅርቡ እንደሰማነው የድንበርና የማንነት ኮሚሽን የሚባል ተቋቁሟል፤ እነሱ አሁን ምንድን ነው የሚሰሩት? “ክልል ይወገድ፣ ይቅር!” የማለት አቅሙ፣ የማሳመኑ ችሎታ አላቸው? ይሄ ከባድ ነው፡፡ ቢቻል ክልል የሚለው ነገር ይቅር፡፡ አሁን ለምሳሌ እኔ ከኦሮሞና አማራ የተወለድሁ ኢትዮጵያዊ ነኝ፡፡ በዚህ መልክ ሚሊየንስ አበራዎች አሉ፤ ከትግሬና አማራ፤ ከአማራና ኦሮሞ፣ የተወለዱ፡፡ ይሄ እውነት ኢትዮጵያውያንን ባስተሳሰረበት ሁኔታ ክልል ምን ያደርጋል? ይሄንን ፀጋ ተቀብለን ታላቂቱን ኢትዮጵያ ማምጣት የሚቻለው የዩኤን መርህ የሆነውን ስልጣንን ለሕዝብ የማድረግ ሲስተም መተግበር ስንችል ነው፡፡

***ግዮን፡- ሕገ መንግስቱ፣ ኢህአዴግ የሚከተለው የፖለቲካ ሲስተም፣ ከዛም ባሻገር በብሔር የተደራጁ የፖለቲካ ፓርቲዎች ፍላጎትን ከተመለከትን ይህን ሀሳብ በዚህች ሀገር ላይ ዕውን ማድረግ ይቻላል?***

ፕ/ር አበራ፡- የሕዝብ ጥያቄ አይሎና ገፍቶ ከመጣ ምንም የማይሆን ነገር የለም፡፡ እንግሊዞች ወደው አይደለም ሕንድን የለቀቁት፡፡ ሕዝብ ለተቃውሞ ሆ ብሎ ሲወጣ፣

የመጀመሪያው ረድፍ ላይ ያለው ሕዝብ በጥይት ሲረግፍ የተመለከተው ከኋላ ያለው ሰልፈኛ፣ ሸሽቶ ወደ ኋላ አልተመለሰም፤ ተቃውሞውን አጠናክሮ ወደፊት ነው የገፋው:: ይሄን ዓይነት ነፃነት፣ ራስን በራስን በትክክለኛ መንገድ የማስተዳደር ፍላጎትን ባገናዘበ መልኩ ሕዝብ ሆ ብሎ ከተነሳ የማይቀየርና የማይተገበር ነገር የለም:: አሁን ደግሞ እንደ ዕድል ሆኖ ጥሩ ጠ/ሚ/ር አለን፡፤ በነገራችን ላይ ይሄ ሀሳብ በሌላ ዓለም የተሰራበት ነው:: እኛ ጋር የማይሆንበት ምክንያት ምንድን ነው? በርግጥ “ይሄ ነገር ከመጣ የእኔ ጥቅም ሊቀር ነው” ብለው የሚያስቡ ሰዎች በመንግስትም፣ በተቃዋሚ ፓርቲዎች ውስጥ ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ እሱ እንደተጠበቀ ሆኖ የሕዝብ ፍላጎት፣ ጥያቄና አንድነት ግን መጠበቅ አለበት:: እንግዲህ እኔም ይሄን ሃሳብ ይዤ መጥቻለሁ፣ ጠ/ሚኒስትሩን ጨምሮ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግስት ኃላፊዎችን ለማግኘት እየጣርኩ ነው::

***ግዮን፡- ከዓመታት በፊት የአፍሪካ ዩንቨርስቲን በኢትዮጵያ ለማቋቋም የተወሰነ ዕርምጃ ተራምደው ነበር:: ግን ሀሳብዎ በመለስ ዜናዊ ዕገዳ ምክንያት ተደናቅፏል:: ምክንያቱ ምን ነበር?***

ፕ/ር አበራ፡- አፍሪካን ኢንተርናሽናል ኦርጋናይዜሽን ዩንቨርስቲን ለማቋቋም መነሻ የሆነኝ እ.ኤ.አ በ2000 ዓ.ም አንድ ትልቅ ካምፓኒ 2.5 ሚሊየን ብር፣ አርብ ተጀምሮ እሁድ ለሚያልቅና አዲስ አበባ ለተካሄደ ኮንፍረስ በጀት መድቦ ነበር:: “የአዕምሮ ወይም የተማረ ሰው ፍልሰት ለምንድን ነው?” በሚል ዙሪያ ለመነጋገር፣ በአፍሪካ ያሉት ትምህርት ሚኒስትሮች፣ በውጭው ዓለም ያሉትም ተሰባስበው የተወያዩበት መድረክ ነው::

በወቀቱ ተሰብሳቢዎቹ ሁለት ነገሮች ምክንያት ሰጥተው ነው የሄዱት:: አንዱ ያለው የፖለቲካ ሲስተም የተማረ ሰውን ወደ ውጭ ይገፋዋል:: የተማረ ሰው ያለማቋረጥ ጥያቄ ስለሚጠይቅ፣ እንደሱ አይነቱን ስልጣን ላይ ያለው አካል ስለማይፈልገው፣ ከሀገሩ እንዲወጣ ይገፋዋል:: ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ የውጭው ዓለም ሀገራት የተማረውን ኃይል ከየሀገሩ ይሰበስባሉ፣ ይመጣሉ:: እነዚህ ሰዎች “ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት ዶክተሮች፣ ኒውዮርክ ያሉት በብዛት ረገድ ይበልጣሉ” የሚል ምሳሌ ማቅረባቸው ደግሞ በጣም እንዲሰማኝ አደረገኝ:: እኔ አሜሪካ ለሶስት ዓመት ለመማር ነው የሄድኩት፣ ግን አርባ ሰባት ዓመት በሰው ሀገር ቀረሁ::

በኋላ በዚህ መልክ “ብሬን ሪቴን” የሚለ ውን ሀሳብ አመንጭቼ አንድ ሀሳብ ላይ ጽሁፍ አቀረብኩ:: በጊዜው ብዙ ፓስተሮች ተጋባዥ ነበሩ፤ አንዱ ፓስተር ሀሳቤን በጣም ስለወደደው፣ ይሄንን ነገር ወደ ተግባር ለመለወጥ ተነጋገርን:: ቨርጅኒያ ስቴት ብቻ 750 ቸርቾች አሉ፤ እሱ የእዛ ማህበር ም/ፕሬዝዳንት ስለሆነ ፈንዱን ሕዝቡን በማስተባበር ሊሸፍን ተስማማን፡፡ አራት ጊዜያት ያህል አብረን ወደ አዲስ አበባ መጥተናል::ያኔ ሰዓሊ ሻምበል ለማ ጉያ ለህክምና ኒዮርክ መጥተው ስለነበር፤ ሀሳቤን አማክሪያቸው፤ የአፍሪካ ዩነቨርስቲውን ምስረታ ሀሳብ በፅሁፍ ላክሁላቸው፤ እሱን

***...የውጭው ዓለም ሀገራት የተማረውን ኃይል ከየሀገሩ ይሰበስባሉ፣ ይመጣሉ:: እነዚህ ሰዎች “ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት ዶክተሮች፣ ኒውዮርክ ያሉት በብዛት ረገድ ይበልጣሉ” የሚል ምሳሌ ማቅረባቸው ደግሞ በጣም እንዲሰማኝ አደረገኝ...***

በወቅቱ የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንት ለነበረው ጁነይዲን ሳዶ ቢሮው ሄደው ሰጡት::

***ግዮን፡- ከአቶ ጁነይዲን ምን ምላሽ ተሰጥዎት?***

ፕ/ር አበራ፡-ሀሳቡን ስለደገፊው ሶስት ገጽ ሙሉ ደብዳቤ ፅፎ፣ ወደ ኢትዮጵያ እንድመጣ ነው የጠየቀኝ:: ያኔ አብረውኝ ሰባት ፓስተሮች ናቸው ወደ ኢትዮጵያ:: በእሱ ቢሮ ተገናኝተን በግልፅ ተወያየን:: በሌላ ቀን ሶስት ፓስተሮችን ይዤ ሄድኩ::ጁነይዲን ብሪሊየንት ነው፤ ማስተርሱን እንግሊዝ ሀገር የተማረ በመሆኑ ስለአሜሪካን ሲቪልራይት፣ ማርቲን ሉተርኪንግ ሞት በዝርዝር ሲነግራቸው ፓስተሮቹ በጣም ተገረሙ:: አደነቁት:: ከዛ በኋላ በዚህ ቢሮ ውስጥ እንፀልይ ተብሎ ጁነይዲንን መሀል አቁመን በፓስተሮቹ አማካይነት ፀሎት ተደረገ::

በኋላ ምሳ ጋበዘንና “ምንድን ነው የምትፈልገው? አለኝ፤ “ለጊዜው እዚህ ደርሰናል ለማለት፣ እንደ እሴት መሬት ብናገኝ” ጥሩ ነው ስለው፤ መኪና ከሹፌር ጋር ሰጠኝና ዞረህ ፈልግ አለኝ:: እስከ ዝዋይ ነው የተንዝኩት:: መጨረሻ ላይ ቢሾፍቱ አከባቢ ለሶሻል ሳይንስ፣ ሞጆ ለሜዲካል ሳይንስ፣ አዋሽ ለአግሪካልቸራል ኢንዱስትሪ ሶስት ካምፓስ ለመመስረት ቦታ መረጥኩ:: ለጊዜው ቢሾፍቱ በመረጥነው ልንጀምር ቦታ አግኝተን፣ አየር ኃይል ክለብ ትልቅ ድግስ ጁነይዲን ደግሶ፣ ፕ/ት ግርማ ወ/ጊዮርጊስና አቶ ግርማ ብሩ ባሉበት በክብር ተሞግሰናል:: ተሸኝተናል::

በኋላ ጉዳዩን ይዘን አሜሪካን ኮንግረስ በማድረስ ለመጀመሪያ ግንባታ 50 ሚሊዮን ብር ስንጠይቅ “የኢትዮጵያ መንግስት ከደገፈው በዚህ ብቻ ሳንቆም፣ ሌላም ዕርዳታ እንሰጣለን” ስላሉ፤ ተስፋ በማድረግ ወደ ኢትዮጵያ ብንመጣም፣ መለስ ዜናዊ የድጋፍ ደብዳቤውን ሊፅፍልን ባለመቻሉ ሀሳባችን ዕውን ሳይሆን ቀርቷል::

***ግዮን፡- በጊዜው ቨርጅኒያ ውስጥ ያሉት 750 ቸርቾች ፕሮጀክቱ ውስጥ አሉበት መባሉ የሐይማኖት ወረራን አስመስሎ እንደነበር በስፋት ተነግሯል:: ምናልባት ያ ይሆን?***

ፕ/ር አበራ፡- የሃይማኖት ወረራ አልነበ ረም:: በቅንነት የአእምሮ ፍልሰትን ከአፍሪካ ለማቆም፣ አካዳሚክን መሰረት ያደረገ ፕሮጀክት ነው:: እኔ የእግዚአብሔር አማኝ ነኝ፤ እዚህ ነኝ፣ እዚያ ነኝ ባልልም፤ በርግጥ ኦርቶዶክስ ነኝ:: ሀሳባችን ከአፍሪካ ሀገራት በሙሉ ነበር ተማሪዎችን ለመሰብሰብ ያቀድነው፡፡ ማስተርስና ፒኤችዲ ነው የምንሰጠው፣ አንደር ግራጁየት የለም:: ከፍ ባለ ደረጃ ነው ሀሳቡን የጠነሰስኩት:: ምክንያቱም ብዙዎቻችን ለከፍተኛ ትምህርት እየሄድን ነው እዛ የምንቀልጠው እንጂ፣ እንደተባለው የሃይማኖት ጉዳይ አልነበረውም::

***ግዮን፡- በዛን ወቅት በመላ ሀገሪቱ በተለያዩ ቦታዎች አዳራሾችን በመከራየት መንቀሳቀስ የጀመሩ፣ የፕሮቴስታንት ቸርቾች ተበራክተው ነበር:: በድጋፍ ረገድ ወደኢትዮጵያ ሲመላለሱ ከነበሩት ሰባት ፓስተሮች ጋርስ ግንኙነት ይኖረው ይሆን?***

ፕ/ር አበራ፡- በፍፁም አልነበረውም:: ምንም ግንኙነት አልነበራቸውም:: ግንኙነት የጀመሩት በዚህ ፕሮፖዛል መጥተው በነበረበት ሁኔታ ከአካዳሚክ ጋር በተያያዘ እንጂ ሌላ ተቀፅላ ሀሳብ አልነበረውም::

***ግዮን፡- ከጀርባ እንዲህ ዓይነት ዓላማ ከሌላ የእርስዎ ፕሮጀክት በጠ/ሚ/ሩ ለምን ተቀባይነት አጣ?***

ፕ/ር አበራ፡- የሀገራዊ ጉባኤ ፕሬዝዳንት በነበርኩበት ጊዜ፣ በየስቴቱ እየሄድኩ የፓርላማ የበላይነትን በመናገር ትልቅ ቅስቀሳ አደርግ ነበር፡፤ በዛ ጊዜ ዳዊት ዮሐንስ ፓርላማ ውስጥ ቆሞ ነው ያወገዘኝ:: “አንዳንዶች ቾክ መለቅለቅ ትተው፣ ሀገር እንመራለን እያሉ ነው:: ይህን አካል የሚመራው አበራ ሚሊሻ በሚባለው ሰው ነው” በሚል የተናገረው ፣ኢንዲያን ኦሽን ጆርናል ላይ ወጥቷል::

እኔ በፖለቲካ መስክ የፖለቲካ ትርፍ አገኛለሁ ብዬ የማስብ ሰው አይደለሁም:: ፖለቲከኞቹ የሚናገሩትን ለምን አይፈጽሙም? ነው የምለው:: በኋላ ሀሳቡን ዕውን ለማድረግና ከአሜሪካ መንግስት ድጋፉን ለማግኘት የኢትዮጵያ መንግስት ደብዳቤ እንዲፅፍልን ፓስተሮቹን ይዤ መጣሁ:: መለስ ዜናዊ ቢሮ ቀጠሮ የያዘልን ጁነይዲን መለስ ጋር ከፓስተሮቹ ጋር አብሬ እንድሄድ ፈልጎ ነበር፡፡ “ግድ የለም፤ እኔ ልቅርና እናንተ ሂዱ” ብዬ አሜሪካኖቹ በቀጠሮው መሰረት ሄደው ነበር:: የእኔ ስም በኢህአዴጎች ዘንድ በመጥፎ በመነሳቱ መሄዴ አላስፈላጊ ነበርና::

ግን የሚገርምህ እነዛ ሰዎች ጠ/ሚ/ሩ ቢሮ በተባሉት ሰዓት ቢደርሱም፣ መለስ “ከዚህ ፕሮጀክት በስተጀርባ ኢህአዴግን ሲተች የኖረው አበራ መሸሻ የተባለ የሀገራዊ ጉባኤ ፕሬዝዳንት የነበረ ሰው አለ” ብሎ ስላመነ ሊያነጋግራቸው፣ ፕሮጀክቱንም ሊደግፍ አልፈለገም:: ቢሮ ውስጥ ሁለት ሰዓት ያህል ቢቀመጡም አል ተጠሩም:: በኋላ መልዕክተኛ መጥቶ “ጠ/ሚ/ሩ ሌላ አስቸኳይ ጉዳይ ስላጋጠማቸው መገኘት አልቻሉም፣ ከሶስት ቀን በኋላ ተመለሱ” የሚል መልዕክት ደረሳቸው:: በዚህ መንገድ ከመንግስት ፈፅሞ ድጋፍ እንደማናገኝ ስናውቅ፣ ያንን የመሰለ ፕሮጀክት ውስጣችን እያረረም ቢሆን እርግፍ አድርገን ተውነው::

***ግዮን፡- እናመሰግናለን::***



ጥላሁን መሸሻ

# ኢትዮጵያ ዛሬ አርበኛ ትውልድ ትፈልጋለች !

*(ካለፈው የቀጠለ)*

የዚያ ዘመን ትውልድ ለዚህ ወይም ለዚያ ዘር ወይም ነገድ፣ ጎሳ ወይም ብሔር አልታገለም፣ ስለ ሕዝብ በደል፣ ስለሰዎች ልጆች "ሰብዐዊ ውርደትና ጭቆና ለምን" ብሎ ነበር የተነሳው፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰርቶ ለምን ይደኸያል? በሀገሩ ለምን የውርደት ኑሮ ይኖራል? ለምንስ ኢትዮጵያ ሀገራችን የድሆች ድሀ ትባላለች? ብሎ ጠየቀ፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያ ለውጥ ያስፈልጋታል፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ መማር፣ ማደግና ከኂላ ቀር ሕይወት መላቀቅ ይገባዋል፣ መብቱም ነው ብሎ ጠየቀ፣ ታገለ፣ መስዋዕትነትንም ተቀበለ፡፡ ለግፍ አገዛዝ ሳይንበረከክ፣ ለግል ጥቅምና ልዕልና እጁን ሳይሰጥ "ለዚች ሀገር ድህነት፣ ለዚች ሀገር ኂላቀርነት፣ ለዚች ሀገር ርሀብና ጉስቁልና አይገባትም" ብሎ ታላላቅ አባቶቹ ስለሀገራቸው ክብር በድንበር ላይ እንደወደቁ ሁሉ እርሱም የነፃነት ዓርማ ይዞ፣ የነፃነት ባንዲራ ሰቅሎ በግፈኞች አደባባይ ወደቀ፡፡ ምንም እንኳን ድል ባይቀናውም ለትውልድ መማሪያ ታሪክ ጥሎ አለፈ፡፡ ያ ክቡር ዜጋ ስለሀገሩ ክቡር ሕይወቱን ሳይሳሳ ገበረ፣ ካልወሰደ የታሪክ አስተማሪነቱ ይሰረዛል፡፡ የሰውም አዋቂነቱ ውሸት ይሆናል፡፡ ታሪክንም በአስተማሪነቱ መቀበል አይቻልም፡፡ ከትናንቱ ተምሮ ዛሬን ማሳመር ካልቻለ፣ የሰው ልጅ ብልሀቱና አስተዋይነቱ ከጭንቅላቱ አይኖርም፡፡ ከትናንት ዛሬ ተሽሎ የለውጥና ዕድገት ባለቤት መሆን ከስዎች ሕይወት ውስጥ ይሰረዛል፡፡ በመሆኑም ሰዎች ከትናንት ዛሬ፣ ከዛሬ ደግሞ ነገ የተሻለ ሕይወት አይኖራቸውም፡፡ ለዚህም ነው እኛ ከታሪክ ባለመማራችን ሕይወታችን ዝም ብሎ መኖር ብቻ እንጂ ለውጥ ማሳየት ያልቻልነው‹፡፡ እኛ የ1950/60ዎቹ ትውልዶች የለውጥ ሀሳብን ከቀደምቶቻችን የአውሮፓና የቻይና ኮምኒስቶች ተማርን፡፡ የትግል ጥበባቸውንና ስልታቸውንም እንዳለ ገልብጠን ከቦታና ሁኔታዎች ጋር ሳናገናዝብ፣ ከኛ ዘመን ባህሪ፣ ከኛ ሀገር ሁኔታ ጋር ያለውን ተመሳሳይነትና ልዩነት ሳናወዳድር ርዕዮተ ዓለሙንም፣ ተግባሩንም እንዳለ ገልብጠን ስራ ላይ ለማዋል ሞከርን፡፡ ጥበብና ስልቱን በዚያ አገርና ሁኔታ እንደነበረ ወስደን፣ ያለ ምንም ማስተካከል "ሌኒን እንዲህ አለ፣ ማኦ እንዲህ አለ" እያልን "በሬን ንዳ ገበሬ" ብለን በነበረው የትግል ማጥ ውስጥ ገባንበት፡፡

በወቅቱ እኛን የገጠመን ሀይል እንደ ራሻዎቹና ቻይናዎቹ የታሪክ አስተማሪዎቻችን ውስጥ፡፡ ልዩነታችን እንኳን ለሀገራችን ሕዝብና ደጋፊዎቻችን ግልፅ አልነበረም፡፡ የስልጣን ንጥቂያ ግብግብ ብቻ መስሎ በሚያሳዝን ሁኔታ አለፈ፡፡

በአዲስ ጦር የተሳለ የወታደር መንግሥት፣ ሥልጣን የተራበ የጎረምሶች ቡድን፣ የኛኑ ርዕዮትዓለም በታጠቀ ማርክሲስት ሌኒንስት ነኝ ባይ ኃይል እየታገዘ፣ አንድ ዓይነት ስብከት፣ አንድ አይነት ርዕዮትዓለምና አንድ ዓይነት ገታራነት ይዘን ተወዛገብን፡፡ ሕዝባችንንም ግራ አጋብተን በጋራ እና በአንድነት አለቅን፤ እርስ በራሳችንም ተጫረስን፡፡ ኢትዮጵያ ሀገራችንም ኪሷን አራግፋ፣ ወዳጆቿንም አስቸግራ ያስተማረቻቸውን እጂግ ብዙና ምጡቅ፣ ለሀገር ተቆርቋሪ ዜጎችዋን አጣች፡፡ በሀዘን ተቆራምዳ፣ በቂም በቀል ተለውሳ ከል ለበሰች፡፡ "የገደለው ባልሽ የሞተው ወንድምሽ ሀዘንሽ ቅጥ አጣ፣ ከቤትሽ አልወጣ" ሆኖ ያ ጊዜ አለፈ፡፡ እንግዲህ በዚህ የታሪክ ሂደት ውስጥ ማን ነበር ትክክል? ማነስ ነበር የተሳሳተ? "ኢትዮጵያ በልጆችዋ ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር" የሚለው መፈክር ባዶ ወሬ ሆኖ ቀረ፡፡ በመጨረሻም ምኞታችን፣ ርዐያችንና በርቀት ስናየው የነበረው የሀገር ዕድገትና ብልፅግና፣ የዜጎቻችን የክብርና የልዕልና ምናባችን እንደጢስ በኖ ቀረ፡፡ ይልቁንም ያ በዚያን የትግል ዘመን የነበረው የአንድ ኢትዮጵያ ልጆች ወንድማማችነት፣ መከባበርና መተማመን ማሰሪያው ላልቶ ይኸው ዛሬ ደግሞ በዘውግና በጎጥ ተቧድነን ፣ ዛሬም እንደገና እርስ በራሳችን እንታመሳለን፡፡ መቼ ተረጋግተን? መቼስ ተመካክረን? መቼስ ለስራ፣ ለትምህርት፣ ለምርምርና ለዕድገታችን እንስራ? መማር አለብን፡፡ አሁንም፣ አሁንም ካለፈው ችግራችን መማር አለበን፡፡ ነገረኛና ተሚጋች ሰው ኢኮኖሚውን ሳይሆን የሚያሳድገው፣ ያኑ ነገሩን ብቻ ነው ሌት ተቀን የሚያስበው፣ የሚያበለፅገውና የሚያሳድገው ፡፡

> *...አርበኙነት በታሪካችን ያልተለየንና የኖርንበት ነው፡፡ ፅንሰ ሀሳቡም እጅግ ሰፊ ነው፡፡ በአርበኙነት ስም ከኛም አልፎ በዓለም ላይ ሕዝቦች "አባት ሀገርህን አድን፣ እናት ሀገርህን ተከላከል" እያሉ ሕዝብን ለጦርነት ሲቀሰቅሱበት፣ አምባገነኖች የሥልጣን ጥማቸውን ሲያረኩበት ኖረዋል...*

ለሀገሩ የመጨረሻና ትልቁን ስጦታ አበረከተ፡፡

የሆነ ሁኖ በጊዜውና በዘመኑ የተሰሩትን መጥፎ ነገሮችና ስህተቶች ማመን፣ ችግሮቹን ነቅሶ ማውጣትና ለትውልድ መመሪያ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ የስው ልጅ ከትናንቱ ዛሬ፣ ከዛሬ ደግሞ ነገ ካልተማረ፣ በከረመው ስህተቱ ካልተፀፀትና ከዚያ ስህተት ልምድ ሀገርና ሁኔታ የደከመ ስርዓት አልነበረም፡፡ አዲስ ሀይል፣ አዲስ ጉልበት፣ በቀላሉ መለየት የማያስችል የተቀላቀለና የተመሳቀለ ርዕዮትዓለም ይዘን ነበር የተገዳደርነው፡፡ ሕዝባችንም ማን ከማን እንደሚሻል መለየት ተቸገረ፡፡ ሲጀመር በጋራ አብረን ተነስተን መንገድ ላይ ተለያየን፡፡ ያውም በአጭር ጊዜ ውስጥ፣ በአንድ የታሪክና የጊዜ ማዕቀፍ

## የአሁኑ ትውልድ አርበኛ ትውልድ መሆን አለበት

አርበኙነት በታሪካችን ያልተለየንና የኖርንበት ነው፡፡ ፅንሰ ሀሳቡም እጅግ ሰፊ ነው፡፡ በአርበኙነት ስም ከኛም አልፎ በዓለም ላይ ሕዝቦች "አባት ሀገርህን አድን፣ እናት ሀገርህን ተከላከል" እያሉ ሕዝብን ለጦርነት ሲቀሰቅሱበት፣ አምባገነኖች የሥልጣን ጥማቸውን ሲያረኩበት ኖረዋል፡፡ በአንደኛውና በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት እነጀርመን ለወረራና ለሀገር ማስፋፋት ሲጠቀሙበት፣ ራሺያ ደግሞ ሕዝቧን አነቃቅታ ከጀርመንና▶

ሌሎች ተስፋፊዎች ሀገሯን አድናለች፡፡ ኢትዮጵያም እንደዚሁ ሰፊ የአርበኝነት ታሪክ አላት፡፡ ቻይና በ1940ዎቹ ከጃፓን ወራሪዎች ሀገሯን ስትከላከል፣ ኢትዮጵያ ከዚያ ትንሽ ቀድም ብላ ከኢጣሊያ ፋሺስት ጋር ስትዋጋ የተጠቀመችበትን ስልትና ጥበብ በትምህርትነቱ ወስዳ ተጠቅማበታለች፡፡ የኢትዮጵያ የአርበኝነት ታሪክ ቢጠና ታላቅና አስደማሚም ነው፡፡ የሆነው ሁኖ ይህ ሀገርን የመከላከል የአርበኝነት ታሪክ ዛሬ በዚህ ትውልድ በሌላ መልኩ መደገም አለበት፡፡ ይህ ትውልድ በከፍተኛ ሀላፊነት ላይ ያለ፣ በመንታ መንገድ ላይ የቆመ፣ በመስራት ወይ ባለመስራት፣ በመኖር ወይ ባለመኖር የሕይወት ግብግብ ላይ ያለ፣ ከመቼውም ጊዜ የበለጠ ሕብረት፣ ዕውቀት፣ መመካከርና አብሮ መስራት፣ ታሪክንም የመለወጥ ሀላፊነት ያለበት ትውልድ ነው፡፡ የአሁን ዘመን አርበኝነት የጦርና የግብግብ አርበኝነት አይደለም፡፡ የአሁኑ ዘመን አርበኝነት የትምህርት፣ የሳይንስና የምርምር አርበኝነት ነው፡፡ የአሁኑ ዘመን አርበኝነት ያለፈውንና ጊዜ የጣለውን፣ የከሸፈውን የአርበኝነት ስህተት መድገም አይደልም፡፡ የአሁኑ ዘመን አርበኝነት መጥፎን ታሪክ መለወጥ ነው፡፡

የአሁኑ ዘመን አርበኝነት ሜዳውን ማረስ፣ ተራራውን መናድ፣ ወንዙን መገደብና ማላመድ፣ ገበሬውን በጥናትና ምርምር መደገፍ፣ ትራክተሩን ማስማራት፣ ፋብሪካውን ማሮጥ፣ በትምህርት መትጋትና በዕውቀት መበልፀግ ነው፡፡ ያልተማረ ትውልድ መንገዱ ሁሉ ጨለማ ነው፡፡ ውጤቱም ርሃብና ድህነት ነው፡፡ መጨረሻውም ነገር፣ ንትርክና ጦር መማዘዝ ነው፡፡ ድንቁርናና ድህነት መንገዳቸው ጭቅጭቅ፣ ጦርነትና ሰላም ማጣት ነው፡፡ ሰላም ማጣት ደግሞ አለመስራትና አለመማር ነው፡፡ የዚህ ውጤቱ ምን እንደሆነ ከሌላ መስማት አይጠበቅብንም፡፡ ከታሪካችን መማር ካልቻልን እድሜ ዓለም ዘለዓለም ድሃና ተመፅዋች ሆነን እንቀራለን፤ ስድባችንም ከኛ አይርቅም፡፡ የኛ ታሪክ ደግሞ ለሚያስተውል ሰው ሁሉ እጂግ አስተማሪ ነው፡፡

አርበኛ ትልውድ ያለፈውን ታሪክ በአስተማሪነቱ ይወስዳል፣ ይገነዘባል፡፡ አርበኛ ትውልድ ታሪክን ያርማል እንጂ የታሪክ እስረኛ አይሆንም፡፡ ትናንት ማታ ወደቤትህ ስትገባ ያደናቀፈህ ድንጋይ ዛሬ ደግሞ ካደናቀፈህ ድንጋዩ አንተ እንጂ እርሱ አይደለም ነው ብሂሉ፡፡ ታሪክና ምሳሌ ለትምህርትና ለግንዛቤ ተፈጠረ እንጂ ለወሬ ማሳመሪያ አይደለም፡፡ የወሬ የለው ፍሬ፣ የአበባ የለው ገለባ ነው ቁም ነገሩ፡፡ ከብሂልና ስድብ ትምህርትና ቁጭት ወስደን ሰው መሆን፣ የጠለሸ ታሪክን መቀየር፣ ወደፊት መመልከትና ሕይወትን መቀየር፣ ራስን ከወደቀበት ፅልመት አውጥቶ ብርሀን ማሳየት፣ በዕውነትና በብርሀን ውስጥ መመላለስ ነው፡፡ ይኸ ነው ሕይወትን ፍለጋ ማለት፡፡ ይኸ ነው ከፅልመት መውጣት ማለት፡፡ የራስን መልካም ታሪክ መስራት ነው በሰው ዘንድ ከበሬታን፣ በዓለም ፊት ኩራትን የሚያጎናፅፈው፡፡ ዛሬ እኛ ኢትዮጵያውያን በዓለም ታሪክ የትህትና፣ የአክብሮት፣ የሀይማኖትና በራስ የመተማመንና በማንነት የመኩራት ምሳሌዎች የነበርነውን ያህል ወደ ጥልቁ ዘቅጠን በባዶ አጥንት እንደሚናከሱ ውሾች እርስ በራሳችን የምንናከስ፣ ትናንት ዓለም በታሪካችን ያከበረንን ያህል ዛሬ የናቀን፣ የደጃችንን ትተን የሌሎችን የምንናፍቅ፣ ለስደትና ለባርነት በርትተን የተሰለፍን፣ ዛሬ በዓለም ፊት በኩራት የምንቆምበት ስራ የሌለን፣ ያልተማርን፣ እንደ ዘመነ ብሉይ በሳርና ውሀ መጋጨት የለት ከዕለት ተግባራችን የሆነ፣ ሰምተንና አንብበን ትምህርት የማንወስድ እጅግ ኋላቀር ሕዝቦች ሆነናል፡፡

እስኪ ንገሩኝ ይህ ዕውነት አይደለም? ይህ የጠቀስኩት፣ ያልኩትና የተናገርኩት ዕውነት አይደለምን? ራሱን በራሱ የማይገስፅ፣ ራሱን በራሱ የማይሰድብ ትውልድ ሌላው ይሰድበዋል፡፡ ከሌላው መማር ቀርቶ በራሱ ግብር፣ በራሱ ችግር ያልተማረ ሰው የሌሎች መሳቂያና መሳለቂያ ይሆናል፡፡ ዛሬ እኛ ለም መሬት ይዘን የምንራብ፣ መልካም አየር ይዘን ከሰማይ ዳቦ የምንጠብቅ፣ በሚሊዮን የሚቆጠር የወጣት ጉልበት ይዘን የማንሰራ፣ የሚለማ ሀብት ይዘን የምንለምን አሳዛኝ ሕዝቦች ነን፡፡ እስኪ አስቡት፤ ከሕዝባችን ምን ያህሉ ነው ሰርቶ ምን ያህሉን ይመግባል? ልሂቆቻችን ጥሮ ግሮ ማደርንና ሰርቶ መበልፀግን ሳይሆን የሚያሰተምሩን መቆራቆስና መነጣጠቅን፣ ጦር መማዘዝንና ሽፍትነትን፣ ሰርቶ ሳይሆን ነጥቆ መብላትን፣ ፍቅርንና አብሮ መስራትን ሳይሆን መገፋፋትን ነው፡፡ አንዲት ጥይት በሰው ላይ ተተኩሳ የሌሎች ብዙ ጥይቶችን ምላሽ እንደምታስከትል መረዳት ማን ይሳነዋል? ጥይት ጥይትን ታስከትላለች እንጂ ሰላምን አታመጣም፡፡ ሰላም ለመስራት፣ ለመማር፣ በዕውቀትና በሀብት ለመበልፀግ የመጀመሪያ ደረጃ መሳሪያ ናት፡፡ ሰላም ሲኖር ጎበዝ ገበሬ ያርሳል፣ ጎበዝ ተማሪ ይማራል፣ ጎበዝ ሳይንቲስት ይመራመራል፣ ጎበዝ ኢንቨስተር ኢንቨስት ያደርጋል፡፡ ሀቀኛ ነጋዴ በሕግ ይነግዳል፣ ሲጠቃለልም ሁሉም ዜጋ አማራጩ ሥራና መስራት ብቻ ይሆናል፡፡ ይህ ሲሆን ዜጎች ራሳቸውን ይችላሉ፣ ከዚያም አልፎ ይበለፅጋሉ፣ ሀገርም ከድህነትና ልመና፣ ከጥገኝነትና ኋላቀርነትም ትላቀቃለች፡፡

ትውልድ ሆይ ቃሌን ልስጥህ አድምጠኝ፣ አንተም ቆም ብለህ አስብ፡፡ እነዚህን የዚያ ትውልድ ትራፊዎች ቃል አትስማ፡፡ መልካሞቹ አልፈዋል፣ ምርጦቹ እፊት ቀድመው ስለሀገራቸው መስዋዕትነትን ተቀብለዋል፡፡ አርበኛ ትውልድ መሆን አለብህ፣ መማር መመራመር ይገባሀል፡፡ መስራት መለወጥ አለብህ፡፡ አርበኝነት ማለት ዛሬ እንደዱሮው ልማድ ምሽግ ይዞ መታኮስ አይደለም፡፡ አርበኝነት ማለት ዛሬ ዲፕሎማሲ ነው፡፡ ከዓለም ጋር መቀላቀል ነው፤ አዎ መቀላቀል፡፡ በሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ በንግድና እርሻ፣ በትምህርትና ስነጥበብ፣ በባህልና ዕውቀት ማደግ ይገባል፡፡ ከዓለም ጋር መቀላቀል ያስፈልጋል፡፡ ለዚህ ደግሞ መጀመሪያ እኛ ራሳችን መቀላቀል አለብን፡፡ ከቀሪው ዓለም ትምህርት ማግኘት፣ ዕውቀት መውሰድ፣ ለሌላውም ዓለም ትምህርት የሚሰጥ ትውልድ መፍጠር ይገባል፡፡ በረባ ባረባ በዘርና በጎጥ ተለያይተህ ስትታኮስ በዕውቀት ወደኋላ ትቀራለህ፡፡ የስራ ጊዜህ በከንቱ ይባክናል፣ በዚህም ምክንያት ድህነት ይጫንሀል፡፡ መጨረሻ አንተም ትጠፋለህ፣ አገርህንም ታጠፋለህ፡፡ እስኪ ቆም ብላችሁ አስቡት፤ ኢትዮጵያ እንዴት ሆና ነው አማራ፣ ትግሬ፣ ኦሮሞ ሱማሌ፣ ወላይታ ሲዳማ ብለን የምንለያያት? እንዴትስ ነው ድንበር የምናበጅላት? ለመሆኑ ወደኋላ ሁለት መቶ ዓመታት እንኳን ሄደን ዘመነ መሳፍንት የነበረበትን ስርዓት ብናይ፣ የሕዝቦች ድንበር ተለይቶ አይታወቅም ነበር፡፡ አንድ ጊዜ ወደ አንድ አቅጣጫ ሲገባ፣ በሌላ ጊዜ ደግሞ ወደሌላ አቅጣጫ ሲጓዝና ሲመሳቀል የኖረ ሕዝብ ያላት ሀገር ናት ኢትዮጵያ፡፡ በድንበሮች አካባቢ የሚኖሩ ሕዝቦች ሁሉም አንዱም ሌላውን ቋንቋ የሚናገሩ፣ የተጋቡና በተለያየ መልኩ የተጋመዱ ናቸው፡፡ አንዱን ከሌላው መለየት የሚያስቸግር፡፡ ይህ የሚያመለክተው ኢትዮጰያውያን በሀገራቸው ውስጥ ድንበር ማበጀት እንደማይችሉ ነው፡፡ የሚገርመው ነገር ደግሞ እኛ ወደሰው አገር ሄደን መስራትና መለወጥ እንፈልጋለን፤ በአገራችን ግን የሀገራችን ሰዎች ከአንዱ ክልል ወደሌላው ሄደው መስራት እንዳይችሉ እናደርጋለን፡፡ ይህ ልንፈታው ያልቻልነው ግራ የሚያጋባ እንቆቅልሽ ነው፡፡


ስለዚህ ሀሳቤን ለማጠቃለል ያህል፤ ተረፈ የ1950/60ዎቹ ትውልድ ግማሾቹ በኢሰፓ፣ ግማሾቹ በመኢሶን፣ ግማሾቹ ደግሞ በኢህአፓ፣ በሌላም፣ በሌላም ስር ተደራጅተው በዚያን ዘመን ለስልጣን ሲተናነቁ ኖረው አልሆንላቸው ሲል፣ ወደዘር ፖለቲካ የተሸጋገሩ፣ ዛሬም ስልጣንና ስልጣንን ብቻ የሚያነፈንፉ፣ በወንዜ ልጅና በጎሳየ በሚል ተደራጅተው ይህን ትውልድ መሳሪያ ሊያደርጉት በመቶ ፓርቲዎች ተደራጅተው በየማዕዘኑ ይንጫጫሉ፡፡ ኢትዮጵያን መቼም በዓለም ታሪክ ተወዳዳሪ የሌላት በፖለቲካ ፓርቲዎች ብዛት በዓለም አንደኛ የሆነች አገር አደረግናት፡፡ በዚህም ለነገር የተጉ፣ ለስራ ግን የዘነጉ ልሂቃን አገር አደረግናት፡፡ ይህ ግን ምን ጥቅም አለው? የኛ አገር የፖለቲካ ፓርቲ መብዛት ምን ጥቅም ይሰጠናል? አርሰው አያበሉን፡፡ ይልቁንም አርሶ የሚያበላን ገበሬ ቢበረታ፣ ዕሴት የሚጨምር ፋብሪካ ቢበዛ፣ የምናርስበት ትራክተር ቢበረክት ምን ያህል ታላቅ በሆንን ነበር! ይህ እንዲሆን ግን የሚጠይቅ ትውልድ፣ የሚማርና የሚመራመር ትውልድ፣ ጥቅሙንና ጉዳቱን በራሱ አውቆና ተረድቶ የሚሰራ፣ የራሱ ራዕይ ያለዉ፣ ራዕዩን ወደ ድርጊት የሚቀይር ትውልድ ያስፈልገናል፡፡

ስለዚህ ለዚህ ትውልድ ያለኝ መልዕክት ዘመኑ የእናንተ ነው፡፡ የወደፊቱም ዘመን የእናንተ የሰራ ውጤት ነውና ራሳችሁን በትምህርት፣ በእውቀትና በስራ ባህል አሳድጉ፡፡ ለሥራ ትጉ፣ ቱታ ለብሳችሁ ቡት ተጫምታችሁ እርሻ እረሱ፣ ግብርና በዘመናችሁ ሁሉ ወሳኝ የኢኮኖሚ አውታር ነውና፡፡ ሰላማችሁን ጠብቁ፣ ፖለቲካን ቀንሱ፣ ጥናትና ምርምር ላይ በርቱ፡፡ በፖለቲካ ንፋስ አትወሰዱ፣ ሀገራችሁን ውደዱ፣ እርስ በራሳችሁ ተዋደዱ፣ የራሳችሁን ታሪክ ስሩ እንጂ የሌሎች ተቀጥላ አትሁኑ፤ የዘመናችሁ አርበኛ ሆናችሁ እለፉ፣ የአገራችሁንም ታሪክ ቀይሩ፡፡

***ኢትዮጵያ በዜጎችዋ ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!***

ምልከታ

# ለአንድ አገር የሚጠቅመው የጋራ፣ የግል፣ ወይስ የቡድን የበላይነት?



መታሰቢያ መልአከ ሕይወት

የሰው ልጆች ከእናታችን ማሕፀን ከወጣን ጀምሮ የጋራ የምንለው ፍላጎት አለን። ይህ ፍላጎት መብላት፣ መጠጣት፣ ንፁህ አካባቢ መኖር እና ሌሎችንም ያካትታል። ሁለተኛ በግለሰብ ደረጃም መከበር የሚገባቸው በርካታ ፍላጎቶች አሉ፤ ከእነዚህም በጥቂቱ ሰብዓዊ፣ ቁሳዊና፣ መንፈሳዊ መብቶች ሲሆኑ፤ ሌሎችም በየደረጃው በግለሰብ ደረጃ ሊነሱ የሚችሉ የመብት ጥያቄዎች ይኖራሉ።

በሶስተኛ ደረጃ በወል ወይም በቡድን ሰዎች ተሰባስበው የሚጠይቋቸው የመብት አይነቶች አሉ። ከእነዚህም በቋንቋ የመናገር፣ የጋራ ባሕላዊ እሴቶችን መጠበቅ ወዘተ የመሳሰሉና ሌሎች በርካታ ጉዳዮች ሊነሱ ይችላሉ። ይህ የቡድን ጥያቄ ወይም መብት የብሔር፣ የሐይማኖት ስብስቦች፣ የርዕዮተ አለም የጋራ ስብስቦች ወይም ሌሎች ሊሆኑ ይችላሉ።

ነገር ግን አንድ አገር የጋራ የሆነውን የሰው ልጆች ፍላጎት የበላይ አድርጋ ሁሉንም የአገሪቱን ዜጎች ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት ካልቻለች ወይም በሌላ አነጋገር፣ የግለሰብን ወይም የቡድንን ፍላጎት የበላይ አድርጋ ከተንቀሳቀሰች የሚጠብቃት ውድቀት ብቻ ነው።ምክንያቱም የቡድን ፍላጎት ማለቂያ የለውም። አንዱን ለመመለስ ሲሞከር ሌላው "እኔስ" ይላል። ወይም በማግስቱ ሌላ ቡድን ይፈጠራል።

አንዱ ቡድን ሥልጣን ላይ ሲወጣ የራሱን የቡድን አባላት ተጠቃሚ ለማድረግ ሲሯሯጥ፣ ሌላው ቂም አዝሎ ስልጣን የያዘውን ኃይል ለመበቀል ወይም የራሱን የበላይነት ለመፍጠር ይንቀሳቀሳል። በዚህ መሀል የጋራ የሆነው የአገር ልማት እና የጋራ ዕድገት ተገቢውን ትኩረት ማግኘት ያቅተዋል። የዛሬ 28 ዓመት ጀምሮ ሥልጣን የያዘው ኢህአዴግ የቡድንን ፍላጎት ከምንም በላይ ለማስተናገድ በመስራቱ አሁን ድረስ በችግር ውስጥ ለመኖር ተገደናል።

በተለይ ደግሞ የሐይማኖት ቡድን ፈጥ ረው፣ በርካታ ተከታዮችን አስከትለው፣ አስፈሪ መስለው የቀረቡትን ቡድኖች ከአገሪቱ አቅም በላይ ልዩ ትኩረት በመስጠት (ለስልጣኔ አደጋ ናቸው ብሎ ስለሚያስብ) ልዩ እንክብካቤ በማድረግ የጋራ የሆነውን ሐብት ሁሉ በማባከን፣ በአገር እና በጋራ ልማት ላይ አሉታዊ ተግባር ፈፅሚል።

በአገራችን ተመስርተው "አለሁ አለሁ" የሚሉት የፖለቲካ ፓርቲ ተብዬዎች በአመዛኙ የቡድን ፍላጎትን ይዘው ቤተ መንግስት ለመግባት የሚሯሯጡ ሐይሎች ናቸው። የቡድን በተለይ የብሔር ርዕዮተ ዓለም በሌለበት ሁኔታ ዩኒቨርሳል የሆነውን የፖለቲካ አስተሳሰብ ማራመድ ሲገባቸው፣ የብሔር ስም ይዘው "የፖለቲካ ፓርቲ ነን" ብለው መነሳታቸው በምንም መልኩ ተቀባይነት የለውም። መንግስትም በምንም መልኩ ለእነዚህ ዕውቅና መስጠት የለበትም።

በአገራችን ደቡብ ኢትዮጵያ የሚደረገው የልማት ተግባር፣ ሰሜን ኢትዮጵያ ያለው ዜጋ "የኔ ልማት ነው" ብሎ ማሰብ ካልቻለ በአንድ ክልል የሚደረግን የልማት ስራ ያ ልማት "የነ እንትና እንጂ ለኔ ምኔ ነው?" የሚል አስተሳሰብ በየጊዜው እየተጠናከረ ከሄደ፤ አገራዊና የጋራ አጀንዳ በየጊዜው እየተሸረሸረ መምጣቱ ግልጽ ነው።

ይህ ብቻ ሳይሆን ለምሣሌ በትግራይ ውስጥ የትግሬዎች የአንድ ብሄር የበላይነት የሚንፀባረቅ ከሆነ፣ በሱማሌም፣ በአማራም በኦሮሚያም ወዘተ በእንደዚህ ዓይነት ቦታዎች ኢትዮጵያዊነት ፈልጎ ማግኘት አስቸጋሪ ከሆነ፣ ለልማትም ለብልፅግናም ከፍተኛ እንቅፋት ተፈጠረ ማለት ነው።

> ...አዲስ አበባ ውስጥ አንድ ሰው እንኳን አማርኛ ቋንቋ መናገር ችሎ በምልክት ቋንቋ እንኳን እያወራ ሠርቶ ሐብት ማፍራት ይችላል፡፡ ከየት መጣህ? ዘርህ ምንድን ነው? የሚሉ ኋላ ቀር ጥያቄዎች አይቀርቡለትም...

አንድ ነግዶ ሐብት ማፍራት የሚፈልግ ሰው ገንዘቡን አውጥቶ መሥራት የሚፈልገው የቡድን የበላይነት የማይንፀባረቅበት ቦታ ነው፡ ፡ ምክንያቱም በብዙ መመዘኛ አትራፊ የመሆን ዕድሉ ከፍተኛ በመሆኑ። አዲስ አበባም በከፍተኛ ፍጥነት ማደግ የቻለችው የቡድን ሳይሆን የጋራ ፍላጎት የሚንፀባረቅበት ብቸኛ ደሴት በመሆንዋ ነው። የቡድን የበላይነት ባለበት ቦታ እንኳን ነግዶ ማትረፍ በሰላም ወቶ መግባት እጅግ አስቸጋሪ እየሆነ እንደመጣ ማንም ሊመሰክረው የሚችለው እውነት ነው።

በኢትዮጵያ ያሉ የቋንቋ ስብስቦች ቋንቋቸው አድጎ በቂ መጽሐፍት እንኳን ማግኘት በማይቻልበት ሁኔታ በቋንቋቸው ተሰባስበው በመገኘታቸው ብቻ በርካታ ጥቅሞችን እና ኢንቨስትመንትን እንዳጡ ቶሎ ቢገባቸው የተሻለ ይመስለኛል።በተለይ ወጣቱን ትውልድ "በአፍ መፍቻ ቋንቋህ ተጠቀም" እያሉ ሌላ ቦታ ተዘዋውሮ ዝቅተኛ የተባለ ሥራ እንኳን ሠርቶ እንዳይኖር እያደረጉት በመሆኑ ይህ ጉዳይ ፈጣን እርምት የሚፈልግ ጉዳይ ነው።

ባለፉት 50 ዓመታት እጅግ ፈጣን ዕድገት ያሳዩ እንደ ኮሪያ ቻይና ያሉ አገራትን ታሪክ ብናጠና የምናገኘው እውነታ ሁሉም ለጋራ ጥቅም ከምንም በላይ ተግተው መሥራት በመቻላቸው ነው ለታላቅነት የበቁት።ከላይ እንደተጠቀሰው የቡድን ፍላጎት መጀመሪያ እንጂ መጨረሻ የሌለው፣ የጋራ ልማትን የሚያቀጭጭ፣ አርቆ የማሰብ ብቃት እጥረት ውጤት ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል።

ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በማንኛውም ቦታ እራሱን ፈልጎ ማግኘት፣ በምንም መልኩ ሊከብደው አይገባም። እዚህ አዲስ አበባ ውስጥ አንድ ሰው እንኳን አማርኛ ቋንቋ መናገር ችሎ በምልክት ቋንቋ እንኳን እያወራ ሠርቶ ሐብት ማፍራት ይችላል። ከየት መጣህ? ዘርህ ምንድን ነው? የሚሉ ኂላ ቀር ጥያቄዎች አይቀርቡለትም።

በተቃራኒው በክልሎች እንኳን የክልሉ ተወላጅ ያልሆነ ሰው ለፌደራል መንግስት እንኳን በተገቢው መልኩ ተንቀሳቅሶ ለመስራት አስቸጋሪ የሆነ ቦታ እንደሆነና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከረ እንደመጣ መመልከት በእጅጉ ቀላል ነው።የፌደራል ሥርዓት በመመስረት ቀዳሚ እንደሆነች የሚነገርላት አሜሪካ የፈጠረችው የፌደራል ስርዓት በአመዛኙ ጆግራፊያዊ ሲሆን ሕዝቦቿ በአግባቡ መልካም አስተዳደር እንዲያገኙ ከማስቻሉም በላይ የአለም ታላቅ መንግስት እንድትሆን አስችሏታል።

አሜሪካኖች እንኳን አሜሪካ ውስጥ ከአሜሪካ ውጭ የሚደረግ ማንኛውንም የመንግስታቸውን እንቅስቃሴ እንደራሳቸው ▶

መብት ስለሚያዩት በማንኛውም ጊዜ ለፌደራል መንግስት ውሳኔ ተባባሪ እንጂ ችግር ፈጣሪ መሆን አይፈልጉም።እኛ አገር አንድ ቡድን ስልጣን ይዞ የራሱን ቡድን አባላት ከሚገባው በላይ ተጠቃሚ ለማድረግ ይጥራል እንጂ የጋራ የሆነውንና ኢትዮጵያዊ አጀንዳ ላይ ተግቶ ሲሰራ አይታይም።

እዚህ ላይ አንድ ምሳሌ ልጥቀስ። ሕወሓት/ ኢህአዴግ ሥልጣን ላይ በነበረበት ወቅት ለትግራይ ሕዝብ ምንም ጥቅም የማይሰጥ ነገር ግን ስግብግብነት በሚመስል መልኩ አንድ የሰራው ሥራ አለ። አክሱም ከተማ አጠገብ እንደሚታወቀው ኤርፖርት አለ፤ ይህ ኤርፖርት መገንባቱ በእጅጉ ተገቢ ነው። ነገር ግን በጣም የሚገርመው ከአክሱም የአንድ ሠዓት መንገድ ላይ የምትገኘዋ ሽሬ ከተማ ሌላ ኤርፖርት እንዲገነባ ተደርጓል። ይህ በእውነቱ የገንዘብ ብክነት እንጂ ምንም ፋይዳ የለውም። በተቃራኒ እንደ ጎሬ ያሉ ጥንት ኤርፖርት የነበራቸው ቦታዎች አሁን ኤርፖርት አልባ ሆነዋል፤ ይህ የሚያሳየን የቡድን ስሜት ውጤት ነው።

አንድ ቡድን ሥልጣን ላይ ሲወጣ የሚጠቅም ብቻ ሳይሆን የማይጠቅምም ተግባር በስግብግብነት ስሜት መስራት ሌሎችን እንደሚያስቀይም መገንዘብ ተገቢ ይመስለኛል።በአሁኑ ወቅት የተለያዩ ሰላማዊ ሰልፎች ላይ የሚንፀባርቀው መፈክር በአመዛኙ የቡድን ፍላጎትን የሚያሳይ ነው፡ ፡ "እኛጋ የኢንዱስትሪ መንደር ይገንባልን? ኤርፖርት ይሰራልን?" የመሳሰሉ ጥያቄዎች ሌላ ቦታ ኢትዮጵያ ውስጥ የተሰራውን ሥራ እንደ ራስ ካለመቁጠር የመነጨ አስተሳሰብ ውጤት ነው።

በአለማችን ትልቅ ጥቁር ነጥብ ጥሎ ያለፉ ታሪኮችን ብንመለከት፣ በአመዛኙ የቡድን ፍላጎትን በጋራ ፍላጎት ለመለወጥ የተደረጉ ትግሎችን እናገኛለን።በደቡብ አፍሪካ ነጮች የበላይ በነበሩበት ወቅት የቡድን የበላይነት ተንፀባርቆ የነበረበት ወቅት ነበር። ይህንን ሥርዓት ለመለወጥ ብዙ መስዋዕትነት ተከፍሎአል።ይህ ስርዓት ከተወገደ በኋላ አገሪቱ ከዓለም ማህበረሰብ በመቀላቀሏ ከፍተኛ እመርታ ማስመዝገብ ችላለች።

እዚህ ላይ ሁላችንም ልንገነዘበው የሚገባ ጉዳይ አሁንም የቡድን ፍላጎት በማዕከላዊ መንግስት ደረጃም እየተንፀባረቀ እንደሆነና ይህ ሁኔታ ሁሉም ኢትዮጵያዊ የማዕከላዊ መንግስት ውስጥ በቂ ውክልና አለኝ የሚል ስሜት እንዲኖረው ሥልጣን የያዘው ኃይል ተግቶ መሥራት አለበት።የዚህ ፅሁፍ አቅራቢ የቡድን ፍላጎት ይደምሰስ ወይም ትኩረት ይነፈገው ማለቱ እንዳልሆነ ማንም ሊገነዘበው ይገባል።

በተጨማሪም በአንዳንድ አገሮች በተለያዩ ታሪካዊ ምክንያቶች የአንድ ሐይማኖት ቡድን በቋሚነት የበላይ ሆኖ ያለበት ሁኔታ እንዳለ እንገነዘባለን። በተለይ በተፈጥሮ ሐብት የታደሉ የአረብ አገሮች የነዳጅ ሐብታቸው እስካለ ድረስ ይህንን አሰራር ሊቀጥሉበት ይችላሉ። ነገር ግን ከመላው አለም አስተሳሰብ ጋር እራሳቸውን አዋሕደው መኖር የሚገደዱበት ወቅት ሲመጣ የግድ ዓለም አቀፋዊን አስተሳሰብ ለመከተል ይገደዳሉ።

እኛ ኢትዮጵያውያን ከአቅማችን በላይ የቡድንን አስተሳሰብ ቦታ በመስጠታችን ለጋራ ኢኮኖሚያችን በቂ ትኩረት እየሰጠን አይደለም። ኢኮኖሚው በተፈለገው ፍጥነት እየሄደ በውጭ ንግድ እንኳን እድገት ሳናስመዘግብ በብዙ ዘርፎች የኋሊት ጉዞ ላይ ነን።የወጣቱ ቁጥር ደግሞ እየጨመረ ነው፤ የውጭ እዳችንን መክፈል አቅቶን አጣብቂኝ ውስጥ ገብተናል። ሌሎችም በርካታ ችግሮች ከበውናል።

እኛ ግን አሁንም በግትርነት የቡድንን የበላይነት ይዘን እየተጓዝን ነው። የውጭ ባለሐብቶች በተለይ በማዕድን ዘርፍ የተሰማሩ ካምፓኒዎች በቂ የማዕከላዊ መንግስት ጥበቃና አገልግሎቶች እያገኙ ባለመሆኑ በማዕድን ዘርፍ ኢትዮጵያ ምንም አይነት እድገት አላሳየችም።የማዕድን ሐብት ደግሞ ሁሉም ሊባል በሚችል መልኩ የሚገኘው የቡድን የበላይነት ባለባቸው አካባቢዎች ነው። አሁንም ቢሆን በእነዚህ አካባቢዎች የጋራ የበላይነት ካልተፈጠረና የፌደራል መንግስት (በአለም አቀፍ ማህበረሰብ እውቅና ያለው) የበላይነቱን ማሳየት ካልቻለ በማዕድን ዘርፍ በቅርብ ጊዜ ውጤት እናስመዘግባለን ብዬ አላምንም።

በየክልሉ አምባገነን የሆኑት ቡድኖች የራሳቸው ስልጣን እንጂ የሕዝቡ ተጠቃሚነት እምብዛም አያሳስባቸውም። በተጨማሪም በዓለም አቀፍ ማህበረሰብ እውቅና ስለሌላቸው የሚፈልጉትን የልማት ሥራ የፌደራል መንግስት ብቻ ነው ሊሰራላቸው የሚችለው። እነዚህ ቡድኖች በፌደራል ሥራ ጣልቃ እየገቡ ችግር ሲፈጥሩ በየጊዜው ይስተዋላል።

በመጨረሻም በአንድ አገር ውስጥ የጋራ ፍላጎት፣ ከዚያ የግለሰብ ፍላጎት፣ በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ የቡድን ፍላጎት በቅደም ተከተላቸው መሰረት መስተናገድ ካልቻሉ መጨረሻው ውድቀት ብቻ ነው የሚሆነው፡ ፡ ከላይ እንደተጠቀሰው እጅግ ውጤታማ ዕድገት ያስመዘገቡና በሰላም ከሚኖሩ እንደ እስካንድኔቪያን አገሮች የምንማረውም ይህን ነው። እንደ አሜሪካ ባሉ አገሮች ደግሞ የግለሰብ መብት ጎልቶ የሚታይ በመሆኑ እዚያም አንዳንድ ችግሮች አሉ። እኛ ግን ወደ ዕድገትና ሰላም የግድ መሸጋገር ስላለብን የግድ የጋራን ፍላጎትና ጥቅም ማስቀደም አለብን፡ ፡ የክልሎች ስልጣንም የግድ በሕገ መንግስቱ ላይ ከፌደራል መንግስት በታች እንጂ የበላይ መሆን የለበትም። ምክንያቱም አለም አቀፍ እውቅና ሳያገኙ የበላይ ሥልጣን ሊኖራቸው አይችልም፤ ይህንን ስራ ለመስራት ጊዜ መባከን የለበትም።

**...እኛ ኢትዮጵያውያን ከአቅማችን በላይ የቡድንን አስተሳሰብ ቦታ በመስጠታችን ለጋራ ኢኮኖሚያችን በቂ ትኩረት እየሰጠን አይደለም...**

እኔ በግሌ በጣም የሚያሳስበኝ ጉዳይ እኛ ኢትዮጵያውያን በርካታ መስዋዕትነት ከፍለን አገራችንን ከቅኝ ገዥዎች ጠብቀናታል፤ ብዙ የአፍሪካ አገሮች ቅኝ ግዛት ካቆመ በኋላ የነጮች የበላይነት በተለይ በኢኮኖሚው ላይ በስፋት ይስተዋላል። እኛ ግን ከወራሪዎች የጠበቅነውን አገር የአገሪቱን ዜጎች ተጠቃሚ ማድረግ የቻለ የኢኮኖሚ ዕድገት ማምጣት አልቻልንም። በተለይ በግድ ከኢትዮጵያ ግዛት እንዲቀላቀሉ የተደረጉ ሕዝቦች በተለያዩ ምክንያቶች አጥጋቢ ዕድገት ማሳየት አልቻሉም።

በአንድ አገር ከነፃነት ማግስት ብልፅግና ካልመጣ ሕዝቦች ባዶ ነፃነት ብቻ እንደ ግብ አድርገው አይወስዱትም።ኢትዮጵያ ውስጥ በርካታ የሐይማኖት፣ የብሔር፣ የጎሳ ቡድኖች አሉ፤ እነዚህን ቡድኖች በአሁኑ ሥርዓት ከአቅማችን በላይ ለማስተናገድ በመሞከራችን የጋራ አጀንዳችን የሆነውን የአገር ልማት በበቂ ፍጥነት ማራመድ አልቻልንም።

ለምሣሌ ቻይናውያን፣ ሃይማኖታዊ ቡድኖችን አሉ ሊባሉ በማይችሉበት ደረጃ በማድረሳቸው ሙሉ ትኩረታቸውን ለጋራ ልማት ለማዋል አስችሎአቸዋል። ቻይና የግለሰብን የኢኮኖሚ መብት በማክበር በኩል ባለፉት 30 ዓመታት አጥጋቢ ውጤት ማስመዝገብ ብትችልም የግለሰብን የዴሞክራሲ መብት በማክበር በኩል ገና ጉዞ አልጀመረችም፡ ፡

አፍሪካን ቅኝ የገዙ ኃይሎች አፍሪካ ውስጥ ያሉትን የቋንቋ ቡድኖች ለማጥፋት ወይም ለማዳከም የተሳካ ስራ በመስራታቸው ዛሬ ሁሉም ሊባል በሚችል መልኩ ቅኝ የተገዙ የአፍሪካ አገራት ለጋራ ዕድገታቸው ነው እየሰሩ ያሉት።እኛ ግን ቅኝ ስላልተገዛን የቋንቋ ቡድኖች ተጠብቀው በመቆየታቸው አሁን ልንሸከመው ከምንችለው በላይ የቤት ስራ ሆኖብናል። በዚህ ምክንያት የቡድን ፍላጎትን ለማሟላት የሚባክነው ጊዜና ገንዘብ የጋራ ልማትን ለማምጣት በሚደረገው ትግል ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ መፍጠሩ የግድ ነው።

በአለማችን ልዩነትን መጨፍለቅ የቻሉ አገሮች ለምሣሌ እንደ አሜሪካ፣ ብራዚል፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ካናዳ የመሣሠሉ አገሮች ያላቸውን አቅም ሁሉ ተጠቅመው ለጋራ ልማት ስለሚሰሩ ባሁኑ ጊዜ እጅግ አመርቂ እድገት ባለቤት ናቸው። አንዳንዴ የቡድን ፍላጎትንና የጋራ ፍላጎትን አንድ ላይ ለማስኬድ መሞከር ፍየልና ነብር በአንድ ጆልባ ለማጓጓዝ እንደመሞከር ነው። ባንድ ወቅት ጠ/ሚ/ር ዐቢይ ሲናገሩ "መደመር ማለት መጨፍለቅ ማለት አይደለም" ብለው ነበር፤ ይህ አባባል በጭራሽ ትክክል አይደለም። እርግጥ መጨፍለቅ የ50 — 100 አመት የቤት ሥራ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን የመጨረሻ ግብ ሆኖ መወሰድ አለበት? በመሆኑም ሁላችንም በዚህ አቅጣጫ የሚወስደን ሕገ መንግስታዊ ሥርዓት ዘርግተን የ21ኛው፣ ክፍለ ዘመን ተጠቃሚ ለመሆን ብንተጋ የተሻለ ነው የሚል ሐሳብ አለኝ።

# የቅዱስ . . .

◀ ከገጽ 12 የዞረ

የአብያተ ክርስቲያናት መቃጠል፣ የክርስ ቲያኖች መገደልና ከቂያቸው መፈናቀል፣ በሃይማኖታቸውና በሃይማኖታዊ ሥርዓታቸው ላይ ተጽዕኖ ማድረግ፣ የአብያተ ክርስቲያናት ነባር የይዞታ ቦታዎችን በሕገ ወጥ መንገድ መቀማት፣ የሚሉትና የመሳሰሉት ጥቃቶችና ጫናዎች እየደረሰብን እንደኾነ ያስረዳው መግለጫው፣ የፌዴራሉ መንግሥት፣ ኢትዮ ጵያንና ሕዝቧን በፍትሕ ርትዕ ይመራሉ ብሎ ላስቀመጣቸው የዞንና የወረዳ አስተዳዳሪዎች ኹሉ አስፈላጊውን መመሪያ እንዲሰጣቸው ጠይቋል፡፡

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚማሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታዮች፣ በሥርዐተ እምነት ነፃነታቸው ላይ የሚደርስባቸው ጫና ተወግዶ ሕገ መንግሥታዊ መብታቸው እንዲከበር አሳስቧል፡፡ እንደ እምነታቸው ሥርዐት፣ በዓመት ባሉት ሰባት አጽዋማት፣ የመጾም መብታቸው ተጠብቆ አስፈላጊው አቅርቦት እንዲደረግላቸው፣ ሃይማኖታዊ በዓላትንም በሚያከብሩባቸው ጊዜያት፣ የኖረና የቆየውን ትውፊታዊ አልባሳት የመልበስ መብታቸው እንዲጠበቅ፣ ለየኮሌጆቹና ለየዩኒቨርሲቲዎቹ ማሳሰቢያው እንዲደርሳቸው መወሰኑን አስታውቋል፡፡

ለተዘጉ አብያተ ክርስቲያናት፣ ለአብነት ት/ቤቶች፣ ሰው ሠራሽ አደጋ ለደረሰባቸው አብያተ ክርስቲያናት፣ ለተፈናቀሉ ወገኖች፣ ለጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት ሕንፃ ማደሻ የሚኾን የገንዘብ ድጋፍ ማድረጉን ገልጿል፡፡

በቅዱሳት መጻሕፍት ኹሉ የተወገዘው ግብረ ሰዶም፣ ዜጎች በቅድስናና በፈሪሃ እግዚአብሔር ተከብረው የሚታወቁባትን የአገራችንን ታሪክ የሚቀይር፣ የዜጎችን መልካም ሥነ ምግባር የሚለውጥ፣ ሕገ ተፈጥሮንና የተቀደሰውን ጋብቻ የሚያበላሽ እንደኾነ መግለጫው አትቷል፡፡

ይህን ነውረኛ፣ ውጉዝና የወንጀል ተግባር፣ በአገራችን ለማስፋፋት፣ በዚህም የቅድስት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ቅድስና የሚጎዳ ተግባር ለመፈጸም፣ መቀመጫውን በአሜሪካ ያደረገው የግብረ ሰዶማውያን አስጎብኚ ድርጅት ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት ማስታወቁን ቅዱስ ሲኖዶሱ ተቃውሟል፤ ቅዱሳት መካናትንም እንዳይጎበኝ አውግዟል!!!

ቅዱስ ሲኖዶሱ አያይዞም፣ ላልተወሰነ ጊዜ በተራዘመው 4ኛው ዙር የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ፣ ካህናትና ምእመናን፣ በምልአትና በትክክል እንዲቆጠሩ በየአህጉረ ስብከቱ ሊሰጥ የሚገባውን ትምህርትና ግንዛቤ አፈጻጸም የሚከታተል ኮሚቴ በጠቅላይ ጽ/ቤቱ መሠየሙን በመግለጫው አስፍሯል፡ ፡ "መንግሥት፣ ዜጎች እንዲቆጠሩ በያዘው መርሐ ግብር መሠረት፣ የቤተ ክርስቲያኒቱ ተከታዮች በትክክል እንዲቆጠሩ፣ ቆጠራውም በሰላም እንዲከናወንና አገራዊ ተልእኮውም እንዲሳካ፣ በየአህጉረ ስብከቱ ትምህርት እንዲሰጥ፣ አስፈላጊውም ክትትል እንዲደረግ የኮሚቴ አባላት እንዲሠየሙ ተደርጓል፤" ብሏል መግለጫው፡፡

በውጭ አገር የሚገኙ አህጉረ ስብከትን በማጠናከር መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎታቸውን ማስፋፋት እንዲቻል፣ ከቃለ ዐዋዲው እና ከየአገሮቹ መንግሥታት ጋራ የተጣጣመ ደንብ እንዲዘጋጅና ለጥቅምቱ 2012 ምልአተ ጉባኤ እንዲቀርብ መወሰኑን መግለጫው ጠቅሷል፡፡

የቋሚ ሲኖዶስ ሥልጣንና የሥራ አፈጻጸም አስመልክቶ ተከሠቱ በተባሉ የሥራ አፈጻጸሞችና ታዩ በተባሉ ግድፈቶች፣ ጉባኤው በሰፊው ተነጋግሮ፣ በቀጣይ ማንኛውም መንፈሳዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች ሕገ ቤተ ክርስቲያንን መሠረት አድርጎ እንዲሠራ መመሪያ ሰጥቷል፡፡ በዚህ የመግለጫ ነጥብ፣ ኹነኛ የጉባኤው ማሳያ የነበረው፣ የመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ውዝግብ ነው፡፡ በቋሚ ሲኖዶሱ የተወሰነው፣ የኹሉም ወገኖች አቤቱታ ሳይታይና የሀገረ ስብከቱ ሚና ሳይጠየቅ፣ በአጠቃላይ የቅሬታ አቀራረብ(ይግባኝ) ሥርዓቱ ሳይጠበቅ በመኾኑ፣ ዳግም ወደዚያው ተመልሶ አፈጻጸሙ እንዲታይ ተስማምቷል፡፡

ከአገር ውስጥ፥ የከፋ፣ ከውጭ አህጉረ ስብከት የደቡብ አፍሪቃ፣ የኢየሩሳሌም ገዳም፣ የአትላንታ ሰዓሊተ ምሕረት ቅድስት ማርያም እና የፊላዴልፊያ ቅዱስ ዐማኑኤል አብያተ ክርስቲያናትን በተመለከተ፣ በአጣሪ ልኡካን የቀረቡ ሪፖርቶችን ተመልክቶ፣ "መፍትሔ የተባለ ውሳኔ" ቅዱስ ሲኖዶሱ መስጠቱን በመግለጫው አስታውቋል፡፡

እውነታው ግን፣ ውሳኔዎቹ፣ ፍጹም መፍትሔ ሊኾኑ አለመቻላቸው ነው!!! ከውሳኔዎቹ አንዳቸውም፣ አቤቱታ አቅራቢ ወገኖችን እንዳላስደሰቱ፣ ለተጨማሪ ውዝግብና ለምእመናን መራቅ ምክንያት እንዳይኾኑ ስጋት የሚፈጥሩ ናቸው፡፡ ይልቁንም፣ "ቤተ ክርስቲያን የጳጳሳት ብቻ ናት ወይ?"፤ "አባትነት ወይስ አገዛዝ?"፤ "ከሲኖዶሳዊ አንድነት ወደ ሲኖዶሳዊ ማጥራት መቼ?" የሚሉ ጥያቄዎችን በብርቱ እያስነሡ ያሉ መኾናቸው ነው፣ እውነታው!

አዲስ አበባን ጨምሮ በየአህጉረ ስብከቱ ያለው የቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ ችግር፣ አካል ገዝቶ መልክ አውጥቶ በዐደባባይ ገንፍሎ እያመሰን፣ ከቫይረስ የረቀቀ ይመስል ዐሥሬ ይጠና እየተባለ፣ ተጠንቶ ልሞና ደቆ የቀረበውና በመሳቢያ የተቆለፈበት የለውጥ ሰነድ፣ በአማሳኞች ተንኰልና ዛቻ እንዲሰወር፣ መፍትሔው ኾነ ተብሎ እንዲዘገይና እንዲርቅ እየተደረገ ያለበት ኹኔታ፣ በዚኹ የምልአተ ጉባኤ ስብሰባ ላይ በግልጽ ተንጸባርቋል፡፡

• ከጥቅምት 2006 ዓ.ም. ጀምሮ ኹለንተናዊ ችግሩን ከነመፍትሔው ፍንትው አድርገው የሚያሳዩ ከአንድም ሦስት መሠረታዊና ጥልቅ ጥናቶች እያሉና እኒህም ከወቅቱ ጋራ ተጣጥመውና በበጀት ተደግፈው እንዲተገበሩ ምልአተ ጉባኤው በተደጋጋሚ አጽድቋቸው እያለ፣ እንደገና ሌላ የጥናት ማደንዘዣ የታዘዘበት፣ እንደገና ሌላ የኮሚቴ ድሪቶ ያየንበት መደበኛ ስብሰባ ነው፣ ይህ የ2011 ግንቦት የርክበ ካህናት ምልአተ ጉባኤ!!!

• የአስተዳደራዊ ለውጥን አስፈላጊነት በተሻለ ኹኔታ ይረዳሉ፤ በሠለጠነ አገርም እንደ መቆየታቸው በትግበራው ይደግፋሉ ተብለው ተስፋ የተጣለባቸው የውጭ ገቦችም ምንተ ዕዳዬ ያሉበት ይብሱኑ አንዳንዶቹ ለኑፋቄና ለተወገዙ መናፍቃን ሽንጣቸውን ገትረው ጉባኤውን ያለከልካይ የሞገቱበት አሸማቃቂ መደበኛ ስብሰባ ነው፣ ይህ ምልአተ ጉባኤ!!!

• የገዛ ውሳኔውን እንኳ ማስታወስና ማስከበር ተስኖት፣ ሃይ ባይ ላጣው ፓትርያርካዊ ዓምባገነንት የተጎናበሰ ምልአተ ጉባኤ ነው፣ ይህ የቅዱስ ሲኖዶስ መደበኛ ስብሰባ!!!

• ከመርሕና የርእሰ ጉዳይ ጭብጥ፣ የኹሉ አባትነትና ሚዛናዊነት ይልቅ የጎሠኝነት መደጋገፍና መነቃቀፍ በየአጀንዳው በግላጭ የታየበት ምልአተ ጉባኤ ነው፣ ይህ የርክበ ካህናት ቅዱስ ሲኖዶስ መደበኛ ስብሰባ!

• በተለይም፣ በአነጋጋሪ አጀንዳዎች፣ የድጋፍና ተቃውሞ ወሳኝ መነሻ በነበረው የዋና ጸሐፊ እና የዋና ሥራ አስኪያጅ የምርጫ አጀንዳ ላይ እንዳፈጠጠ፥ በአዳራሽና በውጭ፣ በገሃድና በኅቡእ እርስ በርሱ እየተሻኮተ ሰንብቶ፣ምርጫው ከተከናወነ በኋላና በማግሥቱ ደግሞ፣ የመሪ ዕቅድ ትግበራን ያህል የህልውና አጀንዳ ላይ ለመነጋገር መንፈሳዊ ወኔ የከዳው ግዴለሽነት የታየበት ምልአተ ጉባኤ ነው፣ ይህ መደበኛ ስብሰባ!!!

በመግለጫው ተ.ቁ(4)፣ "የአዲስ አበባንና የአህጉረ ስብከት ችግሮችን አጥንተውና ለይተው እንዲያቀርቡ፣ ብፁዓን አባቶችና ባለሞያዎች እንዲሠየሙ ተደርጓል" እያለ ማላዘኑ፣ የዚሁ ገጽታው ተጨባጭ ማረጋገጫ ነው!!!

በቤተ ክርስቲያን የሥልጣን መዋቅር ከፍተኛው አካልና ለተቋማዊ ዕድገቷም ውድቀቷም ግንባር ቀደም ተጠያቂ የኾነው ቅዱስ ሲኖዶስ፣ በአገር ሰላምና ጸጥታ ጉዳዮች ያሳየውን የሚያስመሰግን አቋም፣ እጅግ ተፈላጊ በኾነው ወሳኝ ውስጣዊ አስተዳደራዊ ለውጥ አጀንዳዎች ላይ አልደገመውም፡፡ በውጫዊ ጉዳዮች ተደማጭነቱና ተጽዕኖ ፈጣሪነቱ፣ በውስጣዊ ተቋማዊ አንድነቱና ጥንካሬው ላይ የተመሠረተ ስለ መኾኑ ከቶ እንደምን ማስረዳት እንደሚቻል የጨነቀ ኾኗል፡፡

ብዙ የተደከመበትን የመሪ ዕቅድ ትግበራ ሒደት፣ በጊዜ የለንም ንቃትና ዝግጁነት፣ በቀዳሚ አጀንዳነት አንሥቶና የምር ገምግሞ ተገቢውን አቅጣጫና መመሪያ መስጠት ሲገባው፣ በተሰላቸበት የመጨረሻ ቀን ወደ ኋላ እንዲመለስ፣ ተንገራግጮም እንዲቆም በር ለሚከፍት ዓምባገነናዊ ውሳኔ አሳልፎ ሰጥቶቷል!!

ዋናው ተጠያቂ ፓትርያርኩ ቢኾኑም፣ በሲኖዶሳዊ ሥልጣኑ ገሥጾ ሊገራቸው ሲገባ በዋዛ ያልፋቸዋል፡፡ ፓትርያርክ አቡነ ማትያስም፣ ሐሳቡን ያመነጨኹት እኔ ነኝ፤ የእኔ ሐሳብ ነው፤ እያሉ በቃለ ነቢብ በየመድረኩ የሚመጻደቁበትን፣ በተጨባጭ ግን በየሰበቡ የሚያጓትቱን ወሳኝ የአስተዳደራዊ ለውጥ አጀንዳ፣ ከፀረ ለውጥ አማሳኞች ጋራ በጨለማ እየዶለቱ አግተውት ይገኛሉ!!

የቅዱስ ሲኖዶስ ምልአተ ጉባኤ፣ አስተዳደራዊ መዋቅሩ ለተመሠረተበት የካህናትና ምእመናን ኅብረት አቤቱታዎች ፍትሕ ሳያይ፣ ለሊቃነ ጳጳሳቱ አድልቶ እንደ ወሰነ ብዙዎች ታዝበዋል፡፡ ይህ በድምር፣ ረጅም በማይባል ጊዜ ውስጥ ለሚያስከትለው ከቅንዓት የመነጨ የተቆርቋሪ ወገኖች አድማሳዊ ምድር አንቀጥቅጥ ቁጣ ግን ራሱን ያዘጋጀ አይመስልም፡፡

ምንጭ፡- ሀራ ተዋህዶ

# አገራችን . . .

ከገጽ 10 የዞረ

በጉሳ እዚያ አካባቢ የሚገኘው በቁጥር በዛ ያለው ብሔርስ ባይቀበላቸው የት ሊሄዱ ነው? የራሳቸውን ቀጠና ሊፈጥሩ ነው? እንደዚህ ከሄደ መቆራረሱ መበጣጠሱ ምን ላይ ነው የሚቆመው?

ብዙ ጊዜ በብሄሮች መካከል የሚነሱ ግጭቶችን እንዲባባሱ የሚያደርጋቸው የመሪዎች፣ የምሁራንና የልሂቃንና ሚና ነው፡፡ በብዙ አገሮች የብሔሮች ኢኮኖሚና የፖለቲካ ጠብ ተብሎ የሚተረጎመው በእነዚያ ብሄሮች መሪዎች መካከል ያለ የኃይል፣ የሥልጣንና የኢኮኖሚ ጥቅም ሽኩቻና ፉክክር ነው፡፡ የተደበቀው የመሪዎቹ የግል ፍላጎት፡ና ዓላማ የብሄራቸው ፍላጎት ወይ ብሶት ተደርጎ ስለሚቀርብ ሕዝቡ በቀላሉ ይቀሰቀሳል፡፡ንቃተ ሕሊና የጎደላቸውም የብሔሩ አባሎች የተደበቀውን አጀንዳ በጥልቅ ሳይረዱ ብሔራችን ተጠቃ ወይ ተነፈገ በማለት መሪው "ለብሄራችን መብት ወይም መጠቀም መሰናክል ናቸው" ካላቸው የብሄር ሰዎች ጋር ሰው ሳይለዩ ማንነው አጥፊ፣ ማንነው አልሚ ሳይሉ በጅምላ ይጣላሉ ወይም ያጠቃሉ፡፡ እንግዲህ እንደዚህ ዓይነት ግጭቶች ከላይ ከላይ ሲታዩ የህዝብ ለሕዝብ ግጭት መስለው ቢቀርቡም፣ ሥረ ምክንያታቸው ግን የመሪዎቹ ግጭት እንጂ በብሄሮቹ መካከል በቋንቋ፣ በባህል፣ በዘር መለያየት ወይም አለመጣጣም አይደለም፡፡

> ***...የአገራችንን ሁኔታ ስንመለከት እራሴ ልጅ በነበርኩበት ጊዜ ባደግኩበት ከተማ ብዙ ብሄሮችና ሃይማኖቶች ቢኖሩም ስታዘበው ያደግሁት መተባበርና መደጋገፍን እንጂ መጣላትንና መራራቅን አልነበረም...***

በተለያዩ አገሮች ካፈራሁዋቸው የሥራ ልምዶች የወጡ ለዚህ ማስረጃ የሚሆኑ ብዙ ምሳሌዎች አሉ፡፡ ከነዚህ አንዱ፣ በጎረቤታችን ኬንያ ውስጥ ከጥቂት ዓመታት በፊት የተከሰተው መተላለቅ ነው፡፡ ላለፉት ብዙ ዓመታት ኬንያ ውስጥ ኪኩዩና ሉዎ በሚባሉ ሁለት ታላላቅ ብሄሮች መካከል ብዙ ግጭትና መገዳደል ተፈጽሟል፡፡ የሁለቱ ብሄሮች መሪዎች፣ በኪኩዩው በኩል የኬንያታ ቤተሰብና በሉዎ በኩል የኦዲንጋ ቤተስቦች ናቸው፡፡ ሁለቱም ቤተሰቦች የፖለቲካ ሥልጣን የኛ ነው፤ በእጃችን መሆን አለበት ወይም በእጃችን መቆየት አለበት ባይ ናቸው፡፡ ምርጫ በመጣ ቁጥር የሉዎ ብሔር አባሎች "አሁንም ኪኩዩዎች ሊገዙህ ነውና ተነሳና የሚገባህን ሥልጣን ያዝ" ተብሎ ይቀሰቀሳል፡፡ የኪኩዩም ሕዝብ "ሉዎች ያለህን ሥልጣን ሊወስዱብህ ነውና ተነስና ለመብትህ ቁም" ተብሎ ይቀሰቀሳል፡፡ በ2007 እ.ኤ.አ በእነዚህ ብሄሮችና አጋሮቻቸው የተነሳው ግጭት ወደ 1300 ሰው ሕይወት ሲያጠፋ፣ 600 000 ሰው አፈናቀለ፤ በቢሊዮን ዶላር የሚቆጠር ንብረት አወደመ፡፡ የዚያን ጊዜ ከአፍሪቃ አንድነትና ከነኮፊ አናን ጋር ሆነን ይህንን ግጭት በድርድርና የጥምር መንግስት በመመስረት ካስታረቁት ሰዎች እኔ አንዱ ነበርኩ፡፡ ይህ ግጭትና የአፈታቱ ዘዴ ለኛ ለኢትዮጵያን ብዙ የሚያስተምረን ትምህርቶች አሉ፡፡

በብሄሮቹ መካከል ብዙ ደም ከፈሰሰ በኂላ ብጥብጦቹን የመሩት የኬንያ የፖለቲካ መሪዎች (ማለት፣ ኡሁሩ ኬንያታና፣ ራይላ ኦዲንጋ፣ ዊልያም ሩቶን ጨምሮ) በሥልጣን ክፍፍል ተስማምተዋል፡፡ ሦስቱም ሥልጣን ላይ ተቀምጠዋል፡፡ በኪኩዩ፣ ሉዎና ካላንጂን ብሔሮች መካከል በጠቅላላ ሰላም ወርዷል እንኳን ባይባልም መጋደሉ ቆሟል፡፡ሆኖም በዚህ ስምምነት ተጠቃሚዎቹ መሪዎቹ እንጂ የተራ ሉዎው፣የተራ ኪኩዩውና የተራ ካላንጂኑ ሁኔታ እምብዛም አልተሻሻለም፡፡ መሪዎቹ ተጋደል ሲሉት ተጋደለ፤ አሁን ደግሞ በሰላም አብረህ ኑር ሲሉት፣ ይኸው አብሮ በሰላም ይኖራል፡፡

እንግዲህ ለነዚህ ግጭቶች የመሪዎችን ሚና ከመመልከት በላይ ፖለቲካ ፓርቲዎችንም በብሄር ከመመስረት ፋንታ በአይዶሎጂ ላይ የተመሠረቱ እንዲሆኑ ማድረግ የብሄር ግጭትን ለመቀነስ አንዱ ሌላው መፍትሄ ሊሆን ይችላል፡፡

በተጨማሪም መልካም አስተዳደርን ከመገንባት በላይ በተለይ ዜጎች አኩልነታቸው ሙሉ በሙሉ የሚጠበቅበትና ከአንድ ወይ ከሌላው ብሄር የተወለዱ በመሆናቸው ብቻ የማኅበረሰባዊ፣ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ አድልዎ ሰለባ እንዳይሆኑ አስተማማኝ ዋስትና የሚሰጡ ሕጎችና አሰራሮች መኖር አለባቸው፡፡ በሌላ አነጋገር የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሙሉ የዜግነት መብቱ መከበር፣ መጠበቅ አለበት፡፡ ይኸም ካልሆነ ብዙ ጊዜ ሳይወስድ፣ ካለ ብዙ መሰናክል፣ መጉላላትና ወጭ፤ ባስተማማኝ ሁኔታ ሙሉ የዜግነት መብቱን የሚያስከብርበት ሂደት እና መዋቅር መኖር አለበት፡፡ አንድ ዜጋ ሙሉ መብቱ ባስተማማኝ ሁኔታ ከተከበረለት ብዙ በብሄሮች መካከል መብትን ለማስከበር በሚደረግ ጥረት ምክንያት የሚፈጠሩ ግጭቶች ሊቀረፉ ይችላሉ፡፡

ከዚያም አልፎ ሌላው ዘላቂ መፍትሄ ዘግነትን ማጠናከርና የህዝቡን ንቃተ ሕሊና ማስፋት ነው፡፡ ልሂቃን ለራሳቸው ግል ጥቅምና ሥልጣን ሕዝቡን ከለላ አድርገው አርስ በርስ ሲያጣሉት፣ በዚህ ምክንያት በክፉም በደጉም አብሬ ከኖርኩት፣ መከራዬንና ደስታዬን ከተካፈለኝ፣ ከተጋባሁት ጎረቤቴ ጋር የሌላ ብሄር ሰው ብቻ በመሆኑ አልጣላም፣ አልገድልም፣ አልለያይም፣ አላፈናቅልም ማለት እንዲችል ሕዝቡን ማስተማር ለዚህ ዓይነቱ የብሄር ግጭት አንድ ታላቅ መፍትሄ ይሆናል፡፡

የብሄር ግጭቶችን መፍትሄ በተመለከተ፣ ከሁሉ የሚያስገርመው ነገር አንድ ብሄር፣ አንድ ቋንቋ፣ አንድ ባህል ያለው ሁሉ ባንድ ቀጠና ስለተካለለ ብቻ ያለግጭት በሰላም ይኖራል ማለት አይደለም፡፡ አንድ ብሄር፣ አንድ ቋንቋ፤ አንድ ሃይማኖት፣ አንድ ታሪክ ያላት ሶማሊያ እርስ በርስ መተላለቅ ውስጥ ከገባች አሁን ሰላሳ ዓመት ሊጠጋ ነው፡፡ የርዋንዳው ጄኖሳይድ አንድ ቋንቋ አንድ ባሕል አንድ ሃይማኖት ባላቸው ሕዝቦች መካከል የተፈጸመ መፈጀጀት ነው፡፡ በሌላ በኩል ዛምቢያ 72 ብሄር ያለባት አገር ናት፡፡ ግን እነዚህ ሁሉ ብሄሮች እያላት በባህልና በቋንቋ በመለያየት ብሄር ለብሄር አልተፋጀም፡፡

የአገራችንን ሁኔታ ስንመለከት እራሴ ልጅ በነበርኩበት ጊዜ ባደግኩበት ከተማ ብዙ ብሄሮችና ሃይማኖቶች ቢኖሩም ስታዘበው ያደግሁት መተባበርና መደጋገፍን እንጂ መጣላትንና መራራቅን አልነበረም፡፡ ቤተ ክርስቲያን ሆነ መስጊድ ሲሰራ ክርስቲያኑም ሙስሊሙም መዋጮ እያደረገ ሲገነባ ነው የማስታውሰው፡፡ አሁን በአገራችን የተከሰተውን ሁኔታ አንስተው አንድ የሙስሊም አዛውንት ሲናገሩ፡ "በአገራችን፣ በማኅበረሰባችን ብሄርና ጎሳ ነበር፡፡ግን አሁን አገራችን ያለውን ብሄርና ጎሳ እኛ አዛውንቶቹና የአገር ሽማግሌዎቹ ልናውቀው አልቻልንም፡፡ ድሮ ብሄሮች ተጣልተው ስናስታርቅ፣ በሉ ተጋቡ ነበር የምንለው፡፡ ጋብቻቸው ሁለቱንም አንድ ስለሚያደርጋቸውና፣ እንደገና እንዳይጣሉ ገደብ ስለሚሆናቸው፡፡ አሁን አገራችን ያለው ብሄር ግን ተለያዩ እንጂ ተጋቡ የሚል አይደለም" ሲሉ ተናገሩ፡፡

በእኔ ግምት የኢትዮጵያን ብሔሮች ከሚለያያቸው ይልቅ የሚያገናኛቸው ይበልጣሉ ብዬ አምናለሁ፡፡ ላለፉት 27 ዓመታት ስናስተምረው የነበረው፣ ቋንቋችንና ባህላችን ልምዶቻችን ሃይማኖታችን ምንያህል እንደሚለያዩ እንጂ ምንያህል የአንድ ከፍ ያለ ባሕላዊ ወይም የአንድ ፍልስፍና፣ ርዕዮተ ዓለምና ሥልጣኔ ተቀጣጣይ እንደሆነ አይደለም፡፡ ብዙ ጊዜ የብሔሮችና የባሕል ጥናት የምንለው፣ ምንያህል አንዱ ከሌላው እንደተለየ ? እንጂ ምንያህልም መገናኘትና መተሳሰር አለው? የሚለው ጥያቄ ላይ አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር እምብዛም አላተኮረም ፡፡ ብሔሮችን የሚያስተባብራቸውን፤ ባሕላቸውና እሴቶቻቸውም ምን ያህል ተመሳሳይ ተያያዥነት እንዳላቸው ትልቅ ጥናት ብናደርግ፣ ምናልባት የአገራችን ሕዝቦች መመሳሰልና አንድነት ከጠበቅነው በላይ ያስደንቀን ይሆናል፡፡ ይህንን ሥራ ለተመራማሪዎቻችን እንደቤት ሥራ በደምብ መስጠትና ውጤቱንም ለሕዝቡ ማስተማር ይኖርብናል፡፡ ይህ በራሱ አንድ የአገር ግንባታና የሰላም ዕቅድ ሊሆን ይችላል፡፡

***በቀጣይ እትማችን ስለ ሃይማኖት መሪዎችና የሀገር ሽለማግሌዎች ሚና ምን መሆን አለበት? በሚለው ላይ እመለስበታለሁ፡፡***

# ሃይ ባይ ያጡት ደላሎች !

**አሸናፊ በሪሁን**

የካናዳ መንግስት በቅርቡ በቀጣዮቹ ሦስት ዓመታት ወደ 1 ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎችን እንደሚቀበል ካስታወቀ ወዲህ ለደላሎች አዲስ የማጭበርበሪያ ሥራ ተከፍቶላችዋል። ቢቢሲ በአማረኛ ደረ-ገፁ ላይ በቅርቡ እንዳስነባበን ይህንን የሰማችው ኑአሚን የዛሬ ዓመት ገደማ ነበር ወደ ካናዳ እንወስድሻለን ያሉ ሰዎች በኩል እንቅስቃሴ የጀመረችው። ጓደኛዋ ሆኑ ኑአሚን ወደ ካናዳ እንወስዳለን ብለው የሚሉትን ሰዎች በአካል አያውቋቸውም። ትውውቃቸው ከስልክ የዘለለ አልነበረም። በሰላሳዎቹ መጀመሪያ የዕድሜ ክልል ውሰጥ የምትገኘው ኑአሚን መኩሪያ የካናዳ ጉዞ ሂደቱን የጀመረችላት ካናዳ የምትኖር የቅርብ ጓደኛዋ ነች። ኑአሚን በተለያዩ ጊዜያትን ለሂደቱም ማስፈፀሚያ በሚል ወደ ካናዳ እንልክሻለን ላሉት ደላሎች ከ30ሺህ ዶላር በላይ ከፍላለች። ሰላሳ ሺህ ዶላሩ የተከፈለው በተለያየ አገር ውስጥ እና ውጪ ሀገራት ባሉ የባንክ ሂሳቦች ነው። ኑአሚን አራት ሺህ ዶላር (በብር መንዝራ) ሃገር ውስጥ ባለ የባንክ ሂሳብ ስታስገባ ጓደኛዋ ደግሞ ካናዳ፣ ጣልያን፣ ዱባይና ኬንያ በሚገኙ የባንክ ሂሳቦች ቀሪውን ገንዘብ ለደላሎች አስተላልፋለች። ይሄ ሁሉ ብር ፈሶም ደላሎች በዚህ አልረኩም ወጪዎችን ከላይ ከላይ እየቀለሉ መጠየቁን ቀጠሉበት እንጅ ። ይሄኔ ነው እነ ኑአሚን መተማመኛ ነገር ሲያጡ እና ሂደቱም ለውጥ እንደሌለው ሲያውቁ ቆም ብለው ማሰብ የጀመሩት ። በኋላም ሂደቱ ገና ነው አላለቀም እሉ፤ ሲያጭበርበሩ በነበሩት ደላሎች መጭበርበራቸውን አውቀው ገንዘብ ላለመጨመር አሻፈረኝ ብለው ሂደቱን አቋረጡት።

የኑአሚን ታሪክ በዳላሎች እየተጭበርበሩ ያሉ የበርካታ ኢትዮጵያውያንም ታሪክ ነው። ዛሬም ወደ አውሮጳ ሀገራት ለስራ እንልካለን በሚሉ ደላሎች እና ሰራተኛ እና አሰሪ አገኛኝ ድርጅቶች እየተጭበረበሩ ያሉትን ቤቱ ይቁጠራቸው። በቅርቡም ትልቅ ክፍያ የሚያስገኝ ስራ እናስቀጥራችኋለን በሚሉ አጭበርባሪ ደላሎች ተታለው ወደ ፖላንድ ያቀኑ ኢዮጵያውያን ለከፋ ችግር እየተጋለጡ መሆኑን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታውቋል ። እነዚሁ ስደተኞችም በተለያዩ ድርጅቶች እና ግለሰቦች ቅስቅሳ ተገፋፍተው ከ8 ሺህ ዶላር እስክ 300 ሺ ብር የከፈሉት በፖላንድ ርዕሰ መዲና ዋርሶ የተሻለ ስራ ታገኛላችሁ ተብለው ነበር ። ፖላንድ ከደረሱ በኋላ ግን ምንም ነገር የለም ። እናም ዛሬ ያሰቡት ሳይሆን ቀርቶ መግቢያ እና መድረሻ አጥተው ሜዳ ላይ ወድቀው ስቃይ ላይ ናቸው። ለዜጎችዋ ስራ መፍጠር እየከበዳት ያለችው ፖላንድ አዲስ ስደተኛ ልትቀበል ቀርቶ የአውሮጳ ህብረት የስደተኞች ፖሊሲ ሳይቀር በመቃወም ስደተኞችን በኮታ የመቀበልን ጥያቄ ውድቅ ያደረገች ሀገር ነች ።

በሌላ በኩል ደግሞ ወደ አረብ ሃገራት እንዲልኩ ህጋዊ ፈቃድ የተሰጣቸው ሰራተኛ እና አሰሪ አገኛኝ ድርጅቶች ከተሰ ጣቸው ፈቃድ ውጭ ወደ አውሮጳ፣ እስያ እና ሌሎችም ውጭ ሀገራት እንልካለን የሚሉ አማላይ ማስታወቂያዎችን በድረ ገፆቻ ቸው ላይ በመለጠፍ ማጭበርበራቸውን እንደቀ ጠሉበት ነው። ለዚህ ደግሞ ሰዎችን ወደ ተለያዩ የአውሮጳ እና እስያ ሀገራት ለመላክ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ፈቃድ እንዳገኘ ሲያስተቀዋውቅ የነበረው እና በቅርቡ መግለጫ የተሰጠበት ኢትዮጵያ ሰራተኛ እና አሰሪ አገኛኝ የተባለው ደርጅት አንዱ ነው። ድርጅት ወደ ተለያዩ አገራት ለስራ እና ለጉብኝት ለመላክ ህጋዊ ዕውቅና እንደተሰጠው በመግለጽና ለዚህም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የድጋፍ ደብደቤ እንደጻፈለት በማስመሰል ደረ ገፁ ላይ በመለጠፍ ብዙዎችን ሲያጭበረብር ቆይቶል፡ ፡ ዕውቅና ተሰጠም ባለው ደብዳቤ ላይም ደርጅቱ ወደ ካናዳ፣ እንግሊዝ፣ ጀርመን ፣ ስዊዲን፣ ኖርዌይ፣ ጣሊያን፣ ፈረንሳይ ፣ ሰፔን እንዲሁም ከእስያ ሀገራት መካከል ደግሞ ወደ ቻይና ፣ ጃፓን ፣ ኮሪያ ፣ ሲንጋፖር እና ወደ ሌሎችም ውጭ ሀገራት በህጋዊነት እንደሚልክ ይገልፃል ። ይሁን እንጂ በቅርቡ ውጭ ጉዳይ ሚኒሰቴር መስሪያ ቤት ለድርጅቱ ምንም አይነት ደብዳቤ እንዳልፃፈና ዜጎችም በዚህ የሃሰት ደብዳቤ ተገፋፍተው ችግር ላይ እንዳይወድቁ የሚያስጠነቅቅ ምላሽ ሰጥቷል። ሚኒስቴሩ በድርጅቱ እና ይህን መሰል ወንጀል በሚፈጽሙ መሰል ተቋማትን ተከታትሎ ለህግ እንደሚያቀርብም አስታውቋል ።

በካናዳ ፣ አውሮፓ እና ሌሎችን ሀገራት ለመሄድ በማሰብ የተጭበረበረ ቪዛ እና የመኖሪያ ፍቃድ ለማግኘት ሲባል ሐሰተኛ ማስረጃዎችን መጠቀም እንደ ከፍተኛ ወንጀል ይቆጠራል። ሀገራቱ ሐሰተኛ ማስረጃ መጠቀማቸው ያረጋገጡባቸውን ስደተኞችም በወንጀል ከመክሰስ ባለፈ ዕድሜ ልካቸውን ወደ ሃገራቸው እንዳይገቡ ዕገዳ ሊጣሉባቸው ይችላል።

ማንኛውም ሰው የተሻለ ኑሮ የመኖር ፍላጎት ቢኖረውም ይህን ፍላጎቱን ለማሳከት ግን ትክክለኛው እና ህጋዊ የሆነውን መንገድ መከተል ይኖርበታል። ስደተኞችም የስራ ዕድል ተገኝቷል፣ ነጻ የትምህርት ዕድል ይሰጣችዋል ስለተባለ ብቻ የጉዞ እንቅስቃሴ ውስጥ ገብተው ረብጣ ገንዘባቸውን በከንቱ ከማፍሰሳቸው በፊት የመረጃው ትክክለኛነት ከሚመለከታቸው ተቋማት ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል ። ይህ ለአጭበርባሪ ደላሎች የሚከፈለው ገንዘብም ሃገር ውስጥ ያሉ ሌሎች ስራ የሚፈጠርባቸውን አማራጮችን ለመጠቀም ከበቂ በላይ ው ። በመሆኑም ስደትን አስበን እንቅስቃሴ ውስጥ ስንገባ እንደነ ነአሚን ልንጭበረበር የምንችልባቸውን ዕድሎቸ ሰፊ መሆናቸውን በማሰብ ልናስብበት እና ህጋዊ መንገዶችን ልንጠቀምባቸው ይገባል ።

ሰዎችን ወደ ተለያዩ ውጭ ሃገራት እንልካለን በሚል የሚያጭበረብሩትን ደላሎች እና ድርጅቶችም ሃይ ባይ የሚላቸው ያጡ ይመስላል። ዛሬም ስም እና አድራሻቸውን እየቀያየሩ ብዙዎችን ለከፋ ነገር እየዳረጉ ነው። መንግስትም ሰዎችን በህገወጥ መንገድ በመላክ ፣ ለእንግልት ለስቃይ ብሎም ለሞት እየዳረጉ ያሉ ግለሰቦችን እና ድርጅቶች ላይ የማያዳግም ዕርምጃ በመውሰድ ዜጎችን ሊታደግ ይገባል ።

***...የኑአሚን ታሪክ በዳላሎች እየተጭበርበሩ ያሉ የበርካታ ኢትዮጵያውያንም ታሪክ ነው። ዛሬም ወደ አውሮጳ ሀገራት ለስራ እንልካለን በሚሉ ደላሎች እና ሰራተኛ እና አሰሪ አገኛኝ ድርጅቶች እየተጭበረበሩ ያሉትን ቤቱ ይቁጠራቸው፡፡ በቅርቡም ትልቅ ክፍያ የሚያስገኝ ስራ እናስቀጥራችኋለን በሚሉ አጭበርባሪ ደላሎች ተታለው ወደ ፖላንድ ያቀኑ ኢዮጵያውያን ለከፋ ችግር እየተጋለጡ መሆኑን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታውቋል...***

## “ሞቴን . . .

◀ ከገጽ 4 የዞረ

***ያሳለፍከውን የብቸኝነት የእስር ዘመንህን አቆራኝተህ አንዳንድ ነገሮችን ብታካፍለን?***

አንዳርጋቸው፡- መጽሐፉ ካለቀ በኋላ ነገሮችን ወደኋላ መለስ ብዬ ሳስበው ለራሴ በጣም ይገርመኛል፡፡ ለሁለተኛ ጊዜ ድገመው ብባል እንዲህ ዓይነቱን አጻጻፍ መጻፍ የምችል አይመስለኝም፡፡ እንዳልከው በጣም አጭር ቢሆንም በአራት ወር ጊዜ ውስጥ ነው ያዘጋጀሁት፡፡ ግን ለሚያነበው ሰው በጣም የታሰበበትና ብዙ ነገሮች የታወሱበት ነው፡፡

ዕስር ቤት በነበርኩበት ሰዓት፤ በተለይ ማንንም ሰው እንዳላገኝ ከአንድ ዓመት ከሶስት ወር በላይ በደሕንነት ዝግ እስር ቤት ውስጥ ሆኜ፣ ምናልባትም መጨረሻዬ እየቀረበ ነው፣ “የተፈረደብኝ ሞትም የሚቀር አይደለም” በሚል የቻልኩትን ያህል በመጻፍ፣ ድንገት እኔ አንድ ነገር ሆኜ በሕይወት ባልኖርም፣ በመጻሐፉ ትውልድ ይማርበታል በሚል በከፍተኛ ትኩረትና ረኸ፻ም ሰዓታት በመቀመጥ፣ ሌላ ነገር ፈፅሞ የማያሰላስል ጭንቅላት በወቅቱ በመፍጠር፣ ፈፅሞ ሊሆን የማይችል ስራ ዓይነት አድርጌ ነው ያዘጋጀሁት፡፡ ከተፈታ በኋላ አሁን በየጊዜው ለራሴ ደግሜ አነበዋለሁ፣ “እንዴት አድርጌ ነው በዛ ሁኔታ ላይ ይሄን ልፅፍ የቻልኩት?” በሚል የምገረምበት ጉዳይ ነው፡፡

በጣም ትልቁ ቁም ነገር ግን ፅፌ ከጨረስኩት በኋላ በጣም ጥሩ መጽሐፍ እንደሚሆን ባውቅም የት ይደርሳል? የሚለው ያስጨንቀኝ ነበር፡፡ “ማንም አያገኘውም፣ እነዚህ ሰዎች ያጠፉታል” በሚል የእንግሊዝ አምባሰደርን ለጥያቄ በመጡ እና ባገኘኋቸው ጊዜ ሁሉ የምጮኸው፣ ስለእኔ መትረፍ ሳይሆን መጽሐፉ ለሕዝብ ስለሚደርስበት ሁኔታ ነበር፡፡ በጣም ዕድለኛ ሆኜ መጽሐፉ ከጥፋት መትረፉ ያስደስታል፡፡

ይሄ መጽሐፍ በገበያው ካሉና ከነበሩ፣ በየላይብረሪው ካሉ መጽሐፎች ጋር ላይወዳደር ይችላል፡፡ በአንዳንድ ምክንያቶች በጣም የተለየና የተሻለ ጭምርም ነው ብል ማጋነን አይሆንም፡፡ ታሪክን እንዴት መፃፍ እንደሚቻልም የሚያሳይ ይመስለኛል፡፡

***ግዮን፡- መጽሐፉን ካዘጋጀህ በኋላ ላፕቶፑን የወያኔ ደህንነቶች ወስደውት የነበረ በመሆኑ፣ ሳይወገድ ወይም ሳይጠፋ ሊቆይ የቻለው እንዴት ነው? መልሰህ የማግኘቱ ዕድልስ እንዴት ተፈጠረ?***

አንዳርጋቸው፡- የእንግሊዝ አምባሰደሯና የኤምባሲ ሰዎች ሊጠይቁኝ ሲመጡ ሁሌም የምጠይቀው የመጽሐፉን ጉዳይ ነበር፡፡ እነሱም ወደ ውጭ ጉዳይ ሲሄዱ እሱን መጠየቃቸው አልቀረም፡፡ “መጽሐፉ የግል ንብረቱ ነውና ለምንድን ነው የማይሰጠው?” በሚል፤ እንዲመለሰልኝ፡፡ እንደተፈታሁና እዚህ ለንደን እንደገባሁ አንድ ኢሜይል ከኤምባሲ ደረሰኝ፡፡ “መጽሐፉ ኮፒው አለኝ የሚል ሰው፣ የኢሜል አድራሻውን ከላከልኝ እና የእሱ ፈቃድ መሆኑን ካረጋገጥኩ፤ መጽሐፉን በኢሜል እልክለታለሁ” ብሏል አሉኝ፡፡

በዛ መሰረት ለኤምባሲው የኢሜል አድራሻ ላክሁላቸው በዛ በተሰጠኝ ኢሜል አድራሻ ሰውየው ኮንታክት አደረገኝና “ልላክልህ በኢሜይል? ወይስ ለኤምባሲዎቹ ልስጣቸው?” አለኝ፡፡ እኔም አታችመንት አድርገህ ላክልኝ አልኩት፡፡

***ግዮን፡- ማነው ይሄ ሰው?***

አንዳርጋቸው፡- ይሄንን ያደረገው፣ በዛን ወቅት የደህንነት አባል ሆኖ ይሰራ የነበረ፣ አሁንም እያሰራ ያለ አደራው የሚባል ሰው ነው፡፡ እኔን በመመርመር ከተመደቡ ሰዎች ትልቅ ኃላፊነት የነበረው እሱ ነው፡፡ አሁን ነው ስሙን ማወቅ የቻልነው፣ ያኔ ኢሳይያስ ብለን ነበር የምንጠራው፡፡ ይሄ አደራው የሚባለው የአደዋ ተወላጅ በደርግ ጊዜ ጎበዝ ተማሪ ስለነበር፣ ከዩንቨርስቲ እንደጨረሰ ወደ ብሔራዊ ደሕንነት ተመድቦ ይሰራ የነበረ ሰው መሆኑን አውቂያለሁ፡፡ ፕሮፌሽናል የደሕንነት ሰው ነው፣ የድርጅት አባልም ሆኖ አያውቅም፡፡ በእውቀቱ ብቻ ስለሚያገለግል በደርግም ሆነ በወያኔ ዘመን እንዲሰራ የተመረጠ ሰው ነው፡፡

ዕስር ላይ ሆኜ እኔን ምርመራ በሚያደርግበት ሰዓት ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርግልኝ ነበር፤ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን፡፡ ምንም ዓይነት ቁጣ፣ ስድብ፣ ግልፍተኝነት ሆነ ትርፍ ቃል ሳይናገር፣ በጣም በሚገርም መንገድ ነበር የሚያናግረኝ፡፡ ይሄ ሰውዬ ከዛ በፊት በ1997 ዓ.ም ምርጫ ዝዋይ የታሰርኩ ጊዜም አግኝቼው ነበር፡፡ ይህን ሰው እነ መለስ ልከውት እኔ ጋር በወቅቱ መጥቶ ነበር፣ ያኔም የጠየቀኝ ጥያቄ “በምርጫ 97 ኢህአዴግ ምን ሆኖ ነው እንደዚህ የሆነው?” የሚል ነበር፡፡ በዛን ጊዜ አራት ሰዓት ነው ያወራነው፤ እንደሚመስለኝ ለጠየቁኝ ጥያቄ ምላሽ ሰጥቻለሁ፣ ደብድበው ቢያስሩኝም ችግራቸው ምን እንደሆነ ተናግሬያለሁ፡፡

በድጋሚ ስያዝና ኢንተርቪ ሲያደርገኝ እኔ ረስቼው ነበር፤ እሱ ግን “ረሳኸኝ ወይ?” በሚል የዝዋዩን ቆይታ አስታውሶኛል፡፡ ከፍተኛ ትህትናና መልካም አቀራብ ነው ለእኔ የነበረው፡፡ መፅሐፉን ፅፌ ሳጠናቅቅ መጨረሻ ላይ ኮምፒውተሩን የወሰደው እሱ ነው፤ ፅሁፉን በዛ ኮምፒውተር ላይ ነው ሴቭ ያደረግሁት፡፡ ግን ይሄን ያህል ደረጃ ጠብቆ፣አስቀምጦት በዚህ መንገድ ይመልስልኛል ብዬ ፈፅሞ አላሰብኩም፡፡

> **...በጣም ትልቁ ቁም ነገር ግን ፅፌ ከጨረስኩት በኋላ በጣም ጥሩ መጽሐፍ እንደሚሆን ባውቅም የት ይደርሳል? የሚለው ያስጨንቀኝ ነበር..**

ከእስር በተፈታሁ ማግስት ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አህመድ ቢሮአቸው ጠይቀውኝ ስንገናኝ ያነሳሁላቸው አንዱ ጥያቄ የመጽሐፉን ጉዳይ ነው፡፡ “እሱ ምንም አይሆንም፣ የት ይደርሳል ብለህ ነው፣ ይገኛል” የሚል ምላሽ ሰጥተውኝ ነበር፡፡ እሳቸውም በቀጥታ በጉዳዩ ላይ ይግቡበት አይግቡበት ርግጠኛ ባልሆንም፤ ሰውዬውን መጽሐፉን በተመለከተ ሳያናግሩት የቀሩ አይመስለኝም፡፡ ግን የእዚህ ደህንነት ባህሪይ እንደዛ ባይባልም፣ መጽሐፉን የሚያጠፋ ዓይነት ሰው እንዳልሆነ ገምቻለሁ፡

በእሱ ስር ይሰሩ የነበሩ ሰዎች ናቸው ዛሬ እስር ላይ የሚገኙት፡፡ ለአንዳንድ ሰዎች በመልክ ደረጃ ገጽታቸውን ስነግራቸው ስማቸውን አሁን ከተፈታሁ በኋላ አሳውቀውኛል፡፡እነዛ ደህንነቶች በስልጣን ረገድ ከእሱ በታች ቢሆኑም ለእስር ተዳርገዋል፡፡ ምናልባትም ኮምፒዩተሩ እነሱ እጅ ቢገባ፣ ይሄ መጽሐፍ በምንም ዓይነት መንገድ እጄ አይገባም፣ ለሕዝብም አይደርስም ነበር፡፡ አሁን ለምሳለሌ ይሄ ከላይ የጠቀስኩት መልካም የሆነ የደህንነት ኃላፊ በሌለ ጊዜ “ማአሾ” የሚባለው ሰው ይመጣ ነበር፡፡ እሱ ያለው ቁጣ፣ ጥላቻ፣ እልህ፣ ድርጅታዊ ፍቅርና አምልኮ ደንበኛ ካድሬ መሆኑን እንዳይ ረድቶኛል፡፡ ያኛው ግን ፕሮፌሽናል ባለሙያ ነው፡፡

ይሄ መጽሐፍ የተረፈው በዕድልም ነው፣ በጥሩ ሰው እጅ በመግባቱም ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ ይሄን ሰው መጽሐፉ ላይ ስሙን አልጠቀስኩትም፤ ግን ምስጋና ሲበዛበት ነው ብያለሁ፡፡ እሱ ነው ዛሬ ላይ እዚህ ደረጃ እንዲደርስ ያደረገው፡፡

***ግዮን፡- ከተፈታህ በኋላ በአካል ልታገኘው አልፈለግህም? ወይም አልሞከርክም?***

አንዳርጋቸው፡- ለማግኘት ከባድ ነው ብዬ አላስብም፡፡ በስራ ላይ እንዳለ የእሱ አለቆች ነግረውኛል፡፡ ግን ድንገት እሱ መገናኘቱን የማይፈልገው ነገር ይሆናል በሚል አልሞከርኩትም፡፡ የዚህን ያህል ትልቅ ፕሮፌሽናል ሰው ከሆነ፣ ስራውን መስራት እንጂ ሌላ ነገር አይፈልግም፡፡ ተገናኝቶ መጨዋወቱን አይመርጥ ይሆናል በሚል፣ እንዳላስጨንቀውና እንዳላስቸግረው በሚል ነው እንጂ፤ እኔ ባገኘው ችግር የለብኝም፡፡ የግ መብቱን ላለመጋፋት ነው ማግኘቱን ያልሞከርኩት፡፡

እኔ ማድረግ የምችለው በፊት ስሙን አላውቀውም ነበር፣ አሁን ስሙን ስላወቅሁ መጽሐፉም አደባባይ ስለወጣ፣ ምንም ችግር የለውምና በእንዲህ ዓይነቱ አጋጣሚ ማመስገን ብቻ ነው፡፡

***ግዮን፡- መጽሐፉን በምትፅፉበት ወቅት የተለያዩ ጫናዎች፣ ማንቋሸሽ፣ ሞራል የመንካቱ ነገር ያጋጥማልና በእንዲህ ዓይነት ስሜት ውስጥ ሆነህ የተረበሸክበት ወይም ደግሞ ስትፅፈው ያስቸገረህ፣ ታሪኮችን ለማዋቀር የፈተነህ የትኛው ምዕራፍ ነበር?***

አንዳጋቸው፡- መጽሐፉን ስታነቡ የምታገኙት ነገር አለ፤ እንዳልኩት ይሄን መጽሐፍና እዚህ እስር ቤት እያለሁ መፃፍ የምችለው እስከተወሰነ ዘመን ድረስ ነው ▶

ብያለሁ፡፡ ያ ዘመን አሁን ያለውን የወያኔን ዘመን ሊነካ አይችልም፡፡ ምክንያቱም እሱን ከነካ ወይ በአድርባይነት መፃፍ አለብኝ ማለት ነው፡፡ እንደዛ ከሆነ ደግሞ እውነተኛ ታሪክ አይሆንም፡፡ ወይ ደግሞ እንደልቤ መፃፍ አለብኝ፡፡ እንደዛ ከፃፍኩ ደግሞ በዛ የተነሳ መጽሐፉን ወደ ውጭ የማውጣት ዕድሉን ዜሮ ነው የማደርገው፡፡

ስለዚህ እስከ 1970 ዓ.ም ድረስ ነው መሄድ የቻልኩት፡፡ ሌላ ጊዜ ሌላ ዕድል ሲገኝ ቅፅ ሁለት፣ ሶስት እያልኩ እደርስበታለሁ፡፡ እነሱን የሚነካ ነገር ስለሌለው፣ እነሱን እንዲህ ስለተናገርኩ መፅሐፉን እጄ ይገባል? አይገባም? የሚል ጭንቀት ነገር ውስጥ አልገባሁም፡፡ ግን በጣም ብዙ ስሜት የሚፈታተኑ ቻፕተሮች አሉ እዛ ፅሁፍ ውስጥ፡፡

ስታነቧቸው እንኳን ለኖረበትና በዛ ውስጥ ላለፈ ሰው ቀርቶ፣ ዝም ብሎ ታሪኩን ለሚያነበውም ሰው የውስጥ ስሜትን ይነካል፡፡ አሁን መጽሐፉ ከወጣ በኋላ እዚህ ለንደን አንብበውት ሰዎች ሲያለቅሱ አይቻለሁ፡፡ እኔም በጣም ስሜታዊ የሆንኩበተት፣ እጄ ለመፃፍ የተቸገረበት፣ እንባዬ የፈሰሰበት ቀን አለ፡፡ አንዳንዶቹ ምዕራፎች በተለይ ከጓዶቻችን፣ ከወንድሞቻችን፣ ከቤተሰብ ጋር ሞት ጋር የተያያዘው ዕልቂትና ተዛማጅ ችግሮችን የሚያሳዩት ምዕራፎች ይረብሻሉ፡፡

ወደ ማልቀስ የወሰደኝ ዋነኛ ምክንያት በዘመኑ አላለቀስንም እኛ፤ወንድሞቻችን ተገድለው "ትግል ይሞታል እንጂ ታጋይ አይሞትም" ብለን እናቶቻችን ባበዱበት፣ እንደዛ ሲጮሁና ሲያለቅሱ እያየን አንዲት ዕንባ ከአይናችን ያልወረደበት ሁኔታ መኖሩን፣ ምን ዓይነት ሰዎች ነበርን? የሚለውን ነገር በማስታወስ የአባታችንን፣ የእናታችንን፣ የእህቶቻችንን ሞት በዛ ሰዓት ልጆች ከመሆናችን አኳያ ወላጆቻችን ምን ያህል እንደሚጨነቁ ስለማናውቅ፣ ምን ያህል መከራና ስቃይ ውስጥ ከተናቸው እንደነበር በማስብበት ሰዓት ላይ በጣም ስሜቴ ተረብሾ ነበር፡፡ አሁን አባት ስለሆንኩ የወላጅነት ስሜቱ በደንብ ይገባኛል፡፡ አሳዛኝና አስከፊ ስሜቶች ውስጥ የገባሁባቸው አጋጣሚዎቹ በርካታ ናቸው፡፡

እነዚህ ፓርቶች በጣም አስቸጋሪ ነበሩ፡፡ እያቆምክ ስሜትህን እየተቆጣጠርክ ነው የምትፅፈው፡፡ ባዶ ቤት ብቻዬን ስለታሰርኩ "ተው የሚለኝ" ስለሌለ፣ "እረፍ" የሚል ስለሌለ፣ በተለያዩ ስሜቶች ውስጥ እየገባሁ፣ እየወጣሁ ነው በአራት ወር ውስጥ መጽሐፉን ያዘጋጀሁት፡፡

**ግዮን፡- በዋጋ ረገድ መጽሐፉ ተወደደ፣ የገጽ ብዛቱ በርካታ ቢሆንም በሁለት በመክፈል ብዙኃኑ ሕብረተሰብ በትንሽ ዋጋ ሊያገኘው ይገባ ነበር የሚሉ ወገኖች አሉ፡፡ ምናልባት የሽያጩ 70 ፐርሰንት ለአዲሱ ኢ.ዜ.ማ ፓርቲ ገቢ በመሆኑ ይሆን ዋጋው ከፍ ያለው?**

አንዳርጋቸው፡- አንደኛ ነገር መጽሐፉን ሁለት ቦታ ለመክፈል አልተፈለገም፡፡ አንድ ወጥ የተሟላ መጽሐፍ ስለሆነ፡፡ ገፁ ከስድስት መቶ በላይ በመሆኑ የህትመት ወጪው ከፍተኛ ነው፡፡ ስለዚህ ለቅናሽ ተብሎ ታሪኩ መሸራረፍ የለበትም፡፡ በሌላ በኩል ኢ.ዜ.ማ ከመቋቋሙ በፊት የነበረው የአርበኞች ግንቦት ሰባት ድርጀት 70 ፐርሰንቱ ገቢ እንዲወስድ ነበር ቃል የገባሁት፡፡ አሁን የአርበኞች ግንቦት ሰባት ንብረትና ሐብት ሁሉ የአዲሱ ድርጅት ሀብት ስለሆነ ፣በዛ መንገድ ድርጅቱን በፋይናንስ ይደግፋል በሚል የተወሰነ ጭማሪም ይኖረዋል፡፡

ከሌሎች መፃህፍት ጋር ካስተያየኸው በሁለት መቶና በመቶ ሀምሳ ብር የሚሸጡ በጣም ትናንሽ መጻሕፍቶች አሉ፡፡ ከዛ ስናነፃፅረው አሁን ላይ ከመጣው የመጽሐፍ ህትመት እንዲሁም ከመጽሀፉ ውጪና ከገጽ ብዛቱ ጋር ካወዳደርከው መሆን ያለበት እንደውም 400 ብር ገደማ ወይም ከዛ ማለፍም ነበረበት፡፡ ግን እየተሸጠ ያለው በ380 ብር ነው፡፡

በአሁኑ ጊዜ ያለውን የገንዘብ መውደቅ ግምት ውስጥ ስታስገባና ለትንንሽ ነገሮች የሚከፈለውን ነገር ስታየው፣ 380 ብር በጣም በርካታ ሰው ለተለያየ ነገር የሚያጠፋው ቀላል ገንዘብ ስለሆነ ሊገዛው ይችላል ብለን ነው ያሰብነው፡፡



**ግዮን፡- የመጽሐፉ ታሪክ በ1877 ዓ.ም እንዲጀምር የተፈለገበት ምክንያት ምንድን ነው?**

አንዳርጋቸው፡- የመጽሐፉን የመጨረሻ ክፍሎች ከተመለከታችሁ በጣም ከፍተኛውን ክፍል የሚይዘው ከአብዮቱ ጋር የተያያዘው ታሪክ ነው፡፡ አብዮቱ ደግሞ ዝም ብሎ 1966 ዓ.ም ላይ የወረደ ብቻ አይደለም፡፡ ስለ ከተማው ወጣት የትግል ታሪክ፣ አዲስ አበባ ውስጥ የነበሩትን የፖለቲካ ድርጅቶች ታሪክ፣ የግለሰቦች ታሪክ ስለሆነ የምናወራው፤ እነዚህ ግለሰቦች አብዛኞዎቹ የከተማ ሰዎች ናቸው፣ የከተማ ልጆች ናቸው፡፡ አባቶቻቸው፣ አያቶቻቸው ከእዚች ከተማ ጋር ቅርበት ያላቸው ሰዎች ናቸውና ከከተማዋ ታሪክ ጋራ በሚገባ ተተክለው የሚታዩ እስካልሆነ ድረስ ታሪካቸውን በደንብ ሰው ሊረዳው አይችልም፤ በሚል አዲስ አበባን ከታች አስተዳደጓን፣ ከአካላዊ አንስቶ እስከ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አስተዳደጓ፣ በውስጡ የነበረው አገራዊ ሕይወት ምን እንደሚመስል እያሳዩ 1966 ዓ.ም ላይ መድረስ የ66ቱን አብዮት ምን አመጣው? የሚለውን ትውልዱ በቅርበጽ የሚረዳበትን ዕድል ይፈጥራል ከሚል ነው፡፡


በእንዲህ ዓይነት ማዕቀፍቀኡሽፅ ካላስቀመጥከው አብዮትን የሚያህል ትልቅ ነገር በሚገባ መረዳት አስቸጋሪ ይሆናል የሚል ዕምነት ስላለኝ ነው፣ ከ1887 ዓ.ም ተነስቼ መፃፍ የጀመርኩት፡፡ ሁልጊዜም የዚህ ዓይነት አፃፃፍ መንገድን ና የምከተለው፤ ዝም ብሎ የተቆረጠ ነገር ሳይሆን አንድን ነገር ከስሩ ተከትሎ ወደ ላይ እየተገነባ የሚሄድ አፃፃፍ ይመቸኛል፡፡ ለአንባቢም ይጠቅማል፡፡

**ግዮን፡- ቀረ የምትለው ነገር፣ የምታስተላልፈው መልዕክት ካለ ዕድሉን እንስጥህ፡፡**

አንዳርጋቸው፡- የማስተላልፈው መልዕክት ይሄ መጽሐፍ ሰዎች ሊያነቡት ይገባል የሚል ነው፡፡ ቢያነቡ የሚጠቀሙት እነሱ ናቸው፤ ከልቤ ነው ይሄን የምለው፡፡ መጽሐፉን በመሸጥና ባለመሸጥ ዙሪያ ሳይሆን ፣መጽሐፍ ባለማንበብ ጉዳት ይመጣል የሚል እምነት ነው ያለኝ፡፡ ሰው መጽሐፍ ባነበበ ቁጥር የተሟላ ሰው እየሆነ ይሄዳል የምል ዕምነት አለኝ፡፡

የማንበብ ልምድ መዳከሙ በጣም ያሳስበኛል፡፡ አቅምና ችሎታ ያለው በሙሉ እንዲያነበው፣ ማንበብ ለማይችሉትም ሰዎች በቀላሉ ቁጭ ብለው ሊያዳምጡት የሚችሉት አፃፃፍ ስለሆነ ማንም ሰው ሊያነብላቸው ይችላልና በዚህ መንገድ በስፋት አንባቢ እንዲኖረው ነው ጥሪ የማቀርበው፡፡

**ግዮን፡- እናመሰግናለን፡፡**


ፍቅርተ ተሾመ

# ፈረቃው

መብራትን በፈረቃ ማግኘት ፍትህ አለው፡፡ ህዝብን ለምሬት እና ለአመፅ ከሚያዳዱ እና ቅሬታን ከሚቀብሩ ጉዳዮች አንዱ ኢፍትሐዊነት ነው፡፡ መድረሻ ያሳጣል፣ ህዝብን ጥርስ ያስነክሳል፣ እድገትን ህልም ያደርጋል፤ ለስደትም ይማግዳል፡፡ ፈረቃው ፍትህን ለማስፈን ሁነኛው መንገድ ነው፡፡ ፍትህ ሃብትን በእኩል ለሁሉም ማካፈል ነው፡፡ ይህን ፍትህ በመብራቱ የምናየው በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በሚኖሩ ነዋሪዎች መካከል ፍትሐዊ የመብራት ሃይል አቅርቦት በታወቀ የጊዜ ልዩነት መሰጠቱ ነው፡፡ የሃይል እጥረት አዲስ አበባ ካጋጠማት የሰነባበተ ነው አሁን አይደለም የጀመረው፡፡ የአፍሪካ ህብረት መሪዎችን በስብሰባ አዳራሽ ውስጥ በጨለማ ከመዋጥ ጀምሮ አሁን ህዝቦቿን በሻማ እስከማኖር የደረሰ ችግር ውስጥ ነች፡፡ ስለዚህ ወደ እድገት እየተጓዝንም አይደል? ይህን እንኳን ምንያህሉ እየተረዳነው እንደሆነ ባይታወቅም ቅሉ፤ መረዳቱ ቢኖር ኖሮ ትግሉን በመቀላቀል እንደ ህዝብ ማለትም እንደ ባለቤት መስመር በያዘ ነበር፡፡ ለዚህም ማሳያ የሚሆነው በህዝቡ ዘንድ ይባስ ብሎም በባለ ሃብቱ ዘንድ ነጋዴውንም አካቶ ማለት ነው፡፡ ኢፍትሃዊ በሆነ መንገድ የሃገርን ግብር በተለያየ መንገድ ዘርፎ ሲያበቃ መብራት መጠየቅ አንገትን ሊያስደፋ የሚገባ ድፍረት ነው፡፡ በእድገት መንገድ ላይ የሆነ ሰውም ይሁን ሃገር አሁን ላይ አላደገም ገና ሂደት ላይ ነው ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ በሂደት የሚደርስ ሊሰራባቸው የሚገባ ብዙ ስራዎች አሉት ማለት ነው፡፡ ጎዶሎው ብዙ ነው፡፡ መብራት መጥፋቱ አይቀሬ ከሆነ ለዚህ ደግሞ ፍትሐዊ አካሄድ ማስፈለጉ ወሳኙ ነው፡፡ ይህ አንድ ጋት በመሆኑ ይበል ያሰኛል፡፡ ምክንያቱም አንዱ ታይታ የጠፋችው ይህች ፍትሐዊነት ደግሞ መጥታለችና፡፡ ደግሞም ድጋሚ የፖለቲካ መቀጣጫ እና ልክ መተያያ ከመሆን እንዲሰውራት በመመኘት፡፡

## ህገወጥነትና ፍትሃዊነት

ይህ ሁሉ ሲሆን የህገወጥነት መንሰራፋት በእጅጉ አሳሳቢ እና አስደንጋጭ እየሆነ መጥቷል፡፡ ዝርፊያን እና እንደመብት በመቁጠር መሳሪያዎችን ለዝርፊያ እንደ ቀልድ የሚጠቀመው በበዛበት እና ቢጮኽ እንኳን ደራሽ የማይሆን የዜጎች ህሊና በተገነባበት ሁኔታ፣ ኢፍትሐዊነቱ ገጥጦ ለምን ከሃገር ትሰደዳላችሁ ማለት ማላገጥ ይሆናል፡፡ ወዲህ ደግሞ ትንንሽ አማራሪ ማፍያዎችን በመበታተን ጊዜያዊ ሰላምን እና ፍትሕን ማስፈኑ እረፍት ይሰጣል፡፡ ሁኔታዎቹ መመሳቀላቸው ፍትሐዊነት እና ኢፍትሐዊነት በተለያዩ ጉዳዮች ላይ መኖር እና አለመኖራቸው በሁለቱም ሁኔታዎች አይካድም፡፡ ፍትሐዊነት አለ በመብራት ፈረቃ ላይ፤ ፍትሐዊነት የለም ብዙ ጉዳዮችን መዘርዝር ይቻላል፡፡

## ፍትሕ ለየትኛው በደል

መብራት መኖሩም አለመኖሩም በብዙ መልኩ ሲያማርር የቆየ ችግር ነው፡፡ አለ ሲሉት የሌለ የለም ሲሉ የሚመጣው መብራት ስራን እና አኗኗርን እጅጉን አመሳቅሎ ብዙዎችን ብኩን አድርጎ ለኪሳራ ሲዳርግ ስደትን ሲያስመኝ ቆይቷል፡፡ ይሄ ችግር እንደሚታየው በፈረቃው የተቀረፈ ይመስላል፡፡ መብራቱ ስንት ሰዓት እንደሚጠፋ እና እንደሚመጣ ይታወቃል፡፡ በመምጣት እና መሄዱ ላይ ተመርኩዞም ስራዎች ይታቀዳሉ፡፡ ካልታሰበበት እና ድንገተኛ ከሆነ ምስቅልቅል ወደ ታቀደበት እና መውጫ መንገድ ወዳለው ምስቅልቅል መሸጋገር ይህ ነው፡፡ በቀድሞው ፍትሐዊ ባልሆነው አካሄድ የነበሩ ችግሮች እኚህ ብቻም አይደሉም ለትንንሽ ማፍያዎች መገበርንም ያካትታል እንጂ፡፡ በህዝብ ሃብት በተገነቡ ዩኒቨርሲቲዎች እና ተቋማት ውስጥ ተምረው በመንግስታዊ ተቋማት ውስጥ የሚሰሩ ግለሰቦችን ጊዜ ወደ ማፍያነት ቀይሮአቸው ለነሱ መገበር አንዱ ፈተና ነበር፡፡ መንግስት መሸፈን እየቻለ በአስተዳደር እና በሆዳምነት እክሎች ምክንያት ህብረተሰቡ ለሚደርስበት ከመብራት ጋር የተያያዙ የይስራልንና ይስተካከልን ጥያቄዎች፣ መብራትን በአንድ አካባቢ ውስጥ ለይቶ የተወሰኑ ቤቶችን በማጥፋት ያፈጠጠ ዝርፊያ በማካሄድ የገቢ ማግኛ መስክ አድርገውት ቆይተዋል፡፡ኃላፊዎችም የዚህ ችግር ሰለባ ለሆኑት ሰዎች ጆሮ ባለመስጠቱ የልብ ልብ የተሰማቸው እነኚህ ማፍያዎች ያሻቸውን እያስከፈሉ ህብረተሰቡን በቁጥጥራቸው ስር አድርገው መድረሻ ያሳጡት ነበር፡፡ ይህም ተንፍሷል፡፡ ይህ ፍትሐዊ የመብራት ሃይል ክፍፍል ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል በእኩል ማግኘቱን ማየት በችግር ውስጥም እንኳን የእኩልነት ሃይል ማሳያ ነው፡፡

## ስርዓት

አንድ ህብረተሰብ አካሄዱ መሪና አገዛዝ በተቀያየረ ቁጥር የሚናወጥ እና የሚፈስ፤ እየተነዱ ከመሄድ ባለፈ መንገዱን ማወቅ አልፎ ተርፎም መምረጥ ይኖርበታል፡፡ እኛ የምፈልገው እኛ በመረጥነው የሚገዛልን መድረሻችንም ‹‹እድገት›› ‹‹ሰላም›› … የሚሉ ጥያቄዎች ሊኖሩት እንደሚገባ ይታመናል፡፡ መመዘኛውም ፍትሐዊነትን፣ አግባብነት ያለው የግብር ስርዓትን፣ የአገልግሎት ዘርፎችን ማስፋፋት እና በአለም አቀፉ መድረክ የተገዳዳሪነትን መንገድ የያዘ ወይም ያሳካ መሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም ስርዓት በተቀያየረ ቁጥር የሚቀያየሩ ተሿሚዎች፣ የተሰሩ ታሪኮች ተደምስሰው ሌላ ተመሳሳይ ታሪክ የሚቀዳባቸው ከመሆን ባለፈ፤ መሰረት ያለው ስርዓት ወይም መዋቅር ተመስርቶ ገጊዎች ቢቀያየሩም የማይቀያየር ስር የሰደደ የአገልግሎት፣ የአስተዳደርና የህግ የበላይነት የመመስረቱ አስፈላጊነት አሻሚ አይደለም፡፡ ማስታገሻ እና መድኃኒት ሁለቱም በኪኒን አልያም በመርፌ መልክ ይሰጡ ይሆናል አገ ልግሎታቸው ግን እንደ ይዘታቸው ሳይሆን እንደ ስማቸው ይለያያል፡፡

> ...ወደ እድገት እየተጓዝንም አይደል? ይህን እንኳን ምንያህሉ እየተረዳነው እንደሆነ ባይታወቅም ቅሉ፤ መረዳቱ ቢኖር ኖሮ ትግሉን በመቀላቀል እንደ ህዝብ ማለትም እንደ ባለቤት መስመር በያዘ ነበር...

እነዚህ እንደ ማስታገሻ የምናያቸው በጎና ፍትሐዊ የሚመስሉ የአስተዳደር ስራዎች ማስታገሻ እንጂ መድኃኒት አይደሉም፡፡ መድኃኒት ሊሆን የሚችለው በስርዓት ወይም በመዋቅር የተደራጀ የህዝብ አገልግሎት እና አስተዳደር ሲኖር ለዘላቂ መፍትሔ እና ሌሎች ህልም የሚመስሉ የሃገር ራዕዮችን ከግብ ማድረስ ይቻል እንደሆነ ማሰብ ይጀመር ይሆናል፡፡ በስርዓት እና መዋቅር መጓደል ምክንያት ህዝብ ይሰደዳል፣ ይራባል፣ ይደኸያል፣ ይበደላል፡፡ መድኃኒቱ ጠንካራ ስርዓት ነው፤ የፖለቲካ ሹኩቻ መጠቀሚያ የማይሆን ኃላፊነታቸው እና ግዴታቸውን ያለዩ ቢሮክራቶች የማይፈነጩበት፤ አገልግሎቶች እና ፍትህ በአግባቡ በእኩልነት እንዲሰጥ የሚያስገድድ ስርዓት፡፡

አንድ አገዛዝ ወደ ስልጣን ሲመጣ በአንድም በሌላም መልኩ ምርጫ አይተን ባናውቅም እንኳን የህዝብ ፍላጎቶች ላይ የተመረኮዙ አመራሮች ያለ ምርጫም ቢሆን የህዝብን ሃሳብ እያውለበለቡ ወደ ስልጣን ይፈናጠጣሉ፡፡ ያውለበለበው የህዝብ ሃሳብ የማርያም መንገድ እስከሰጠው ድረስ ሙያዊ(ፖለቲካዊ) በሆነ አካሄድ ደግሞ ከግብ ማድረስ የተረኛው አገዛዝ ኃላፊነት ይሆናል፡፡